# ወጣቱና ጫት



2ተኛ ዕትም

ጋዜጠኛ ወ/አማኑኤል ጉድሶ
Woldeamanuel Gudisso (M.A. Journalism)

04-567-0001-0115

# ወጣቱና ጫት

መ.ቁ 60

## የመቃም ታሪክ

## ከአዝናኝ፣ አስተማሪና አሳዛኝ ገጠመኞች ጋር

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት
Arada Sub-City Woreda 10 Culture & Tourism Office

ጋዜጠኛ ወልደ አማኑኤል ጉድሶ
Woldeamanuel Gudisso(M.A.journalism)

ጥር 2007

©የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

© All Writers rights are reserved

**ደራሲ**

ወልደአማኑኤል ጉድሶ

0940 615468

wgudissoa@yahoo.com

**<u>የግራፊክስ ዲዛይንና ሌይአውት ስራ</u>**

ዘካሪያስ ግርማ

0911 94 58 40 ሀዋሳ

**<u>የኮምፒውተር ጽሁፍ</u>**

ወ/ሮ ጽጌ አበበ

**<u>ልባዊ ምስጋና</u>**

ሁለገብ ድጋፍ ላደረጉት አካላት ሁሉ ከአክብሮት ጋር።

## ማውጫ

መግቢያ .................................................... 2

የጫት ተክል ባህላዊ፣ ታሪካዊና ሳይንሳዊ ቅኝቶች ........ 8

ወጣቱና ጫት .................................................. 44

ስለ ጫት ማን ምን አለ? ..................................... 58

በጫት ዙሪያ ልዩ ልዩ አስተያየቶችና ገጠመኞች ............ 69

ማጠቃለያ .................................................... 88

ጫት ትናገራለች ............................................. 100

የዘገምተኛዋ የጫት ምርቃና አባባሎች ...................... 102

አከባቢያዊ የጫት መጠሪያዎች .............................. 103

ማጣቀሻዎች ------------------------------------------ 105

# መግቢያ

በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩና በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚኖሩ ህዝቦች ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ህይወታቸውን ሲጎዱ በሚችሉ በርካታ ሱሶች ተጠምደው አሊያም ወድቀው ይገኛሉ። በባህላዊና ማህበራዊ አኗኗር ውስጥም የሰውነት አነቃቂ ናቸው በሚል የተሳሳተ እምነት አመጣጣቸው ከዕጽዋት የሆኑ ተክሎችን በፈሳሽ፣ በክኒኒ አሊያም በማኘክ ይወስዳሉ። የሱሶቹ ተጠቃሚዎች ሱሶቻቸውን ለዕለት ውሎ - አዳር የግድ አስፈላጊ ከሆኑ መሰረታዊ ነገሮች እንደ አንዱ አድርገው ያዘወትራሉ። ዕጾቹን የዕለት ከዕለት ተግባራቸው ብቻ ሳይሆኑ የህይወታቸው አንዱ አካል አድርገውታል ማለትም ይቻላል።

ከተጠቃሚዎቹ መካከል አንዳንዶቹ ራሳቸውን ወደ ኋላ መለስ ብለው በማየት ግለሰባዊና ማህበራዊ ህይወታቸው ምን እንደሚመስል መፈተሽ ወደማይችሉበት ደረጃ የደረሱ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ሱሶቻቸውን እየተገለገሉ ለመቀጠልም ሆነ ለመተው መወሰን ተስኗቸው መንታ መንገድ ላይ የቆሙ ናቸው። አንደኛውን ገብተንበታል በማለት ራሳቸውን በራሳቸው በማታለል ቢያንስ ቢያንስ አጋጣሚና ወቅት እየጠበቁ ፍላጎታቸውን ያረካሉ። የራሳቸውን ውስጣዊ ጥንካሬ በራሳቸው በመናድም እስከ ህልፈተ-ሞታቸው ላለመተው ቃል የገቡ ይመስላሉ። ራሳቸውን ለሱሶቹ አስገዝተዋል። አሊያም ተሸንፈው እጃቸውን ሰጥተዋል።

በዚህም የተነሳ ተጠቃሚዎቹ ከራሳቸው፣ ከቤተሰቦቻቸውና ከሌሎችም ማህበራዊ መስተጋብሮች እየተገለሉ ስለሚመጡ



በማይመለሱበት የስነልቦና ቀውስ ውስጥ ይዘፈቃሉ። ቁማርተኛ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ራዕይ-የለሽ፣ ብኩን... ይሆናሉ። ለአጉል እምነት ተከታይነት፣ ለጤንነት ችግር፣ ለእምነት ማጉደል እየተዳረጉ ይመጣሉ። ሥራን በብቃትና በጥራት ያለማከናወን፣ ግለኝነት፣ መግባባት ያለመቻል፣ ራሳቸውን ከመቻቻል ውጪ ማድረግ ከሁሉም በላይ ደግሞ ወንጀለኝነትን ከጀርባቸው አስከትለው ይጓዛሉ። ተስፋ መቁረጥ፣ ገለልተኝነት፣ ብሎም ኢ-ተጨባጭ ወደሆነ ምናባዊ የፍልስፍና ዓለምም ውስጥ ጭልጥ ብለው ይገባሉ። ተጠቃሚዎቹ ለተጠቃሚነታቸውም ሆነ ለሱሰኝነቱ ከሚሰጡት ምላሾች መካከልም «ድፍረት» እናገኝበታለን፣ ባህላዊ መድሃኒት ነው፣ በአጭር ጊዜ መክበር የሚያስችል ግዙፍ ሃብት በአቋራጭ የማግኘት ምኞትና ህልም፣ መነቃቃት፣ ጥቅሙንና ጉዳቱን አስቀድሞ ባለማወቅ ስር የሰደደ ሱስ ውስጥ ዘልቀንበታል የሚሉ ... ይገኙባቸዋል። በዚህም የተነሳ ሱሶቹ የተጠቃሚዎቹ አንዱ የህይወት ጎዳና ይሆናሉ። ያለነዚህ ሱሶች የሚኖሩ አይመስሏቸውም። ዜጎቹ ያለ ሱሶቹ መኖር ቢችሉም ሱሶቹ ደግሞ ዜጎቹ ካልተጠቀሙአቸው እንደሚከስሙ ውስጣዊ ስሜቶቻቸውን በቁርጠኝነት ያለማሳመን ችግር ገዝፎ ይስተዋላል። የተጠቃሚነት ምዛን ሲታይም አንዱ ከሌላ ጎልቶ የሚታይባቸው አከባቢዎች በተጨባጭ እናገኛለን። የሰው ልጆችን ህይወት በሱሰኝነት አዙሪት እያሽከረከሩ የሚገኙ አደንዛዥ እጾች ቁጥር እንደየስያሜያቸውና ዐይነታቸው የሚለያይ ሲሆን የአደንዛዥነታቸውና የአፍዝዝነታቸው ባህርይም እንደየአከባቢው የአየር ንብረትና የአፈር ጸባይ ከፍና ዝቅ ይላል። የተጠቃሚዎቹ ጾታዊ ስብጥር፣ ዕድሜ፣ አኗኗርና መጠንም ከሀገር ሀገር እንዲሁም ከአከባቢ አከባቢ በመብዛት ወይም በማነስ ይገለጻል። በአንዳንድ ሀገሮች ዕጾቹ የህዝቡ

ማህበራዊ ችግር ብቻ ሳይሆኑ የመንግስታትም ትልቁ ራስ ምታት መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ሆኗል።

ከነዚህም ማህበራዊ ምጣኔ-ሀብታዊና ፖለቲካዊ ችግር ከሚፈጥሩ ዕጾች መካከል ኮኬይን፣ ሄሮይንና ማሪዋና ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው። ለአብነትም እንደ ላቲን አሜሪካዎቹ ፔሩ፣ ቦሊቪያ፣ ሜክስኮ፣ አርጀንቲናና ብራዚል በመሳሰሉ ሀገሮች ተጠቃሚዎቹ ብቻ ሳይሆኑ እነዚህኑ ዕጾች ከቦታ ወደ ቦታ በማዘዋወር እጅግ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ያጠራቀሙ ግለሰቦች (ቡድኖች) እያደረሱ ያለው የህይወትና የንብረት ውድመት ወደር-የለሽ ነው። ዘመናዊና የከባድ ጦር መሣሪያ ባለቤት ጭምር በመሆን በስውር የራሳቸውን ተንቀሳቃሽና ታጣቂ ሠራዊት በማደራጀት መንግስታትን በአደገኛ ሁኔታ በመፈታተን ላይ ይገኛሉ። ሀገራዊና አህጉራዊ ብቻ ሳይሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን በመፈጸምና በማስፈጸምም ይታወቃሉ። ይህንኑ ድርጊታቸውን ለማስቆም መንግስታት የሚሰነዝሩባቸው ጥቃቶች በቀላሉ አላስቆሙአቸውም፣ አላንበረከኳቸውም። አንዱ ሌላውን በዐይኑ-ቁራኛ እየተጠባበቁና አጋጣሚ ሲያገኙም እየተጠቃቁ፣ አንዱ ሌላውን እየተፈታተኑ (እያሳደዱ) ይኖራሉ። ከላይ ስለተጠቀሱት የአደንዛዥ ዕጽ ዓይነቶችና አብቃይ ሀገሮች ብዙ መረጃ አዘል ጭብጦችን ማቅረብ የሚቻል ቢሆንም ይህ መጽሀፍ የሚያተኩረው የሀገራችን ምርት በሆነው ጫት ላይ ብቻ ይሆናል። ስለሆነም ወደዚያ ላራምዳችሁ ነውና ይፈቀድልኝ!

ጫት ዛሬ በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች/አስተዳደሮች የሚበቅል ተክል ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም በፍጥነት እያዳረሰ የሚገኝ ጥንታዊና ኢትዮጵያዊ ተክል ነው። ከመዛግብቶች እንደምንረዳው ለረጅም ዘመናት ከሌሎች የሃገራችን አከባቢዎች



በገዘፈ መልኩ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ብቻ ተወስኖ የነበረው ጫት በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የሀገራችን አከባቢዎች «በአናቃቂነቱ» የሚዘወተርና በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ ተክል ሆኗል። በተወሰኑ አከባቢዎች ያለው የጫት አጠቃቀም ስርዓት ያለ ጫት ህይወት ትርጉም የሌለው እስከሚመስል ድረስ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ይቃማል። የተጋነነ ነው የሚሉ እንዳሉ ሁሉ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እየደረሰ ነው የሚሉ ታዛቢዎችም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

ጫት በእምነት ስፍራዎች፣ በትምህርት ተቋማት፣ በመዝናኛ ቦታዎች፣ በቲያትር ቤቶች፣ በአደባባዮች፣ በመኖሪያ ቤቶች፣ በሲኒማ አዳራሾች፣ በመስሪያ ቤቶች፣ በገበያዎች በአጭሩ በሁሉም ጊዜና በሁሉም ቦታ ሲቃም ይስተዋላል። በዚህም ሁለገብ አጠቃቀም የተነሳ "የሁሉም ለሁሉም" ማህበራዊ አገልግሎቶች የሚውል ትይንተ-ዕጽ እስከ መባል እየተቃረበ ነው። በሀገራችንም ሆነ በሌሎች አብቃይና አብቃይ ባልሆኑ ሀገሮች ጫት ባይቃምም ይተከላል፣ ባይተከልም ይቃማል። በጫት ዕርቅ ይካሄዳል። ጥናቶችና ምርምሮች ይካሄዳሉ። ጋዜጠኛው ዘገባ ይሰራል። ደራሲው በጫት ሃይል አዕምሮውን አነቃቅቶና ጨምቆ ሃሳብ ያመነጫል። ሙዚቃኞች ውዝዋዜዎቻቸውንና የፈጠራ ስራዎቻቸውን በጫት ንቅቀት /ሞቅታ/ ያደምቃሉ። በጫት እርሶ አደሩ «የዐይን መክፈቻ» ነው ብሎ በመቃም ለራሱ ጤንነትና ጉልበት ጥንቃቄ ሳያደርግ ማሳውን ከጠዋት እስከ ቀትር ብልት በብልት ይተረትራል።

በብዙ የሀገራችን አከባቢዎች በቁልምጫ (የማጣፈጫ ስሙ) በርጫ ተብሎ የሚታወቀው ጫት መረጃው ተአማኒነት እንዲኖረውና ትክክለኛ ምንጮችን ለአንባቢዎችና ተመራማሪዎች ለማስጨበጥም ሰዎችን በማነጋገር፣ መጽሀፍት

በማንበብ፤ ድህረ-ገጾችን በመቃኘት፤ ጋዜጦችን በማገላበጥ፤ ተጠቃሚዎችን በማግባባት በድምሩ ከአንድ መቶ በላይ ምንጮችን ለመዳሰስ ጥረት አድርጌአለሁ። በዚህም ሂደት መቃሙን የማይደግፉ በርካቶች እንዳሉ ሁሉ መቃምን የሚያበረታቱ ብዙ ተጠቃሚዎችም አጋጥመውኛል። ከነዚህም መካከል ባህላችን ነው፤ አድገንበታል፤ የአኗኗር ስልታችን ነው፤ እንዝናናበታለን፤ አልጎዳንም፤ አልተጎዳንምም፤ ትንሽም ይሁን ትልቅ የሚያሰክር (የሚያመረቅን) ከሆነ ክልክል (ሐራም) ነው፤ የስካር ወይም የመነቃቃት ስሜት እያለ ጸሎት መደረግ የለበትም ---- የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል። መጽሀፉን «ወጣትና ጫት» ያልኩበት ምክንያትም በተለይም ለወጣቱ ትውልድ አስተማሪና አዎንታዊ ብሎም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አሳዛኝ ጎን ያላቸውን መልዕክቶች የማስተላለፍ ግዴታዬን መወጣት አለብኝ የሚል ጽኑ እምነት ስለነበረብኝ ነው። ተስፋ ሳልቆርጥ እነሆ እውን አድርጌአለሁ።

« ***ወጣትነት ወደ ብልጽግና ለመረማመድም ሆነ ወደ ድህነት ለመውረድ ምርጥ ጊዜ ነው።»*** ይባላልና ወጣቱ ማንነቱን የሚወስነው በወጣትነት ዕድሜው በዐይኑ ከሚያያቸው፤ በጆሮው ከሚሰማቸው፤ ከሚዳስሳቸው፣ ከሚያነባቸው፤ ከገጠመኞቹ፤ ከውይይቶች፤ በጥቅሉ በልዩ ልዩ ወቅቶችና ቦታዎች ከሚያጋጥሟቸው አስደሳችና አሳዛኝ ክስተቶች በመነሳት ነው። በነዚህ ልዩ ልዩ ገጠመኞች የራሱን ማንነት ከወዲሁ ጠንቅቆ በመረዳት ወዴት፤ እንዴት፤ መቼ፤ ከማን ጋር መሄድ ወይም ማንን መከተል እንዳለበት መወሰን ካልቻለ ደራሽ ወንዝ ይዞት ይሄዳል። እሲያም ወንዙ በመውሰድ ላይ እያለ መንቃት ያለ በመሆኑ እየወሰደ ያለው ከህያዋን ለይቶ



ከበድን አካላት ጋር እያጋጨ ነውና የአካል በተለይም የስሜት ጉዳት ማስከተሉ አይቀሬ መሆኑን በተግባር እያየን እንገኛለን።

አንዳንድ ችግሮችን አሳንሰው የሚያዩ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ከሚገባ በላይ አግዝፈው የሚመለከቱም ጥቂቶች አይደሉም። ሁለቱም የየራሳቸው ገንቢ ምክንያቶች እንዳሉ ሁሉ አፍራሽ መዳረሻዎችም አሏቸው። ራሳቸውን ወደ ትክክለኛ አቅጣጫ ለመምራት ወይም ለማቃናት በተለይም ወጣቶች ከወዲሁ ጠቃሚውንና ጎጂውን በማወቅ ለለውጥ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ዘመናትን ባስቆጠረና አሉታዊ ጎኑ በሚያመዝነው ባህል ሳቢያ በውስጣችን የተገነባው አርጌ አስተሳሰብ መወገድ አለበት። ጫት በመቃም የማገኘውን ደስታ በምን እተከዋለሁ? መጠጥ በመጠጣት የማገኘውን መዝናናት በምን አካክሳለሁ? ለነዚሁ ውሎዎች (አዳሮች) የማውለውን ጊዜ በምን አካክሳለሁ/አሳልፋለሁ --- ወዘተ ብለው አስበው ያውቃሉ?። እስቲ ራስዎን በራስዎ ይጠይቁ! ምላሽም ይስጡበት።

ይህንን መጽሀፍ በማዘጋጀት ላይ እያለሁ አንድ ጥቅስ ማንባቤ ትዝ አለኝ። ጥቅሱም «እኛ መቃብሮቻችንን የምንቆፍረው በገዛ ባህሪያችን ነው።» የሚል ነው። የመቃምን ባህል በጣም አሳንሰን ወይም አግዝፈን ሳናየው አካባቢያችንን ለመቃኘት እስቲ ቀጠሮ እንያዝ። ውጫዊ ግፊት "ማሳሰቢያ" ይሰጣል፤ ዘላቂ መፍትሄ ግን አያመጣም። በገዛ ራሳችን የራሳችንን መቃብር ላለመቆፈር ባህርያችንን መቀየር አለብን፣ እንችላለንም። ባህሪያችንን ለመቀየርም ከውጫዊ ግፊት ይልቅ ራሳችን በራሳችን ላይ የምናደርገው ተጽዕኖ ወይም ውሳኔ ዘላቂ ውጤታማነት ይኖረዋል። ይህንን ምክር ለሚከተሉ ሁሉ ጥቅሱ የስኬት መንደርደሪያ ይሆናልና ይጠቀሙበት።

ስለሆነም በዚህ ጽሁፍ በጫት ምርት ዙሪያ ሰፋ ያሉና በመረጃ የተደገፉ ጥናታዊ ጽሁፎችን ከተለያዩ ገጠመኞች ጋር በማከል አቅርቤአለሁ። ጽሁፉ በጎልማሳነትና በተለይም ደግሞ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ለሚገኙ አንባቢያን እያስተማረ ያዝናናል፣ አንዳንዴም እያሳዘነ አዎንታዊ ግንዛቤ ያስጨብጣል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ። አንባቢዬ ከመነሻው ጀምሮ እንዲረዳልኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር ይህ ጽሁፍ የታለመው የማንንም ስብእና ለመንካት፤ ማንንም ለማስደሰት ወይም ለማሳዘን አለመሆኑን ነው። የተዘጋጀው ጥቅሙንና ጉዳቱን በተለይም ጎጂ ጎኑን በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በመጠቆም ተጠቃሚው የራሱን ግላዊ ውሳኔ እንዲወስን ማሳየት ነው። በመጽሀፉ ዙሪያ አስተያየቶችን መስጠት ለሚፈልጉ አንባቢዎቼ ሁሉ አስተያየታቸውን ለመቀበል ዝግጁ መሆኔን በአክብሮት እገልጻለሁ።

ጋዜጠኛ ወልደአማኑኤል ጉድሶ

Arada Sub-City Woreda 10
Culture & Tourism Office



## የጫት ተክል ባህላዊ ታሪካዊና ሳይንሳዊ ቅኝቶች

ጫት ከቋሚ ተክሎች ውስጥ የሚመደብ ኢትዮጵያዊ ተክል ነው። ምርቱም ሆነ ተክሉ ራሱ በሀገራችን ጫት ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን በሌሎች ሀገሮች ደግሞ እንደየሀገሮቹ ቋንቋ ወደኛው መጠሪያ ተቀራራቢ የሆኑ ስያሜዎች አሉት። በአጠቃላይ ጫት እንደየአከባቢዎቹ ሁኔታ ከስድሳ በላይ መጠሪያዎችና ስድስት ሳይንሳዊ ስያሜዎች እንዳሉት መረጃዎች ያሳያሉ። ከነዚህም መጠሪያዎች መካከል የአቢሲኒያ ሻይ፤ የአፍሪካ ሰላጣ፤ የቡሽማኖች ሻይ፤ የዐረቦች ሻይ፤ khat, qat, kat, chat, katyna, mirra, murungi, tschat, Catha, tohai, quat, jaad, caftan, mlonge, salahin, tohat, mulungi, iubulu, mulu, crafta, jima, bercha… የሚሉ ይገኙባቸዋል። ለጫት የተለያዩ ስሞች መስጠት የተጀመረው ከ19ኛ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲሆን ከ18ኛ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ በመግለጽ የሚከራከሩ ጸሃፊዎችም አሉ። ለዚህም ምስራቅ አፍሪካንና የዐረብ ባህረ ሰላጤን ይጎበኙ የነበሩ ተመራማሪዎች ዐይነተኛ ተጠቃሾች ናቸው።

የጫት ተክል በስነ ህይወት ጠበብቶች አጠራር «ካታ ኤዱሊስ» በሚል ሳይንሳዊ ስሙ ይታወቃል። ይህንኑ ሳይንሳዊ ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ በመስጠት ለዓለም ህዝብ ያስተዋወቀው ፒተር ፎርስከል[2] የተባለና እ.አ.አ ከ1736-1763 የኖረው ሲዊዲናዊ የስነ ህይወት ተመራማሪ ነው። ፎርስከል የጫት ተክልን ያገኘው ከሌሎች ግብረ አባሮቹ ጋር በመሆን የዓረብ ባህረ ሰላጤን በሚጎበኝበት ወቅት ነበር። እስከ 18ኛ ክፍለ ዘመን ጫት በሳይንሳዊ የምርምር ዓለም በተለይም ደግሞ በአውሮፓ አይታወቅም። ፎርስካል ወደዚያ አከባቢ በመምጣት ሊመራመር

የቻለው የዴንማርክ ንጉስ የነበረው ፍሬደሪክ አምስተኛ አዘጋጅቶት በነበረው አሰሳ (ኤክስፐሎረሽን) ወቅት ነው:: ፎርስካል በፊዚክስና በስነ-ህይወት ተመራማሪነት ባደረገው ተሳትፎም ጫትን ከበርካታ ተክሎች ጋር ለመሰብሰብ በቅቶ ነበር። ጫት «ካታ ኤዱሊስ» ተብሎ የተሰየመበት ምክንያትም ከአምስቱ በጉዞው ላይ ከተሳተፉ አሳሾች ብቸኛ ሆኖ በህይወት የተረፈው የሃኖቬሩ የመልክዓምድር ተመራማሪ ክርስት ነቡር የጓደኛው የ«ካታ-ኤዱሊስ» ማስታወሻ መጠሪያ እንዲሆን በመፈለጉ ነው::



*ጫት የምግብ እህል አርሻን እንዲህ ጠቅልሎ ይይዛል::*

ስለ ጫት ተክል ለመጀመሪያ ጊዜ በህትመት የተደገፈ ማስረጃ የተገኘው እ.አ..አ በ1065 ክታብ አል-ሴይዳና ፊ አል-ክታብ በተባለ የመዲሃኒት ቅመማ ጥናት ላይ ሲሆን ጸሃፊውም አቡ



አል-ብሩኒ ይባላል:: በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ አል-ብሩኒ ተክሉ የቱርክስታን እንደሆነ አስፍሯል [3]:: አል መቅሪዚ የተባለ የዓረብ ጠቢብ ደግሞ ከ1364-1442 በነበረው የህይወት ዘመኑ የአቢሲኒያን የጦርነት ታሪኮች በመፈተሽ የሚከተለውን ጽፎ ነበር:-

«....ከነዚህም መካከል ጫት የሚባል ተክል ይገኛል። እሱም ፍሬ አልባ ተክል ነው:: ሰዎች ቅጠሉን ይመገባሉ:: ቅጠሉም ትናንሽ የብርቱካን ቅጠል ይመስላል:: ተክሉ አስተሳሰባቸውን እንደሚያሰፋና የዘነጉትን ነገር እንደሚያስታውስላቸው ተጠቃሚዎቹ ይናገራሉ:: ተጠቃሚዎቹ ደስታ እንደሚሰጠቸው፤ የምግብ ፍላጎታቸውን ብሎም ወሲብና እንቅልፍ እንደሚቀንስ ያስረዳሉ:: ቅጠሉን መቃሙ ለአከባቢው ነዋሪዎች ከምንም ነገር በላይ በናፍቆት የሚጠበቅና አንጊ ተግባር ነው::»[4]

ጫት የየት ሀገር ብቃይ ተክል እንደሆነ በርካታ ጻሃፊዎች የየራሳቸውን የጥናትና የምርምር ውጤቶችን አስነብበዋል። ይፋዊ የሆኑና ያልሆኑ ምንጮችን በመጥቀስም ጭብጦቻቸውን ተዓማኒ ለማድረግ ብርቱ ጥረት አድርገዋል:: በአፈ-ታሪክ የሚነገሩ ህያው አባባሎችም አሉ:: ከተመራማሪዎቹ አንዳንዶቹ እርስ በርስ የሚቃረኑ ሃሳቦችን ቢያቀርቡም አብዘኛ ዎቹ ጸሀፍት ግን የጫት መገኛ ሀገር ጥንታዊቷ አቢሲኒያ (ኢትዮጵያ) [1] እንደሆነች ይስማማሉ::

ዘመናትን ያስቆጠረውና እንግሊዝ ሀገር ካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው ታሪካዊ ጽሁፍ በበኩሉ እንዳመለከተው ጫት በየመን ሀገር ከስድስተኛ መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ ጥቅም ላይ እንደዋለና ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ መግባቱን አትቷል:: እሮዊድ የተባለ

ተመራማሪ ደግሞ እዛው ዩኒቨርሲቲ የሚገኛውን ሌላ ጽሁፍ አስረጂ አድርጎ እንደገለጸው ጫት ከስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ላይ ውሏል::[5] አብዱል ቃድር የተባለ የአረብ ጸሃፊ በበኩሉ ጫት ከአቢሲኒያ ወደ አረብ ሀገሮች ከቡና በፊት መግባቱን ጽፏል::

ኢትዮጵያ ከጫት መገኛ ሀገርነት ጋር ተያይዞ በተክሉ ውስጥ ለመዲሃኒትነት የሚያገለግሉ ንጥረ ነገሮች መኖራቸውን የህክምና መዲሀኒቶች በሚለው የዐረብኛ መጽሃፍ ያረጋገጠው ነጅብ አድ-ዲን አዝ ሳማራቃንዲ (በ1222) የተባለ ቱርክስታናዊ ዜጋ ነው::[6] መገኛ ሀገሩ ኢትዮጵያ የሆነው ጫት መነሻውን ኢትዮጵያ አድርጎ የመን፣ ኬንያ፣ ማላዊ፣ ዑጋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ የዐረብ ባህረ ሰላጤ ሀገሮች፣ ኮንጎ፣ ዚምባብዌ፣ ዛምቢያ፣ ደቡብ አፍሪካና ሌሎችም ሀገሮች በስፋት ተዛምቷል:: ረጅም ርቀት ተጉዞ ደግሞ ቱርክ፣ አፍጋኒስታን፣ ቱርክሜኒስታን፣ ኡዝቤክስታን፣ ፓክስታን ወዘተ ጫት ይገኝባቸዋል ከሚባሉት ሀገሮች ጥቂቶች ናቸው::

በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በዐረብኛ የተጻፉ መረጃዎች ስዳሰሱ በተለይም የምስራቁ የሀገራችን ክፍል በሆነው የሀረርጌ ደጋማ አከባቢዎች ጫት በብዛት ይመረት እንደነበርና ለየመናውያኑ ከስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ መግባትም መነሻ ይኸው ሀረር ነው የሚሉ የጽሁፍና የትውፊት መገለጫዎች ይገኛሉ:: መረብ የሚባል ደራሲ እንደጻፈው:-

**«የዴልፊክ እባቦችን የሚያነቃቃቸው የጫት ጪስ ነበር ፤ የትሮይ ሄለን ለቴሌማኩስ የሰጠችው የሆመር ማደንዘዣም ጫት እንጂ ሌላ ነገር አልነበረም፣ ታላቁ አሌክሰንደርም ሠራዊቱ በድብርት ወረርሽኝ ተጠቅቶ በነበረበት ጊዜ በመድሃኒትነት ተጠቅሞበታል::»[7]**



በአንዳንድ መረጃዎች መሰረት ይኸው ዶክተር ፒተር መራብ የሚባል ተመራማሪ ከተመራማሪነቱ በተጨማሪ (1876-1930) የዳግማዊ ምንልክ የፍትህ ችሎት ሀኪም ሆኖ አገልግሏል ይላል::

በጫት ዙሪያ የመጀመሪያው የዐረብኛ ማጣቀሻ እንደሆነ የሚታመነውና በፓሪስ ብሄራዊ ሙዚየም[8] የሚገኘው የመካከለኛ ክ/ዘመን ጽሁፍ እንዳመለከተው የይፋት ንጉስ በመረብ ከተማ ውስጥ «ህዝቡ በጣም ይወደዋል» በሚል ስሜት ጫትን ለመትከል ወስኖ ነበር:: ከ1314-1344 በኢትዮጵያ ስልጣን ላይ እንደቆየ የሚነገርለት ንጉስ ዓምደ ጽዮን ጫትን በማዘወተራቸው በሚመስል ሁኔታ በ1333 በሙስሊሞች ላይ ጦርነት አውጆ እንደነበረም አንዳንድ መረጃዎች ያመለክታሉ::

በዚሁ ንጉስ ዜና መዋዕል (Chronicle) ላይ ፒተርስና ደረክ የተባሉ ጸሀፍት እንዳመለከቱት የይፋት ንጉስ በክርስቲያኖች ላይ ጦርነት ከማወጁ በፊት «የራሴ አደርገዋለሁ:: እተክለዋለሁም:: ምክንያቱም ሙሲሊሞች ይወዱታልና» ማለቱ የተጻፈ ሲሆን ይኸው መረጃ በፓሪስ ቤተመጻህፍት ይገኛል:: በጣም አስገራሚው ነገር ደግሞ ጫት ወደ ሀረር የገባው በታላቁ አሌክሳንደር ነው፣ ምክንያቱም ድብርትን ወይም የስንፈተ-ወስብ ወረርሽኝ ለመከላከል ነበር የሚሉ የጽሁፍ መረጃዎች ከላይ በተገለጸው ምንጭ(7) መኖር ነው:: ጫት የኢትዮጵያ ነባር ምርት መሆኑን ካረጋገጡ ተመራማሪዎች አንዱ የሆነው ቦብ ህልስ «ጫት ከሀረር ወደ የመን የገባው በአንደኛውና በስድስተኛ ክፍለ ዘመናት መካከል ነው»[9] በማለት ጽፏል::

ሰይድ አፍታብ የተባለ ፓክስታናዊ እንደጻፈው ጥንት የባሪያ አሳዳሪዎች ሰራተኞቻቸው በከባድና በባህላዊ መንገድ የጉልበት ስራ በሚሰሩበት ጊዜ እንዳይተኙ ወይም እንዳይደክማቸው

ጫትን ያቀርቡላቸው ነበር (Aftab,et.al1987, p:45-48), Ratsch, park street press,1998.) ብሏል። እነዚሁ አሰሪዎች ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ባህል መሰረት ለትዳር የደረሱ ልጃገረዶች ድንግልናቸውን እንደጠበቁ እንዲቆዩ የሚንከባከቡአቸውን ወጣቶች ወሲባዊ ስሜታቸው እንዳይነሳሳና እንዲዳከም ጫት ያስቅሙ እንደነበረም አፍታብ ጽፏል።

አቢሲኒያውያን ቡናን እንደ አናቃቂ ተክል ብቻ ሳይሆን በውጊያ ጊዜ የጦረኞች ምግብ (as a battle food) አድርገው ይጠቀሙ እንደነበረ የጻፈው አፍታድ የጫት ተክል ማርን ለማቅለም ወይም ወደ ጠጅነት ለመለወጥ ይጠቀሙ ነበር ብሎ ከላይ በተገለጸው መጽሀፉ አስነብቧል። ለዚህ ጽሁፉ መነሻ ሊሆን የሚችለው ምናልባትም ጌሾ ጠጅ ለመጣል አገልግሎት ሲውል በማየቱ ሊሆን ይችላል። የእስልምና ሀይማኖት መዛመትን ለመከላከል አቢሲኒያውያን ከደቡብ እስከ ምዕራብ አረቢያ ዘልቀው ወረራ ማድረጋቸውን የጻፈው አፍታድ ቡናም እንዲሁ ከኢትዮጵያ መግባቱን አረጋግጦ በመጻፍ ባሳፈረው ሀተታው " black as devil, hot as hell, pure as an angel & sweet as love. " (ጥቁር እንደ ሰይጣን፤ ፍል እንደ ገሃነም፤ ንጹህ እንደ መላዕክት እና ጣፋጭ እንደ ፍቅር) ተብሎ ይወደስ እንደነበረም ገልጾአል። አፍታድ ጫት ለኢትዮጵያውያን በውጭ ሀገር ገበያዎች ያለውን ጠቀሜታና ተፈላጊነት ሲያብራራም ባሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መስመሩ እየሰፋ ከመምጣት ጋር ተያይዞ ተጠቃሚዎች ወደሚገኙባቸው መዳረሻዎች ሁሉ በቀላሉ ማድረስ ስለሚቻል ጉልህ ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ማድረጉን ጠቅሷል።

ከዚህም በተጨማሪ ትሪምንግሃም የተባለ ተመራማሪ በጫት ዙሪያ ጥናት አድርጎ እንደገለጸው ጫት ወደ ሀረር የገባው



የሀረር ከተማ የመጀመሪያዎቹ ነዋሪዎች በሆኑት ጥንታውያን አደሬዎች ወይም በዛሬዎቹ አጠራር በሀረሪዎች ነበር። የዚሁ ጸሃፊ መረጃ እንደሚያመለክተው በ1887 እስከተካሄደው የጨለንቆ ጦርነት ድረስ ጫት በሀረሪዎች ብቻ በሚስጢር ተጠብቆ የቆየ ሲሆን ከዚያ ጦርነት በኋላ ወደ ሌሎች አከባቢዎች በማይታመን ፍጥነት ተሰራጭቷል። በዚህም ጦርነት ሳቢያ ከሀረሪዎች ብዙ ተዋጊዎች እንዳለቁ ይነገራል።[10]

መነሻው ከወደ ሀረር እንደሆነ የሚነገረው አፈ-ታሪክ እንደሚያመለክተው ደግሞ ጫት ለሰው ልጅ የተገለጸው ለመላዕክት ወይም ለሁለት የሃይማኖት አባቶች ነበር ይባላል። እነዚህም ሁለቱ የሀይማኖት አባቶች ለረጅም ሰዓታት ጸሎት ማድረግ ነበረባቸውና ይህንኑ ጸሎታቸውን ሳያጠናቅቁ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል። ጸሎት አድራጊዎቹ ባጋጠማቸው ሁኔታ አዝነው ለፈጣሪ ተማጽኖ ያቀርባሉ። ፈጣሪ በጸሎት ወቅት ብርታት የሚሰጣቸውን ነገር እንዲያቀርብላቸው ጸሎት አቅርበው በዚህም ሳቢያ ይኸው ተክል እንደተገለጸላቸው አፈ-ታሪኩ ያስረዳል።[11]

ግሪንዌይ ቦብ ሂል፤ ትሪምንግሃምን ምንጭ አድርጎ እንደጻፈው የሙስሊም እምነት ተከታይ የሆነው ሼክ ኢብራሁም አቡ ዛሀሩብ ለሃይማኖታዊ ተልዕኮ ወደ ሀረር መጥቶ በነበረበት ወቅት እዛው የጫት ተጠቃሚ ሆኖ መቅራቱን ጽፏል። እርስ በርስ የሚጋጩ መረጃዎች ስለመኖራቸው ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ በፓሪስ ብሄራዊ ሙዚየም የሚገኝ አንድ ሌላ መረጃ እንደሚያመለክተው ስለ ጫት ለመጀመሪያ ጊዜ በዐረብኛ ቋንቋ የተጻፈው በአብዱል ቃድር ሲሆን ዘመኑም እ.አ.አ. 1587 ነበር።[12]

በዚሁ ምንጭ እንደተመለከተው ቡናን ከኢትዮጵያ በ1454 በማምጣት ለአረቡ ዓለም ያስተዋወቀው ሼህ ጌማልድን አቡ መሀመድ ቢንሳይድ ነው ። ይህም የሚያመለክተው ቡና ለዓለም ህዝብ ከታወቀበት ከስድስት መቶ ዓመታት በፊት ጫት በኢትዮጵያ ይታወቅ እንደነበረ ነው።[13]

ሌዊን በበኩሉ ጥንታውያን ግብጾች ጫትን ከተክሎች ሁሉ የተቀደሰ ነው ብለው ስለሚያምኑ «መለኮታዊ ምግብ»[14] ብለው ይጠሩ ነበር ብሏል። እሮዊድ ኬፐል እና ኦሪኒላስ የተባሉ ጸሃፊዎችን መነሻ አድርጎ ሌዊን በማብራሪያው የጫት ተክል በየመን ከስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ጥቅም ላይ መዋሉን አስረድቷል። ከዚያ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ይዘወተር እንደነበርም እንዲሁ።[15] በዘመኑ የኢራን አንዱ ግዛት በነበረውና በዛሬው አጠራር ኡዝቤክስታን ተብሎ በሚታወቀው ሀገር የተወለደው አቡ-አል- ብሩኒ የተባለ የህዋ ሳይንስ ተመራማሪ (ሴፕቴ 5 973-1048) ጫት በዓረብ ሀገሮች በ1065 ለመድሃኒትነት ይውል እንደነበረ ጽፏል። ይህ ተመራማሪ ከጫት በተጨማሪ በስነ ህይወትና በህዋ ሳይንስ ላደረጋቸው የምርምር ስራዎች ባለውለታነት በኡዝቤክስታን አንዳንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በስሙ እንዲሰየሙ ተደርጓል።

ጫት በኢትዮጵያ ስለመገኘቱና ኢትዮጵያን በወቅቱ ያስተዳድር በነበረው በንጉስ አምደ ጽዮን (ከ1314-1344) የስልጣን ዘመን በርካታ ተመራማሪዎች የነበረባቸውን ጥርጣሬ ያስወገደው ሳማረቃንዲ የተባለ የፋርስ ባህረ ሰላጤ ህክምና ጠቢብ ነበር። ሳማራቃንዲ በዚሁ መረጃው የጫት መገኛ ሀገር ኢትዮጵያ መሆኑን ያረጋገጠው እ.አ.አ በ1237 ነው።[16] እ.አ.አ በ1968 ኤልካይ በተባለ ጸሀፊ እንደተገለጸው ጫት በሚቃምበት ወቅት



ውስጣዊና ውጫዊ ስሜቶችን ሊያነቃቁ የሚችሉ ንጥረ ነገሮች አሉት። እነዚህም ኢፌዲን፣ ከቲኒን፣ ከቲዲን፣ ኢዱሲን፣ ከቴኖናና አምፌሚን ናቸው። ጫት በተጠቃሚዎች ዘንድ የአነቃቂነት ባህርይ መኖሩ በሌሎቹ ዘንድ ብዙም ሳይታወቅ በምስራቅ አፍሪካና በዐረብ ባህረ ሰላጤ ሀገሮች በዋንኛነትም በኢትዮጵያ፣ በየመንና፣ በኬንያ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ዘንድ ለረጅም ዘመናት ጥቅም ላይ ውሎ እንደነበረ ይነገራል።

ትኩስ ቅጠሉን በቀላሉ ማግኘት በሚቻልባቸው ሀገሮች ጫት በቀላሉ እየታኘከ በውሃና በሌሎች ጣፋጭ የፋሳሽ ዐይነቶች የሚወራረድ ሲሆን ትኩስ ቅጠሉ በማይገኝባቸው ሀገሮች እንደ ሲጃራ ተጠቅልሎ አሊያም በጋያ (ፒፓ) ላይ ተደርጎ ይጨሳል። ከማጨስ በተጨማሪ በደቡብ አፍሪካና በአረብ ባህረ ሰላጤ ሀገሮች በሻይ ቅጠልነትና በምግብ ላይ ነስንሶ በመጠቀም ከወደ ኋላ ለሚገለጹት ቀላል የህመም አይነቶች ፈውስነት ቃሚዎቹ ይጠቀማሉ።

እ.አ.አ አፕሪል 1957 በተባበሩት መንግስታት ድርጅት 12ኛ መደበኛ ስብሰባ ለመጀመሪያ ጊዜ ጫትን በሱስ አማጭ ዕጽነት በመፈረጅ ጠንከር ያለ ትችት ያቀረበችው ግብጽ ነበረች። የግብጽን ትችት መነሻ አድርጎ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በወቅቱ ጫት እንዳይቃም አስገዳጅ ውሳኔ ባያስተላልፍም ጸረ-ዕጽ ኮሚሽኑ በተክሉ ላይ የቅርብ ክትትልና ምርምር እንዲያደርግ አሳስቦ ነበር። የአሜሪካ ደህንነት መረጃ ክፍል ማርች 26 1982 ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡ በርካታ ምርቶች መካከል አንዱ የሆነውን ጫት ለጥንቃቄ (አደንዛዥነቱ በትክክል ያልተጠና ነው በማለት) ጠረፍ ላይ ሲገባ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግ መመሪያ አስተላልፎ ነበር።[17]

ጫት በቃሚዎች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ጎልቶ የሚታወቅ ሳይንሳዊ ጥናት ባይኖርም ቦብ ሂል የተባለ ተመራማሪ በቀጥታ ለአደንዛዥነትና ለሱስ አማጭነት እንክብሎች የምንጠቀመው ገለጻ ለጫት አይሰራም በማለት አቅልሎ አይቶታል። የጫት ተሚጋኞች በበኩላቸው በውስጡ የሚገኘው አንቂ ንጥረ ነገር ስትሙሌሽን (ደስታን) ወይም ኤክሳይትመንት (ሀሴትን) ይፈጥራል ይላሉ፡፡ ንጥረ ነገሮቹ በበኩላቸው በቃሚዎች ዘንድ «ሚርቃና» በመባል የሚጠራው የስሜት ምጥቀት ያስከትላሉ።



*አቦ ሚስማር የሚባለው የአወዳይ ምርጥ ጫት እንዲህ እያማለለ ማህበራዊ ቀውስ ያስከትላል።*

የተለያዩ ዝሪያነት ያላቸው የጫት ዐይነቶች በእኩል መጠን አገልግሎት ላይ ቢውሉ (ቢቃሙ) እንኳን እኩል የማነቃቃት (የማመርቀን) ሃይል አይኖራቸውም። ጫቶቹ የሚመረቱባቸው አከባቢያዊ ሁኔታዎች መለያየት ማለትም የቦታው አቀማመጥ፤ የአየር ጸባዩ፤ የአፈሩ ዐይነት፤ የሚደረግለት እንክብካቤ፤ ወዘተ ቀላል የማይባሉ የይዘት ልዩነቶችን ይፈጥራሉ። በሀገራችን የምስራቅ ሀረርጌው አወዳይ ጫት ከ«ጥራቱ»ም ሆነ



ከተፈላጊነቱ ከፍተኛነት አንፃር ለሁሉም ተጠቃሚ ተደራሽ አይደለም። ተፈላጊነቱ ደግሞ በሀገር ውስጥም በውጭ ሀገርም ላቅ ያለ ነው። በአሁኑ ጊዜ ከተፈላጊነቱ ብቻ ሳይሆን ከዋጋ መናር አንጻርም ከሀገር ውስጥ ቃሚዎቹ ኪሳቸው አበጥ ያለ ብቻ ሲሆኑ ይችላሉ፣ ነውም። በፈዲስ ወረዳ ዑመርኩሌ በሚባል አከባቢ የሚበቅል ጫት ደግሞ እጅግ በጣም ሀይለኛ ከመሆኑ የተነሳ ያደነዝዛል ያፈዛልም። በሚያስከትላቸው ውጤቶች ከወደኋላ የምንመለከተው መረጃ እንዳለ ሆኖ ዑመርኩሌ የሚባለውን ጫት ከቃሙ በኋላ ምን እንደሚሰሩና ወዴት እንደሚሄዱ የማያውቁ ሰዎች ሁሉ ያጋጥማሉ። ለቃሚዎቹ ብቻ በሚታወቅ ውስጣዊ ስነልቦናዊ ብኸርታ/ቀውስ ጭንቅላታቸው አብጦና በባዕድ ነገር ተወርሮ የሚታዩ/ የሚሰማቸውም አሉ ይባላል። በእርሻ ስራ ላይ ሆነው ጣታቸው በስለት ሲቆረጥ እንኳን የማይታወቃቸው እንዳሉም አንዳንድ በአካል ያነጋገርኳቸው ተጠቃሚዎች ይነገራሉ።

ጫት በጊዜያዊ አነቃቂነቱ አርሶ አደሮች የእርሻ ተግባራቸውን ባለ በሌለ ጉልበታቸው ሳይሰለቹና ሳይደክሙ እንዲሰሩ ያደርጋል። ጫት ለባህላዊና ሀይማኖታዊ ስርዓቶች ማድመቂያነት ይውላል። በረጅም የጸሎት ስነ ስርዓት ወቅት እንቅልፍ እንዳይገዛ ያግዛል። ድካም በመቀነስ ጊዜያዊ ብርታት ይሰጣል። ረጅም ጉዞ በእግርም ሆነ በተሽከርካሪ ያስኬዳል። ረጅም ጊዜ ቁጭ አድርጎ ያስጠናል። ጊዜ ማሳለፊያ ይሆናል ወይም ደስታ ያስገኛል እየተባለ ይዘወተራል።

ከተጠቃሚዎች መካከል አንዳንዶቹ ጫት ስኳርን፤ አስምን፤ የአንጀት ውስጥ ተውሳኮችን ያስታግሳል ሲሉ በተቃራኒው ጤንነት ያቃውሳል፤ የምግብ ፍላጎትን ይጫናል፤ እንቅልፍ ይነሳል፤ ሰላም ይከለክላል፤ የወሲብ ስሜት ይቀንሳል፤ በመኝታ

ሰዓት እረፍት ነስቶ ያንቆራጥጣል ይላሉ፡፡ በቃሚው ላይ የሚታየው ምርቃና እንደ ሰው ሁሉ በእንስሳትም ላይ በቀላሉ ይታያል፡፡ በአንዳንድ አፈ-ታሪክ ዐዋቂዎች እንደሚነገረው በሀረር አከባቢ ጫት እንደሚያመረቅን ከሰው በፊት የተገነዘበችው ፍየል ነበረች ይባላል፡፡ በአፈ-ታሪኩ መሰረት እረኛው በየቀኑ ፍየሎችን ለማብላት ወደ ጫካ ያሰማራል፡፡ ከመካከላቸው አንዲት ፍየል ከሌሎቹ ፍየሎች ተነጥላ አንድ ተክል ማዘውተር መጀመሯንና ወደ ቤት ስትመለስም ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ በተነቃቃ ስሜት እንደሆነ በተደጋጋሚ ያስታውላል፡፡ ከዚያም ማታ ወደ ቤት ስትገባ ንቁ የነበረችው ፍየል ጠዋት ጠዋት ተደብራ ያያታል፡፡ይህንኑ ትርዒት ያስተውል የነበረው እረኛ ሚስጥሩን ለማወቅ ጉጉት አድሮበት መቅመስ ጀመረ፡፡ ተክሉ ጊዜያዊ ንቅቅት/ምጥቀት የሚፈጥር ተክል መሆኑንም ተረዳ፡፡ ከዚያ በኋላ እሱም የዚሁ ተክል ተጠቃሚና ሱሰኛ ሆኖ ይቀራል፡፡ ከጊዜ በኋላ እረኛው በእርጅና ምክንያት ቤት ለመዋል ቢገደድም ሱሱ ግን አላስረጅ እያለ ስላስቸገረው ያንን ቅጠል ቤት አምጡልኝ አሊያም ጠዋት ጠዋት ከነአልጋዬ እየተሸከማችሁ ውሰዱኝ እያለ ቤተሰቡን ይማጸናል፡፡ ቤተሰቦቹም ተማጽኖውን በመቀበል በየቀኑ ጠዋት ጠዋት ተክሉ ወደሚገኝበት ያደርሱት ነበር፡፡ ይህንኑ ሲፈጽሙ ቤተሰቦቹ ከነአልጋው የሚሸከሙት ግን ጠዋት ጠዋት ብቻ ነበር ሲሉ አንድ በሀረር ከተማ የሚኖሩ በሳል የሃይማኖት አባት አጫውተውልኛል፡፡ የዚህም ክስተት አስገራሚነት ደግሞ ቀኑን ሙሉ ሲቅም ይውልና ከመረቀነ በኋላ ተሸክመውት የወሰዱበትን አልጋ ራሱ ያለ ማንም ረዳት ተሸክሞ መመለሱ ነው፡፡

በአንዳንድ ጥናቶች መነሻ ስማኒያ ከመቶ በላይ ወንዶች፤ ስድሳ ከመቶ በላይ ሴቶችና ከአስራዎቹ ያላነሱ ወጣቶች ጫት በሚቅሙባት የመን ከወር ገቢያቸው ከግማሽ በላይ በጫት



ወጪ እንደሚባክን በራሳቸው አንደበት ይመሰክራሉ፡፡ ከሚያወድሱት መካከል አንዳንዶቹ ደግሞ የጫትን ጥቅም ሲያጎሉ «ጫት ለኛ ውስኪያችን ስለሆነ ጉልበት ይሰጠናል፡፡ ያለ ጫት የመን ለኛ ምናችንም አይደለችም፡፡» ሲሉ አንዳንድ በጥቁር ሻሽ ፊታቸውን የሸፈኑ የመናዊያት ሴቶች ደግሞ «ጫት የገነት ተክል ነው» ብለው ያሞካሻሉ፡፡

በዚህ ሁኔታ የሚቃመው ጫት የሚያስከትላቸው የጤና ችግሮች በርካታ ናቸው ይላሉ ተመራማሪዎች፡፡ ከነዚህም መካከል: ቀበጥባጣነት፤ ቀቢጸ-ተስፈኝነት፤ ጸበኝነት፤ ራስን ወደ መግደል የሚያደርስ ድብርት፤ አካላዊ ጉስቁልና፤ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፤ የጥርስ ችግር፤ ለድንገተኛ ህመም መጋለጥ፤ የሆድና የፊንጢጣ ድርቀት፤ የመተንፈሻ ችግር፤ የአንጀት ማቃጠል፤ መደበኛ ያልሆነ የልብ ምት፤ እንቅልፍ ማጣት— ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የማመዛዘን የማስተዋልና የማገናዘብ ችሎታን ይቀንሳል፣ የስሜት መረበሽና ያለመረጋጋትን ያስከትላል፡፡ በሆነ ባልሆነ መጨነቅና ራስን መጸየፍ፣ ቀስ በቀስ የመስራት አቅም መቀነስ፣ የእንቅልፍ ጊዜ መዛባት ብሎም መፍዘዝን ያስከትላል፡፡ እነዚህ ምልክቶች ስለመኖራቸው በዐረብኛ የህክምና መዛግብቶች ከሰባተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ተጽፏል፡፡[18] የጫት ተክል ጥንት በመዲሃኒትነት ጥቅም ላይ መዋሉን በአዲስ ኪዳን መጽሀፍ ሳይጻፍ አይቀርም የሚል ጥርጣሬ ያላቸውም ነበሩ፡፡[19] ይህ ለምን እንዲህ እንደተባለ ከወደኋላ መረጃ አዘል ማብራሪያ ይኖራል ፡፡

እንግሊዛዊው አሳሽ ጸሀፊና ተርጓሚ ካፒቴን ሰር ርቻርድ በርተን «የመጀመሪያዎቹ የእግር እርምጃዎች በምስራቅ አፍሪካ» በማለት በ1856 በጻፈው መጽሀፉ ጫት ከኢትዮጵያ

ወደ የመን መግባቱን አረጋግጦአል። ርቻርድ በርተን የመጀመሪያ አውሮፓዊ አሳሽ ሆኖ ወደ ሀረር የገባው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ያልሆነ ሰው ወደ አከባቢው ቢገባ አሰቃቂ ቅጣት ወይም ሞት በሚፈረድበት ወቅት ነበር።[20] እንግሊዛዊው አሳሽ ሰር ርቻርድ በርተንም በ1855 የሀረሩን አሚር ለመጎብኘት ዳግም መጥቶ በነበረበት ወቅት ከአሚሩ ጀምሮ ጥሩ አቀባበል እንዳላደረጉለትና በዚህም የተነሳ ጉንጩ ላይ በጦር የመወጋት አደጋ ደርሶበት እንደነበረ የሚያመለክት ጠባሳ ያለበት ፎቶግራፉ በእንግሊዝ ብሄራዊ የፎቶግራፍ ጋሌሪ ውስጥ ይገኛል።



**ጫት ራስን እስከ ማጥፋት የሚያደርስ ድብርት ያስከትላል**

ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ ጫት ኢትዮጵያዊ ተክል እንደሆነ ካረጋገጡት ተመራማሪዎች አብዘኛዎቹ የዐረብ ሀገሮች ዜጎች ናቸው። አል-ብሩኒ በ973-1053 አከባቢ ጫት የቱርክስታን ተክል ነው ብሎ የበኩሉን የጻፈ ሲሆን በጥናቱ ላይ ጫት ቀይና መራራ ቅጠል ያለው ሆኖ አንጀትንና ጉበትን የሚያቀዘቅዝ ወይም ለነዚህ ህመሞች ፈውስ የሚሰጥ ተክል እንደሆነ ገልጾ ጽፏል።



አንዳንድ ምዕራባውያን ሀገሮች «ጭስ አልባ ትምባሆ» የሚሉት ጫት ፈረንሳዊውን ተዋቂ ባለቅኔና ገጣሚ አርተር ራምቦን ገና በልጅነቱ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ከተካነው የገጣሚነት ሙያው አሰገድዶ አስጥሎታል። ወደ ሀረር ከተማ ለመምጣት ዋንኛው ምክንያቱ ለምንልክ ሠራዊት የጦር መሣሪያ በሺያጭ ማቅረብ እንደነበረ የሚነገርለት አርተር ራምቦ በ19 ዓመቱ የሚወደውን ቅኔና ግጥም አቁሞና ከውጤታማ ሥራው ተደናቅፎ እንደቀረ መረጃዎች ያረጋግጣሉ። ለአብነትም ያህል አርተር ራምቦ ስለራሱ የጻፋውን የሚከተለውን አስተያየት ማየት ይቻላል፦

**«በምስራቃውያን ቅርጻ-ቅርጽ ተሰርቶ በሚማርከው እልፍኝ ቤት ውስጥ ህይወቴን ለህልፈተ-ሞት አቃርቤአለሁ። መገለጫዬም ሁሉ ወደ ጡረተኛነት ተሸጋግሯል። የገዛ ደሜን ጠጥቻለሁ። ተነሳሽነቴም ከኔ ላይ በንኗል። ከዚህ ወዲያ ስለሱ ምንም ነገር ማሰብ የለብኝም። በርግጥ መቃብር አፋፍ ላይ ነኝ።»** [21]

አርተር ራምቦ በዚሁ ምሬት ሳቢያ ወደ ሀገሩ ማርሴይ (ፈረንሳይ) በሽተኛ ሆኖ ከተመለሰ በኋላ አካሉም ሆነ አዕምሮው ተጎድቶ ስለነበረ ወዲያው ማረፉ ተመልክቷል። ራምቦ በመቀጠልም ይህንኑ በጽሁፉ እንደሚከተለው አስፍሯል፦

**«የኔ ጊዜ አልፏል፤ ህይወቴን ከጥቅም ውጭ አድርጌ፤ ጥቁር ቆዳዬንና አስፈሪ ዐይኔን ይዤ፤ተመሳስዬ ካለሁበት ወደ አውሮፓ እየተመለስኩ ነው. . .»።**

ሮተንበርግ የተባለ ድህረ-ገጽ እንዳመለከተው ጥንታውያን የዐረብ ህክምና ሊቆች ድብርትንና ስንፈተ-ወስብን ለመከላከል እንዲሁም የጨጓራ ህመምን ለማስታገስ ጫትን ከአንድ ሺህ ዓመታት በፊት ይጠቀሙ እንደነበረ አመልክቶ[24] የመናውያን ደግሞ በስድስተኛ ክ/ዘ በኢትዮጵያውያን ተሸንፈው በነበረበት

ወቅት ይቅሙ ነበር ብሏል[25]:: በሶማሌ ሳንድ ጫት በቀን አራት ጊዜ ይቃማል:: ጠዋት የሚቃመው በርጅ፤ ከምሳ በኋላ ኢጀበና፤ በአመሻሽ ቃርሲስ የማታው ደግሞ ቢዮራሲስ እየተባሉ ይጠራሉ ይላሉ አንዳንድ ምንጮች:: አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ጫትን በየቀኑ በዓለማችን ከአንድ መቶ ሚሊዮን በላይ ሰው ይቅማል ተብሎ ይገመታል:: ከነዚህም ቃሚዎች መካከል አብዘኛዎቹ በየመን፤ ሶማሊያ፤ ኬንያና ኢትዮጵያ የሚኖሩ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ በሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚገኙና ተክሉን መነገድም ሆነ መቃምን ዕለታዊ የህይወታቸው አንዱ አካል አድርገው የሚኖሩ በተለይም ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ፤ የደቡብ ምስራቅ እስያ፤ የመካከለኛ ምስራቅና ተጎራባች የአረብ ባህረ ሰላጤ ሀገሮች ተወላጆች ናቸው:: በብዙ የዓለም ሀገሮች ጫት «ህጋዊና ህጋዊ ያልሆነ ተክል » ሲሆን ህጋዊ ባይሆንም የህጋዊነትን ያህል በየመንደሩ ህብረተሰቡ በስፋት አውቆታል ፤እየተጠቀመም ነው::

ብሪየን ዊትከር የተባለ ዘጋቢ ጁን 16 2008 በእንግሊዙ ዘጋርዲያን ጋዜጣ ሲጽፍ «የመናውያን በጫት ዙሪያ ሲሽከረከሩ በለንደን ምስራቃዊ ክፍል የሚኖሩ ህዝቦች ደግሞ በንግስት ቪክቶሪያ ዙሪያ ይሽከረከራሉ» ብሎ ነበር:: ዘጋቢው በመቀጠልም በየመን ጫት ብሄራዊ ተክል የመሆኑን ያህል ለእንግሊዞችና ለሩቅ ምስራቅ ህዝቦች ሻይ፤ ለፈረንሣዮች ወይን፤ ለራሺያ ደግሞ ቮድከ ተወዳጅ ምርቶቻቸው ናቸው" ይላል::

ጫት እንደ ካናዳና አሜሪካ ባሉ ሀገሮች እንደ ኦፒየም፤ ካናቢስና ሞርፊየም የተከለከለ ባይሆንም በስውር ገበያዎች በገፍ ይቸበቸባል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሀገሮችና ተጠቃሚዎቻቸው ዘግይተው ነው ከተክሉ ጋር የተዋወቁት:: የእንግሊዙ



ዘጋርዲያን ጋዜጣ ምዕራባውያን ከጫት ጋር ዘግይተው የተዋወቁበትን ምክንያት ሲጽፍ በወቅቱ በቀላሉና በትኩሱ ወደሚፈለግበት ቦታ ለማድረስ የዘመናዊ ትራንስፖርት አገልግሎት ያለመኖር አዝጋሚ ማድረጉን ተናግሯል:: አንዱ አብነት የአውሮፓ ተመራማሪዎች በተለይም በ15ኛ ክ/ዘ የየመን ቀይ ባህር ወደብ ወደሆነችው ሞቻ በመጡበት ወቅት ቡናን ለራሳቸው አጣጥመው ወደ ሀገራቸው ይዘው ተመልሰዋል:: ጫት ግን እንደ ቡና በትኩስነቱ ወደ ሀገራቸው ስለማይደርስላቸው ይዘውት ለመሄድ አልሞከሩም::

በጫት ዙሪያ የተለያዩ መረጃዎችን የሚተነትኑ ተመራማሪዎች ሁሉ ከስርዓት በዘለለ አጠቃቀማቸው ጠንከር ያለ ትችት የሚያቀርቡባቸው ተጠቃሚዎች የመናውያን ጂቡቲያውያንና ሱማሊያውያን ናቸው:: አንድ የመናዊ ቃሚ ይህንኑ ትችት በጥንቃቄ ካስተዋለ በኋላ አውሮፓዊውን ተመራማሪ ሲተቸው፡-

«ጫት ላይ የጥላቻ አስተያየት ለመስጠት አትቸኩል፤ ይልቅስ ቡና ከመጠጣትህ በፊት ከኛ ጋር ተቀላቀል ...» ብሎት ነበር::

የመናውያን ጫት ጉልበት እንደሚሰጣቸው፤ አስተሳሰባቸውን እንደሚያሰባስብ፤ የወሲብ ስንፈትን እንደሚያሻሽል፤ማህበራዊ ህይወትን እንደሚያደምቅ፤ ዕለታዊና ወቅታዊ መረጃዎችን መለዋወጥ የሚያስችሉ ውይይቶችን ማካሄድ እንደሚያስችል፤ ሱስ አማጭነቱ ከሌሎች ሀገሮች ዕጾች ጋር ሲታይ በእጅጉ እንደሚለይ ይገልጻሉ:: ከዚህ የተለየ አቋም ያላቸው ደግሞ በህብረተሰቡ ላይ እየደረሰ ያለውን ማህበራዊ ቀውስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ጠንከር ያለ ትችት ይሰነዝራሉ:: ከነዚህም አንዱ የሆኑት የየመን ጤና ጥበቃ ሚኒስትር የነበሩት በአንድ ወቅት የዓለም ባንክና የአውሮፓ ተጠሪዎችን በተክሉ ዙሪያ መሠረታዊ ጥናት እንዲደረግ ተማጽነው ነበር ይባላል::

አንድ ሳናዓ ከተማ የነበረ ጋዜጠኛ «የካናቢስ ዜና» በሚል ርዕስ ሴፕተምበር 19 1999 ስለ ፕሬዚደንት አሊ አብዱላሂ ሳላህ የሚከተለውን ጽፎ ነበር፡-

**ጽሁፉም « ለረጅም ዓመታት የጫት ሱሰኛ የነበሩት አብዱላሂ ሳላህ በአንዳንድ የጫት መቃሚያ ስነስርዓቶች ላይ ባልተጠበቀሁኔታ የማህበራዊ ህይወት ጠንቅ ስለሆነ ከዚህ ጠንቅ ህብረተሰቡ ተጠብቆ ራሱን ምርታማ እንዲያደርግ ተማጽኖ አቅርበዋል።»** ይላል

በወቅቱ የ57 ዓመት ጎልማሳ የነበሩት ፕሬዚደንት አብዱላህ ሳላህ ህዝቡን ሲመክሩ ጫት ለመቃም የሚውሰውን ጊዜ ለትምህርትና ለስፖርት እንዲያውሉ ጠይቀዋልም ብሏል። ሌሎች የሀገር ውስጥ ጋዜጦችም ፕሬዚደንቱ ቀደም ሲል ለጫት ያውሉት የነበረውን ጊዜ ብስክሌት በመጋለብና በኮምፒውተር ሲጽፉ በፎቶግራፍ አስደግፈው አውጥተው ነበር። የእስላህ ፓርቲ መሪና የም/ቤቱ አፈጉባኤ የነበሩት ሼክ አብዱላህ የተባሉ የሃይማኖት አባት በወቅቱ ፕሬዚደንቱንና ተግባራቸውን ሲተቹ፡-

**«የማይፈጽሙትን ነገር ይሰብካሉ፤ ከነዚህ ጣፋጭ ቃላቶች ጀርባ ሆነው ራሳቸው እስካሁን ይቅማሉ»** ብለው ነበር።

አፈጉባኤው ጫት የየመናውያን ህይወት አስለቃሽና ችግር ፈጣሪ ሱስ በመሆኑም ይስማማሉ። ማህበራዊ ችግር እያስከተለ ስለመሆኑም ሽፋፍነው ማለፍ አልተዋጠላቸውም።

ጋዜጠኛው መጨረሻ ላይ የተደረሰበትን ውሳኔ ባይገልጽም ጠቅላይ ሚኒስትር ሞስን-አሊ አይኒ በ1972 ተጀምሮ በነበረው ጸረ-ጫት ዘመቻ በህዝባዊ መድረኮች ሰፊ ቅስቀሳ ማካሄዳቸውንና በተለይም የመንግስት ሰራተኞች በስራ ሰዓት እንዳይቅሙ፤ በሀገሪቱ የሚገኙ የእምነት ተቋማት ሁሉ ይህንኑ



ደንብ እንዲያከብሩና እንዲያስከብሩ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ የግብርና ልማት ሰራተኞች እንዳይቅሙ መነሻ ሃሳብ በማቅረባቸው በዚሁ ባመነጩት አዲስና አወዛጋቢ ሃሳብ ሶስት ወር ባልሞላ ጊዜ ስልጣናቸውን በጉልበት ተነጥቀዋል። ፕሬዚደንቱ ተማጽኖውን ያቀረቡት ከ21 ዓመት የስልጣን ቆይታ በኋላ እንደገና ለፕሬዚደንትነት የሚወዳደሩበት ወቅት ስለነበረ ከላይ የተጠቀሰው ጋዜጠኛ ፕሬዚደንቱን ሲተች «የአንድ ተራ ጫት ቃሚን ያህል እንኳን የማሳመን አቅም የላቸውም፤ በጣም የወረደ ተቀባይነት አላቸው» ሲል ተችቷል።

አለክስ ክሌይን የተባለ ተመራማሪ በየመንና ኢትዮጵያ ቆይታው የታዘበዉንና ያየውን ሲያብራራ "ጫት በሚቃምበት ጊዜ በሮችና መስኮቶች ይዘጋሉ። የዚህም ምክንያቱ ምርቃና በቀነሱ እንዲይዛቸው ተብሎ ነው። በነዚህ ቤቶች የሲጃራ ጭስ ጣሪያ ላይ ደመና ሰርቶ ይንሳፈፋል። ገራባው በየሜዳው ይጣላል። ጫቱ የሚቃመው ሳይታጠብ ነው። ሻይና ውሃ በቅብብሎሽ ንጽህናቸው ባልተጠበቁ ዕቃዎች ይጠጣሉ። ተላላፊ በሽታዎችን ማዛመት የሚያስችሉ መንገዶች ብዙ ናቸው" ብሏል።

ቻርለስ ሙዳድ አውሮፓዊ ደራሲ ነው። ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ «የመቃም ጦርነት» በሚል ርዕስ አንድ ዘገባ አውጥቶ ነበር። ደራሲው ዘገባውን ያቀረበው ቃሚ ከሆነው ሾፌሩ ጋር ያደረገውን ተውኔታዊ ቃለ ምልልሳዊ ውይይት መነሻ አድርጎ ነው። ከዚሁ ጽሁፍ የተወሰደው በጥቂቱ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል:-

ሾፌር፡- ሃይማኖትህ ምንድን ነው?
ቻርለስ፡- ሜቶድስት ( የክርስትና ሃይማኖት አንዱ ዘርፍ)
ሾፌር፡- እኛ ሙስሊሞች እኮ በኢየሱስ እናምናለን፤ ይህንን ታውቃለህ?

ቻርለስ፡- አዎን ግንዛቤ አለኝ

ሾፌር፡- ስለዚህ ማድረግ ያለብህ የመጨረሻ መሣሪህ በሆነው አላህና በእስልምና ሃይማኖት ማመን ነው።

ቻርለስ፡- የውይይቱን አቅጣጫ ለማስቀየር ሲል ሾፌሩን ስለ ጫት ጠየቀው፤

ሾፌር፡- ጫት፣ ጫት መጥፎ ነው፤ ላንተ አያስፈልግህም

ቻርለስ፡- ለምን?

ሾፌር፡- ሀሴት ይፈጥርብሃል፤ የማይጨበጥ ተስፋ ውስጥ ያስገባሃል!

ቻርለስ፡- ታዲያ ሀሴት በኔ ላይ መፈጠሩ ምን ችግር አለበት?

ሾፌር፡- ላንተ አላህን ማመን ብቻ ይበቃሃል፤ ዕጽ አያስፈልግህም። አላህ ከጫት ይልቅ የምትፈልገውን ደስታ ይሰጥሃል።

በመጨረሻም ቻርለስ ሾፌሩ ጫቱን ላለማስነካት የሚያደርገው ጥረት መሆኑ ስለገባው ውይይቱን አቋርጦአል።

እንደ አልኮል መጠጥ ቁራን ውስጥ ጫት የተከለከለ ወይም የተፈቀደ ስለመሆኑ የተጠቀሰ ነገር ባለመኖሩ ጫትን የሚያበቅሉ ሀገሮች በፍላጎትና በምርጫ ይቅማሉ። የየሀገሮቹ የውጭ ምንዛሪ የጀርባ አጥንት እስከ መሆንም ደርሷል። በአንዳንድ አጥኚዎች መረጃ መሠረት ወጣቱ እንዳይቅም ጠበቅ ያለ ህግ ለማውጣት የውጭ ምንዛሪው ተጽዕኖ አድርጓል። እንዲወጣ የተደረጉ ሙከራዎችም ከሙከራ አልፈው ወደ ተግባር የገቡ ስለመሆናቸው ተጨባጭ መረጃ የለም።





*የሐራራ ሰዓት የጫት ገበያ (ፎቶ ከድህረ-ገጽ.)*

ህብረተሰቡ ይቅማል፤ ይነግዳል፤ለምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ይጠቀማል (studies of elmi 1983; Al-hebeshi & skaug, 2005,Gebissa, 2004; Armstrong,2008:638)። ከስነልቦና፤ከጤንነትና ከቤተሰባዊ ጉዳዮች ጋር የሚያይዙም አሉ። (Karunamoorthi et.al 2010:112)። ላኪዎች፤ ቀንጣሾች፤ አርሶ አደሮች፤ ጫኚዎች፤ አውራጆች፤ ቸርቻሪዎች ሁሉ ይብዛም ይነስ የጥቅሙ ተጋሪዎች ናቸው። በየዓመቱ ከሙቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ታገኛለች ከምትባለዋ ሀገራችን ኢትዮጵያ ጀምሮ በሌሎችም ሀገሮች ጫትን እንዳይቅሙ የሚያበረታቱ ቀጥተኛ ያልሆኑ ተግሳጾች ቢኖሩም «አዛውንቶችና በተለይም ደግሞ ወጣቶች» በተለያዩ ምክንያቶች ከማዘውተር አልተቆጠቡም። በአብዘኛዎቹ አከባቢዎችና ከብዙዎቹ የህብረተሰብ ክፍሎች ሙስሊሞች ዋንኞቹ ተጠቃሚዎች ናቸው (Armstrong, 2008: 638)። በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ለጸሎት ብርታት ይሰጣል ተብሎ

ስለሚታመን ቢቃምም ከሙሲሊሙ የበለጠ ክርስቲያኑ በሱሱ ዘልቆ የገባበት ሁኔታም በስፋት ይስተዋላል:: አንዱ ለጸሎት ሌላኛው ደግሞ ለመዝናኛ እያለ፤ እያለ፤ እያለ .....ቀጥሏል:: መነሻው እንጂ መድረሻው አይታይም:: ጫት ድርቅን የሚቋቋምና ከሌሎች ተክሎች በተለየ ሁኔታ ዓመቱን በሙሉ የሚመረት መሆኑ በአምራች አርሶ አደሮች ዘንድ በባህላዊ መንገድ ከሚመረቱ ሰብሎች ሁሉ የበለጠ ተፈላጊ አድርጎታል::

ጫት በግለሰባዊና ማህበራዊ ኑሮ፤ በመንፈሳዊ ህይወት፤ በወርሃዊ ገቢ፤ በጊዜ አጠቃቀም፤ በጤንነት አያያዝ፤ በቤተሰባዊ አኗኗር ... ምን ትርጉም አለው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ አቀራረቦች ሊኖራቸው እንደሚችል ይገመታል:: ኬቭን ፌዳርኮ በትንሽዋ ጎረቤታችን ሀገር ጂቡቲ ጉብኝት አድርጎ በነበረበት ወቅት «በሲኦል ጫፍ ላይ» የሚል ሰፋ ያለ ዘገባ አስነብቦ ነበርና ይህንኑ ማጋራቱ ይጠቅማል:: ኬቭን ጂቡቲያውያን ከጫት ጋር ያላቸው ህይወት ምን እንደሚመስል ገና ከጅምሩ የአንባቢዎችን ቀልብ በሚከተለው ሁኔታ እያማለለ ያስነብባል:-

**«ይህ የጉዞ ታሪክ ነው:: ይህ የዕጽ ታሪክ ነው:: ይህ በዕጽ በነደደ ስሜት የተጻፈና በጫት ቅጠል መቃም ላይ ያነጣጠረ፤ በምድራችን የመጨረሻ መጥፎ ስፍራ ዙሪያ የተጻፈ የጉዞ ታሪክ ነው:: ለማንበብ ተዘጋጅተዋል? እንግዲያው እንሂድ»** ይላል::

ኬቭን በትንሽዋ የጎረቤታችን ምድር ጂቡቲ የጫትን እውነታዊ ትረካ ለመጻፍ ወደዚያ ከመድረሱ በፊት ከቀይ ባህር ጀምሮ የኢትዮጵያን ደጋማ ስፍራዎችና በጣም ዝቅተኛውን ስፍራ ዳሎልን በዲሲ-8 አይሮፕላን ማየቱን ያስነብባል:: ጸሀፊው በጉብኝቱ ወቅት የደንከል በረሃ ሙቀት ወደ 120⁰ ሴልሼስ እንደሚደርስ ይተርካል:: እንግሊዛዊው አሳሽ ኔስቢት ይህንኑ



የመጀመሪያውን ውጤታማ ጉዞ ወደ ደንከል በረሃ አድርጎ በነበረበት እ.አ.አ በ1927 «የተፈጥሮ የገሃነም ጉድጓድ» ብሎ የክርስትና ስም አውጥቶ ነበርም ይላል ኬቭን::

በወቅቱ ጉዞውን ወደ ጂቡቲ ለማድረግ መነሻውን አዋራማ የድሬዳዋ አይሮፕላን ማረፊያ ያደረገውን ጢያራ ውስጣዊ ክፍል ወደ ኋላ ዞር ብሎ ሲያይ ትራስ የሚያካክሉና በነጭ ጨርቅ የተጠቀለሉ ክምሮች ይታያሉ:: ጂቡቲ እንደደረሰም ነጠላ ጫማ ያደረጉና ሸርጥ የለበሱ ሰዎች አይሮፕላኑን በከፍተኛ ጉጉት ይጠባበቃሉ:: አይሮፕላኑ ካረፈ በኋላ ሰዎቹ እየከበቡ መምጣታቸው ለህይወቱ ድንጋጤ ይፈጥርበታል:: ሰዎቹ በርግጥ የሰከሩ ቢመስሉም ደግነቱ ደግሞ ያልታጠቁ መሆናቸው ደግሞ ደስተኛ ያደርገዋል:: ከሁሉም በላይ ጫቱን ከአይሮፕላን ለማራገፍ ተሰልፎ ይጠብቅ የነበረው ወያላና የመኪኖች ፍጥነት አግራሞትን ፈጥሮበታል:: «የተለመደውን ስጠን» ከሚሉ ወፋፌዎች ጀምሮ እያንዳንዱን ክስተት በዐይኑ የሚከታተለውና በጆሮው የሚሰማው ኬቭን:-

**« . . . ከመጠን በላይ ማሪዋና ካጨስክና ከመጠን በላይ አልኮል ከጠጣህ አዕምሮህን ትስታለህ:: ነገር ግን ጫትን ያለ ምንም ማቋረጥ ለ24 ሰዓታት እንኳን ብትቅም አዕምሮህ እየታደሰ ይሄዳል:: ይህ ቅጠል ጉልበት ይሰጥሃል:: እሱን መቃም ስትጀምር የድካምህ ስሜት ጨርሶ ይጠፋል:: ያዝናናልም:: እንደኔ እንደኔ ጫትን በአደንዛዥ ዕጽ ምድብ አላካትትም:: ከነዚህ ሁሉ የተለየ ነው:: አንድ የተለየ የምለው ነገር ቢኖር እሱን መቃም ስጀምር ችግሬ ሁሉ እንደተወገደ አድርጌ ነው የማስበው:: ጫት ወንድሜ ነው:: ከሁሉም ነገር ይጠብቀሃል::»**

ይህ ጥቅስ እዛው ጉብኝት ላይ እያለ አንድ የጫት ተጠቃሚ የሰጠው አስተያየት መሆኑን ኬቭን ገልጾአል::

ኬብን በዚሁ ጽሁፉ መነሻውን ኢትዮጵያ አድርጎ ኬንያና የመን ይበቅል የነበረው ጫት ከሺህ ዓመታት በፊት በምስራቅ አፍሪካና በመካከለኛ ምስራቅ በሙስሊም እምነት ተከታዮች ዘንድ አልኮል በቅዱስ ቁርአን በመከልከሉ የሱ ምትክ ተደርጎ እንደሚወሰድ መገንዘቡን ጽፏል። ጓደኛ ለጓደኛ እየተፈላለጉና ቡድን እየመሰረቱ እስከ ምሽቱ ስድስት ሰዓት ጉንጫቸውን በማሳበጥ እየቃሙ ይቀመጣሉ ይላል። ኬብን አንዳንድ ተመራማሪዎች ጫት ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለመገኘቱም የነበራቸውን ጥርጣሬ ውድቅ በማድረግ መገኛው ኢትዮጵያ መሆኑን በተደጋጋሚ ካረጋገጡ ጸሀፊዎች አንዱ ነው። ከዚህም በላይ የመን ከጠቅላላ የእርሻ መሬትዋ ሁለት ሶስተኛው በጫት ተክል መያዙን ጽፏል። በኬንያ ከሌላው ህብረተሰብ በተጨማሪ ተዋቂ አትሌቶች ሳይቀሩ ለመነቃቃት ይጠቀማሉ ይላል። በመቀጠልም በጫት አብቃይ ሀገሮች «ከኔ ብጤ» ጀምሮ እስከ ርዕሳነ ብሄሮች ሳይቀሩ የጫት ተጠቃሚዎች መሆናቸውን አረጋግጦ ለጂቡቲያውያን ግን ለዘመናት ስር የሰደደውን ስቃይ «ማስታገሻቸው ነው» ብሏል።

ኬብን በጫት ዙሪያ ያሰፈረው ጽሁፍ ረጅም በመሆኑ ሁሉንም ማቅረብ ባይቻልም አለፍ አለፍ እያልን ስንቃኝ ከቃሚዎችና ሻጮች ጋር የሚያደርገው ጣፋጭ ጭውውት እንደቀጠለ ነው። የሁሉንም ይሰማል፤ ሁሉንም በጥንቃቄ ያዳምጣል። ያያል። ያምናል፣ይጠራጠራል። ቀጠለ----

በደቡብ አሜሪካ የሚወሰደውን ኮኬይን ታውቃለህ?

አዎን -አለ ኬብን።

እኛ ጫትን የምንቅመው በኮኬይን ምትክ ነው። ስለሆነም እንቅማለን።



አንተ ለመሆኑ እዚህ ለምን መጣህ?

«እኛ ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ ነው ያለነው። አንድ የመናዊ ቢያንስ ቢያንስ ከወርሃዊ ገቢው አንድ አምስተኛውን ለጫት ያውላል"።



በፍልስፍና ባህር ውስጥ ሰጥመው የሚታዩ የመካከለኛ ምስራቅ ጫት ቃሚዎች
(ፎቶ ከድረ-ገጽ)

«ባይገርምህ ጫት እንዲያውም የወንድን ብልት ያሳንሳል፤ በራሱ ጊዜ እንዲቆምም አያደርግም። ባለቤቶቻችን በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት እርካታ የላቸውም። ይህ የጂቡቲያውያን ሴቶች ትልቁ ማህበራዊ ችግር ነው። ጫት ለጂቡቲያውያን ወንዶች ሁለተኛ ሚስታቸው ሆኗል። ስለዚህ ሴቶች የግድ ለተፈጥሮአዊ ስሜታቸው ማርኪያ ሲሉ ቁሪስቶችን ያሳድዳሉ»።

ኬብን ጂቡቲ በነበረበት ወቅት ባደረገው ጥናት ጫት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው በኢትዮጵያ በተለይም ጀጎል ግንብ በታጠረችው ሀረር ከተማ አቅራቢያ ፍየል ቅጠሉን በልታ ኖሮ ባልተለመደ ሁኔታ የባህርይ ለውጥ ከሳየችበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑንና ከዚያም መቃም መጀመሩን እንደሰማ አብራርቷል።

መረጃዎቹን ፍለጋ መኪና ተከራይቶ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የጫት መኪናዎች ለራሳቸው ገበያ ቅድሚያ በመስጠት፤ ህጋዊ መስመር ባለመከተልና መንገድ በመዝጋት ያስቸግሩት እንደነበረም በጽሁፉ ገልጾአል፡፡

የጂቡቲያውያንን የጫት መቃም ስነ ስርዓት ከጃፓናውያን የሻይ ስነ ስርዓት ጋር የሚያመሳስለው ኬብን «ካልቃምን ዱካክ (የሌሊት ቅዠት) እረፍት ያሳጣናል»፡፡ የሚሉ የጫት አምላኪዎች እንዲሁም ኡረታ የተባለውንና ከኢትዮጵያ የሚሄድላቸውን የአወዳይ ጫት በማወደስ «ቅጠላ ቅጠል ብቻ ሳይሆን ፍራፍሬ ነው » የሚሉ ቃሚዎችም አጋጥመውታል፡፡

ከቡድኑ ጋር ውይይቱ ቀጥሎ እንዳለ አንድ ድንገተኛ ጥያቄ አቀረበላቸው፡፡ ለቡድኑ ያቀረበው ጥያቄ የአከባቢውን የአነጋገር ባህል የጣሰ ይሆን በሚል ስጋት ላይም ወደቀ፡፡ ከተሳታፊዎቹ መካከል ቃድር ተርጉሞ እንዲነግራቸው ትብብር በመጠየቅ «ጫት የወንድን ብልት ያኮማትራል ይባላል፤ እውነት ነው?» አላቸው፡፡

ቃሚዎቹም በአንድ ጊዜ በአራትና በአምስት ቋንቋዎች የየራሳቸውን አስተያየት መስጠት ጀመሩ፡፡ ፈረንሣይኛ፤ ሶማሊኛ፤ አፋርኛ፤ ዐረብኛ .... ብቻ ሁሉም በአዎንታዊ መልክ ጭንቅላታቸውን ሲያወዛውዙ አየ፡፡ አንዱ ሌላውን እንዴት እንደሚያስታውልም በጥሞና ተመለከተ፡፡ ከመካከላቸው ጉንጩን በአረንጓዴ ጭማቂ የሞላው አወል የተባለው የፖሊስ ባልደረባ ብድግ ብሎ ቆመ፡፡ «ጫት ስሜትን የሚያነቃቃ ተክል ነው» ፊቱን ወደ ኬብን አዙሮ በማየት «ስሜትን ማነቃቃት ማለት ምን እንደሆነ አታውቅም? ይህ ማለት ጫትን ከቃምክ በኋላ የሴቶችን ስሜት የሚያረካ ሥራ ትሰራለህ» ቂጡን ጫን፤ ገልበጥ መታ እያደረገ በማሳየት «እንዲያውም እሱን በቃምኩ እለት ሌሊቱን በሙሉ አዝናናለሁ፡፡ ማቆም የለም፡»



ኦማርና ጓደኞቹ እየተቀባበሉ፡
« አዎን፤ አዎን፤ አዎን »
አቦ እናትህን …… «ባለጌ»
«እውነቱን ነው» ይባባላሉ እርስ በርስ፡፡
በመጨረሻም ውስጣዊ ስሜቶቻቸውን የሚኮረኩሩ መግባባቶችን መነሻ ያደረጉ የሃሳብ ልውውጦችን ከኬብን ጋር መጋራት ጀመሩ፡፡
«ጫት ስትቅም ዘና ትላለህ፡፡» ላድር የተባለ የወደብ ሰራተኛ ነበር፡፡

**«— ስራ በሌለህ ጊዜ ጫት ስትቅም ሰላም ታገኛለህ፡፡ እነሆ እንደሚታየን ከጓደኞቻችን ጋር በሰላማዊ ሰፍራ እንገኛለን፡፡ ለምንም አናስብም፤ አንጨነቅምም፡፡ ይህ ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? ምክንያቱም ከጫት ጋር ሁሉም ነገር ይሳካል፤ ይቻላል፡፡ ከጫት ጋር ሰዎች ውጊያ እንኳን ያቆማሉ፤ ከጫት ጋር ሁልጊዜ የሚኖረው ሰላም ብቻ ነው፡፡»**

በዚህ ሁኔታ ሲወያዩ ከቆዩ በኋላ በመካከላቸው ከረር ያለ ያለመግባባት ተፈጠረ፡፡ ለድብድብ መገባበዝም ተጀመረ፡፡ ማን የት መቀመጥ አለበት በሚል በምርቃና ምጥቀት በተነሣው ጸብ አወል (ፖሊሱ) ልብሱን አውልቆ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት ጀመረ፡፡ ደቂቃዎችን በፈጀ ግልግል ሁለቱንም አስታረቋቸው፡፡ ቃድር ደስተኛ ባልሆነና በጭቅጭቁ ስሜቱ የተጎዳ በሚመስለው ፊቱ ወደ ኬብን ዞሮ፡-

**«እጅግ በጣም ብዙ ገንዘብ እናጠፋበታለን፡፡ አንሠራም፡፡ ለልጆቻችን ጫማ እንኳን አንገዛላቸውም፡፡ፍቺ፤ የቤት ውስጥ ጭቅጭቅ፤ … እጅግ በጣም ብዙ ችግሮች»** አለ፡፡ ዐይኑ በምርቃና ተጎልጉሎ ሲወጣ የተቃረበ በሚመስል አንደበቱ፡-

**«ይህም ሆኖ ግን እንቅማለን፤ ከዚህ በላይ ምን ሊባል ነው? ኑሮአችን ይህንን ይመስላል»** በማለት ፊቱን አልቃሽ ህጻን አስመስሎ ተናዘዘ::
ዑመር በተራው በመነሣት:-
**«ጓደኛዬ! ጫት ለኛ ሁሉም ነገር እንደሆነ ተረዳህ?»** አለው:: ከጫት ጋር ብዙ ውሃ በመጠጣት የተዘረጠጠውን ቦርጩን በአንድ እጁ እያሻሸ:-
**« ለኛ ዋናው ነገር አንድ ላይ መሰባሰባችን ነው፤ ለመወያየት፤ ለመሳቅ፤ ለመረዳዳት:: ይህ ባይሆን ኖሮ የኛ ማህበረሰብ አይኖርም፤ጫት ለኛ ሁሉም ነገር ነው:: አይደለም?»** አለው:: ኬቨን በጥናታዊ ጽሁፉ አንባቢዎቹን በረጅም ርቀት ልብ እያንጠለጠለ የጀመረውን ትረካ በሚከተለው ሁኔታ ያጠቃልላል:-
***«ወደ ቤቴ ስመለስ በእርግጠኝነት ይህንን ሥፍራ ጠላሁት:: ጫት ጂቡቲያውያንን በማዝናናት ፋንታ ወደማይወጡት አዘቅት እየከተታቸው ነው ... :: ሊደረስላቸው የሚገቡ ህዝቦች መሆናቸውን ለጓደኞቼ እገልጽላቸዋለሁ:: እጅግ አሳፋሪና አስቀያሚ ገጠመኝ ነው:: በህይወቴ ሁለተኛ የማልመለስበትና መሄድ ያልነበረብኝ ምድር ነው::»***

ኬቨን ሩሽብ የሙሉ ጊዜ ደራሲና ፎቶግራፈር ከመሆኑ በፊት በሱዳን በማሌኻርያና የመን የእንግሊዝኛ መምህር ነበር:: የመረጃ ሰው እንደሆነ ገልጸው የጻፉም አሉ::[26] **«ሶማሊያ በእርስ በርስ ጦርነት ላይ በነበረችበት ወቅት በአይሮፕላን ማረፊያዋ በክብር የሚያርፈው ብቸኛው የክብር እንግዳ ጫት ብቻ ነበር:: ይህም እንግዳ ከኢትዮጵያ በአይሮፕላን የሚመጣ ጫት ነበር:: ጫቱ ሶማሊያ ሲደርስ ከተቀባይነቱ አንጻር የሚቀረው ነገር የክብር ዘብ ሰላምታ ብቻ ነው» ::ብሏል**



ሰን ሚክላቪች እንዳለው ጫት የጫነው አይሮፕላን ሰማይ ላይ በሚያንዣብብበት ጊዜ



*ጫት ሞቃዲሾ አይሮፕላን ማረፊያ ላይ የክብር አቀባበል ሲደረግለት*

አፍላ ውጊያ ላይ የነበሩ የጦር አበጋዞች ሳይቀሩ የተኩስ ማቆም ስምምነት ላይ ይደርሳሉ:: እንደ ሌሎቹ ሁሉ እነርሱም በጋራ የሚናገሩት ቋንቋ ቢኖር ጫት በቅዱስ ቁርዓን የተፈቀደ ባይሆንም የተከለከለ ያለመሆኑን ነው::

እንደ ኢትዮጵያው አወዳይ ሁሉ በኬንያም ምርጥ የሚባል ጫት የሚበቅልባቸው አከባቢዎች ተለይተው ይታወቃሉ:: ጫት በዋንኛነት በኬንያ በሶስት ዋና ዋና አከባቢዎች ይበቅላል:: እነርሱም በስምጥ ሸለቆ የሚትገኘው የኬሪዮ ግዛት፤ እምቡ፤ እንዲሁም ኒያምቤኒ በመባል ይታወቃሉ:: ከነዚህም ከሶስቱ ደግሞ የኒያምቤኒ ግዛት ምርጥ ጫት አብቃይ ግዛት ነው:: በኬንያ ኒያምቤኒ ተራራማ አከባቢዎች የሚኖሩ ነዋሪዎች ጥንት የመቃም ባህል ሲጀምሩ የሚቅሙት በዕድሜ የገፉ አዛውንቶች ብቻ ሲሆኑ ያውም በሠርግ ስነስርዓት ወቅት ብቻ ነበር:: ዛሬ ግን የአብዘኛው ነዋሪ መጠቀሚያና በሁሉም ሥፍራ የሚገኝ ሱስ አማጭ ተክል ሆኗል::

አንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ከዓመታት በፊት በሶማሌላንድ፤ ፑንትላንድ፤ ጂቡቲና በኢትዮጵያ ኦጋዴን አከባቢዎች ጥናት አድርጎ በነበረበት ወቅት በነዚህ አከባቢዎች ጫት ለመቃም ብቻ በዓመት ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደሚጠፋ ድምዳሜ ላይ ደርሷል። ከ1333 በፊት ጀምሮ የዐረብ ሀገሮች ለተለያዩ በሽታዎች ፈውስነት ይጠቀሙ ነበር የሚባለው ጫት ዛሬ ዛሬ እንደ ሶማሌ፣ የመን ጂቡቲ ባሉና በሌሎችም መቃም በጣም በሚዘወተርባቸው ሀገሮች ጉዳቱም የዚያኑ ያህል ነው። ለዚህም አብነት አንድ ሶማሊያዊ ነጋዴና የአንድ መስግድ ሃላፊ ቃሚዎችን ሲተቹ የተናገሩትን እንመልከት፡- **«ይህ ተክል ሀገሬን ወደ ቁልቁል እያወረዳት ነው»** ሲል ነጋዴው ኢማም ሳሊም የተባሉ በሶማሌ የአንድ መስጊድ ሃላፊ በበኩላቸው ለቢቢሲ ጋዜጠኛ በሰጡት አስተያየት **«ሚስቶች ባሎቻቸው ሌሊቱን በሙሉ በጫት ተጠምደው ስለሚያድሩ ለግብረ ስጋ ግንኙነት፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ለህክምናና ለልጆች ትምህርት ቤት ክፍያና ለምግብ ወጪ (ማሸሩፍ) ተቸግረዋል።»** ብለዋል

ጫት ከኢትዮጵያ በማይታወቅና አስገራሚ በሆነ ሃይል ወደ ሀገራቸው እንደገባ የመናውያን ያምናሉ። አብደላ አልሱጃ የተባለ የሳናዓ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስ ፕሮፌሰርና «ጫት- አልባ ማህበር» ሊቀመንበር ለዜጎቻቸው በአንድ ወቅት ሲናገሩ፡-



**«ለሰዓታት ለችግሮቻችሁ መፍትሄ መስጠት የሚያስችል ውይይት ብታካሂዱም ውጤታማ አይደላችሁም፤ ችግራችሁ የባሰ የከፋ እየሆነ ነው። ውሳኔዎቻችሁም የከፉ እንጂ የተሻሉ አይደሉም። ይህም የሆነበት ምክንያት ጫት እየቃማችሁ ለችግሮቻችሁ መፍትሄ ስለምትፈልጉ ነው»** ብለው ነበር።



*እንዲህ የራስን ደህንነት እየጠበቁ መቃምና መሸጥም አለ።*

*(ፎቶ ከድህረ-ገጽ)*

በአንዳንድ የአውሮፓ ጸሀፊዎች ምልከታ ጫት እንደ የመን፤ ጂቡቲና ሶማሊያ ላሉ ሀገሮች አሁንም ሆነ ወደፊት የህዝቡን ማህበራዊ ህይወት የሚያቃውስ ስለመሆኑ የየሀገራቱ መንግስታት እርግጠኞች ሆነዋል። በተለይም ለየመን ህዝብ በጣም የከፋ የሚሆነው ውሃን ከመጠን በላይ እያባከነ መሆኑ ነው። በዚያ አለታማ መሬት ላይ ለጫት እርሻ ሲባል በመስኖ የሚለቀቀው ውሃ መጠን ከጨዋማነት ተለይቶ ለመጠጥ ከዋለው ውሃ 30 ከመቶ በላይ ይሆናል ተብሎ ይገመታል። በየመን ሀገር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሰባ አምስት ከመቶ

የመስኖ ልማት ሥራ ለጫት ብቻ የተወሰነ ነው የሚሉ ውስጥ ዐዋቂዎችም አጋጥመውኛል:: አንድሪው ኤል ባተርስ «የመን ራስዋን ወደ ሞት እየቆረጠመች ነው» ባለው ጥናታዊ ጽሁፉ በአፍሪካ ቀንድና በዐረብ ባህረ ሰላጤ ያሉ አብዘኞዎቹ ሀገሮች ጫትን በተወዳጅ ሱስነት እንደሚቅሙ አብራርቶ የየመን ግን «መፍትሄ የሌለው ብሄራዊ ሱሰኝነት ነው» ብሏል::

የጫት ሱስ ሰለባ ሆነው መላቀቅ ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች አንድ ተመራማሪ የሚከተሉ ተግሳጾችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይመክራሉ::

- መቃሚያ ቀናትን ቀስ በቀስ መቀነስ
- በሚቃምበት ጊዜ እንደ ኮካኮላና ሻይ የመሳሰሉ ጣፋጭና አንቂ ነገሮችን መቀነስ፤ በምትኩ ንጹህ ውሃና ወተት መጠቀም
- እየቃሙ ማጨስን ማስወገድ፤ ተሸንፈው የሚያጨሱ ከሆነ ደግሞ በርና መስኮት ለንጹህ አየር መግቢያነት መክፈት
- ከመቃም በፊትም ሆነ በኋላ ተመጣጣኝ ምግብ መውሰድ፤ የእንቅልፍ ሰዓትን ለጫት ያለማዋል
- ከጫት በኋላ አፍንና ጥርስን ሁልጊዜ ማጽዳት
- ከጫት በፊትም ሆነ በኋላ ሌሎች ዕጾችን መደረብና አልኮል/ጨብሲ መጠቀም ዘግይቶም ቢሆን አደጋ ማስከተሉ አይቀሬ መሆኑን በትክክል መገንዘብ
- በሀኪም ካልታዘዙ በስተቀር የእንቅልፍ ኪኒን ያለመውሰድ
- በየቀኑ ቢያንስ የ30 ደቂቃ ስፖርት መስራት
- ጫትን እያኘኩ አፍ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ማቆየት ጥርስን ያበሰብሳልና ትንቃቄ ማድረግ
- በእርግዝና ወቅት መቃምን ጨርሶ ማቆም፤ ይህ ካልሆነ ከድብርት እስከ አፍና ጎሮሮ ካንሰር ድረስ የሚዘልቅ ችግር ያስከትላል:: የሚሉ ናቸው::



በአንድ ወቅት አንድ የአሜሪካ ዲፕሎማት በየመን ቴሌቭዥርን ቀርቦ ለዲቪ ሎተሪ አሸናፊዎች ጫት ቃሚዎች ከሆኑ ቪዛ እንደማይሰጣቸው ማብራሪያ በመስጠቱ ትልቅ ተቃውሞ ገጥሞት እንደነበረ አለን ብላክ የተባለ ጸሃፊ ገልጾአል:: በትላልቅ የሀገራችን ከተሞች መዳረሻዎች ወይም ወጣ ብሎ ግራና ቀኝ፤ በየዛፉ ጥላ ስር ጫት መቃም ዘመናዊ ባህል እየሆነ ነው:: ከዝቅተኛ እስከ ቅንጦት መኪኖች እየያዙ መምጣት፣ ፍራሽ አንጥፎና ትራስ ተደግፎ እየቃሙ መዋል፤ እዛው ገላጣ ሜዳ ላይ ቡና ማፍላት ወይም ማስፈላትም . . . እየተዘወተረ መጥቷል:: ያልተለመደና መጤ ባህልም እየሆነ ነው:: ለዚህም ሌሎች አከባቢዎች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው ባይሆኑም የጫት ጉዳይ ሲነሳ ሀረርጌን ጨምሮ ተጎራባች የምስራቁ ሀገራችን ክፍሎች ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ሆነዋል:: የመሀል ሀገሮችም ወደ ውድድሩ ሜዳ በፍጥነት መግባታቸውን ሳንዘነጋ ማለት ነው:: ወደ ጂቡቲ፤ የመን፤ ሶማሌ፤ እንግሊዝ፤ ሆላንድ፤ አሜሪካ፤ ከናዳ፤ አውስትራሊያ፤ አውሮፓና ሌሎችም ሀገሮች ዘልቆ በመግባት የታወቀው ጫት መነሻውን ለካስ እኛው ጋ አድርጎ ነበርና ነው? ይላሉ አንዳንድ ያነጋገርኳቸው አስተያየት ሰጪዎች የየአከባቢዎቻቸውን ነባራዊ ሁኔታ በመግለጽ::

በዚህም መሰረት ሀረር አከባቢ የሚገኙ የጫት ዐይነቶች: ኡረታ፤ ቂዱ፤ ቀርጪ፤ ጭራ፤ ፋቃ፤ ታጫሮ፤ ጨባላ፤ ሚስማር፤ አወዳይ፤ ዑመርኩሌ፤ ገለምሶ ወዘተ ይባላሉ:: በጋምቤላ አከባቢ ቀነኒሳ ተብሎ የሚጠራ የጫት ዐይነትም አለ:: አፋር አከባቢ ደግሞ ከዋጋው ውድነት ጋር በተያያዘ መቶ ወይም መተው እየተባለ መጠራት ተጀምሯል ብሎኛል አንድ ጓደኛዬ:: በአከባቢው ይህ አባባል የተጀመረው ከዋጋ መናር

የተነሳ መቶ ብር ይዘህ ና ካልሆነ ተወው ለማለት ነውም ብሎኛል። የአደንዛዥነት ደረጃውም ከመነቃቃት እስከ ህሊና መሳት የሚያደርስ (ለምሳሌ የፊዲሱ **ዑመርኩሌ**) ዐይነት ጫት ሲኖር እንደ አፈሩ አይነትና በአፈሩ ውስጥ በሚገኘው ንጥረ ነገር ይዘትም ይለያያል። ከአንዳንድ የምርቃና/ምጥቀት መገለጫዎች ወደፊት መዳረሻ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፦

አንድ ተጠቃሚ ቀኑን ሙሉ ሲቅም ውሎ ሲመረቅን ጣቱን በአካፋ መቁረጡን ሳያውቅ በማግስቱ ነቅቷል። ቃሚው ጣቱን የቆረጠበት ምክንያት ተቅሞ የሚጣለውን ተረፈ-ጫት (ገራባ ) እግሩ ላይ ሲወረውር ቆይቶ በምርቃና የተነሣ በገራባው ውስጥ የሚንቀሳቀስ ነገር ሲያይ ተደናግጦ ጣቱን በአከፋ ቆርጦ በመጣሉ ነው ይባላል። ሰውየው የቃመው ጫት ዑመርኩሴ ይባላል። አንዳንድ ሰዎች **ዑመርኩሴ** እንዲህ የስሜት ምጥቀት የሚያመጣበት ምክንያት ስፍራው በኢትዮጵያና በሶማሌ ጦርነት ወቅት የብዙ ተፋላሚዎች ደም የፈሰሰበት አከባቢ ከመሆኑ የተነሣ እንደሆነ ነዋሪዎች ይናገራሉ።

የበላችውን ቁንጫ ፈልጎ በማጣቱ የተከራየውን ቤት ጣውላ በሙሉ ነቃቅሎ ይጨርስና ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ውጭ ወጥቶ ቡችላ ያለችበትን ክፍል ከፍቶ በመግባት ቡችላዋን በሣሙና ሲያጥብ ቡችላዋ የሳሙና አረፋ በአይኗ ገብቶ ትጮሃለች። ባለቤቶቹ ደንግጠው በመውጣት የድርጊቱ ፈጻሚ ጤነኛ ሰው እንደነበረና ምን እንደነካው ሳይረዱ ድርጊቱን ለጊዜው በማጣጣል አረጋግተው ወደ ቤት እንዲገባ አድርገዋል። ቃሚው ከድካሙ ብዛት የተነሳ ተመልሶ ከተኛ በኋላ የፈጸመውን አስነዋሪ ድርጊት የተገነዘበው በማግስቱ ራሱ የፈራረሱ ጣውላዎችን ምን እንደነካቸው ጠያቂ በመሆን ነበር።



በቀድሞ ሀረርጌ ክፍለ ሀገር ኤጀርሳ ጎሮ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ለማንም ሳይናገር ሌሊት ወጥቶ በመጥፋት በመጨረሻም አማቾቹ በሚገኙበት ሀረር አማሬሳ ከተማ የተገኘው የጫት ሱሰኛ እንደነበረም የአከባቢው ነዋሪዎች ገልጸውልኛል።
የአንድ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ሰባህሌ የሚባል አከባቢያዊ መጠሪያ ያለውን ጫት ቅሞ ፍጹም ራሱን በመሳት በባቡር ተሳፍሮ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ ምርቃናው ሲበርድለት «ማነው እዚህ ያመጣኝ» ብሎ አምባጓሮ ፈጥሮ እንደ ነበረም በመረጃ ፍለጋ ወቅት የተዋወቅኩት ጓደኛዬ አጫውቶኛል።
አንድ የአከባቢው ተወላጅ እንደነገረኝ ደግሞ ጓደኛው ከወደ ጉራጌ የመጣውን ሃይለኛ ጫት ከቃመ በኋላ ራሱን ይስታል። ከዚያም ባባቤቱ አራስ ነበረችና ጨርቅ አጥቦ፤ ቤቱን ወልውሎና ሌሎች በርካታ የቤት ውስጥ ስራዎችን ካከናወነ በኋላ ባለቤቱ በተኛችበት ካላጠብኩሽ ብሎ ሲታገል በጎረቤት ሃይል መገላገል ተችሏል።
አንድ ቃሚ ደግሞ ከነቤተሰቡ በትራንስፖርት መኪና እየቃመ ሲጓዝ ውሎ እየተጓዘ ያለው ከነቤተሰቡ መሆኑን ዘንግቶ መንገድ ላይ ወርዶ ቀርቷል። እሱ የቃመው ጫት ዑመርኩሴ የተባለውን ነበር ይላል መረጃውን የሰጠኝ ሰውየ።
ናዝሬት ከተማ ነበሩ የሚባሉ አንድ የህክምና ባለሙያ ለበርካታ ዓመታት የቆረጡአቸውን የሎተሪ ቲኬቶች አይቀዱዋቸውም አሊያም አይጥሏቸውም አሉ። ከዕለታት አንድ ቀን በከረጢት ሞልተው መኪና ከአስመጪ ኩባኒያ ለመግዛት አዲስ አበባ ሄደው ነበር ያሉኝም ሰው ነበሩ። እርሳቸው የቃሙት ጫት በናዝሬት አከባቢ «አርፊሽ ተኚ» ተብሎ እንደሚጠራም ይነገራል። ጫቱ ዛሬም ይህንኑ ሲያሜና "ተስፋ" እንዳስጠበቀ ይሆን! መልሱን ለአከባቢው ተጠቃሚዎች እንተወው!! አይመስላችሁም?

መኪና እየነዳ ጫት ቅሞ ከመረቀነ በኋላ ያልተበላሸውን ቴፕ ተበላሽቷል በማለት ሲጎረጉር የዋለ ሾፌር ደግሞ የሃዋሳ ገጠመኜ ነው፡፡ የስራ ባልደረባዬ በመሆኑም የመረጃ ፍላጎቴን ስለሚያውቅ ሳያፍርና ሳይሸማቀቅ በራሱ ጊዜ ስለሰጠኝም በወቅቱ አመስግኘዋለሁ፡፡

አንድ ስር የሰደደ የጫት ሱስ ያለው ቃሚ ደግሞ ለምን መቃም አታቆምም ተብሎ ሲጠየቅ የሰጠው ምላሽ ካልቃመ በቀር በአዕምሮው የተከማቹ ቁንጫዎች እንቅልፍ እንደማይሰጡት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ከዚህም ከዚያም ካገኘሁአቸው መረጃዎች መካከል "አረንጓዴዎቹ የአፍሪካ ኮረብታዎች" በሚል ርዕስ በአንድ ድህረ ገጽ የተሰራጨው ጽሁፍ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

**"ከድሬዳዋ እያጓራ የሚመጣው አንቶኖቭ አይሮፕላን ሲያርፍ ጂቡቲ የሰላም አየር የነፈሰባት ከተማ ትሆናለች፡፡ ከዚያም አብዮት የሚያስነሳ ሸብር፤ ቀጥሎም መቃም ይጀመራል፡፡ ጦርነት የሚያሳውጀው የሀራራ ሰዓት ያልፋል፡፡ ወግ ይጀመራል፡፡ እንደገና ቃም፤ቃም ይደረጋል፡፡ አሁንም ወግ፡፡ ይታደራል፡፡ ከዚያም ያ ሁሉ የምርቃና አብዮት ይረሳና ሌሊት ይነሳሉ፡፡ አይሮፕላን መጠባበቅ ይጀምራሉ፡፡"** ሰዎች! ከዚህ አብዮት ይሰውረን ማለቱ አይሻልም!?

በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 10
ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት
Arada Sub-City Woreda 10
Culture & Tourism Office



## ወጣቱና ጫት

*"ወጣትነት ወደ ብልጽግና ለመረማመድም ሆነ ወደ ድህነት ለመውረድ ምርጥ ጊዜ ነው፡፡" የግሪክ ገጣሚ፡፡*

ወደድንም ጠላን፤ ፈለግንም አልፈለግን ሀገራችን በልማታዊ ዕድገት የለውጥ አዙሪት ውስጥ ገብታለች፡፡ የለውጥ አዙሪቱ እንደ ሀገር ለበርካታ ዓመታት ካንቀላፋንበት ህይወት ባነን ወደፊት ልንራመድ የተነሳንበት አሊያም እዛው ተኝተን የምንቀርበት ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲያው ለነገሩ ተኝተን የምንቀርበት ጊዜ ሊሆን ይችላል ልበል እንጂ የምናንቀላፋበት ጊዜ መሆኑ ቀርቶ የምንተኛበትም ወቅት ባለመሆኑ በቀጥታ ወደ ሀገራዊ ብሎም ዓለም አቀፋዊ ልማታዊ የውድድር ሜዳ ውስጥ ገብተናል፡፡

ውድድሩ ፈጣን ልማታዊና ወቅታዊ እንደ መሆኑም ልናሸንፍ እንደምንችል ደግሞ ጥርጣሬ የለኝም፡፡ ማሸነፍ የምንችለው ደግሞ በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ የተናጥል ጉዞ (የተናጥል ጉዞ ሁሉ ለራሱ ውጤታማ እያደርግም የሚል እምነት ባይኖረኝም) በማድረግ ሳይሆን እጅ ለእጅ ተያይዘን የመራመድን ጥበብ ካወቅንበትና እርስ በርስ ከተባበርን ብቻ ነው፡፡ ኳስዋን በቀጥታ ወደ ግብዋ አነጣጥረን መለጋት ከቻልን ነው፡፡ በርትተንና ንቁ ሆነን ከተደጋገፍን ነው፡፡ የምንደጋገፍበትን ሀሳብ ልብ ለልብ ተገናኝተን ማመንጨትና መወያየት ስንችል ነው፡፡ ያመነጨነውና የተወያየነው ሀሳብ ለሀገራችን ልማታዊ እንቅስቃሴና ለመላው ህዝባችን ተጠቃሚነት አስተዋጽኦ መኖሩ መረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡ የተረጋገጠውና ተቀባይነት ያገኘው ሀሳብ ግብ እስከምመታ ድረስ ሂደት ነውና ተስፋ የሚያስቆርጥ

ጨለምተኝነት ባያደናቅፈን ነው። የእጅ ለእጅ ጉዞ የጋራ ውጤትና ስኬት፣ የጋራ ተጠቃሚነትን እንደሚያመጣ በጋራ ስንረዳ ስናስረዳና ስንረዳዳ ነው። የጋራ ተጠቃሚነት ደግሞ በሀገራዊ ልማት ዙሪያ "የጋራ አስተሳሰብን" ያመጣል። ከዚያም በጋራ ማደግ!!

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ሁሉም ሰው የራሱን አስተሳሰብና አመለካከት ማራመድ የለበትም ማለት ግን አይደለም። በሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ አብዛኛው ህዝብ በሚስማማው አጀንዳ የጋራ አቋም መያዝ ድር ቢያብር አንበሳን ያስር ነውና ለማለት እንጂ። ይህ የጋራ አስተሳሰብ በተለይም እንደኛ ገና ከእንቅልፋችን እየነቃን ላለነው ህዝቦች ዘላቂ ዕድገትና የጋራ ተጠቃሚነትን ያሰፍናል እንጂ ጉዳት የለውም። ይህ ካልሆነ በአንድነታችን ለዘለቄታው የምናጎለብተው ጥንካሬያችን ይሸረሸራል። አሸዋ ላይ የተገነባ ቤት ይሆንና ገና ከጅምሩ ይፈርሳል። ከንቱ ልማት!! ከንቱ ልፋት!! ይሆናል።

ለሀገራችን ልማት፣ ለህዝቦቻችን መጻዒ ህይወትና ብሩህ ተስፋ መፈንጠቅ ወጣቶች በምንም በማንም ሊተካ የማይችል ሚና አላቸው። ለሀገራዊ ልማት ትልቅ አምራች ሀይል ናቸው። ትልቅ አቅም በመሆናቸውም አዳዲስ ሃሳቦችን የማፍለቅና ይህንኑ ሃሳብ ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ ተነሳሽነት ቁርጠኝነትና ፍላጎት አላቸው። ወጣቶች በአግባቡ ከተመሩ ወደመሩበትና ወዳሳዩበት መንገድ በቀላሉ የመከተል ትልቅ ተመክሮ አርአያነትና ተሰጥኦም አላቸው። ወጣቶች አንጋፋ የለውጥና የልማት አንቀሳቃሽ ሞተሮች ናቸው። የብሩህ አዕምሮና የፈጣን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ግንባር ቀደም ተዋናዮች በመሆናቸውም በጥንቃቄ ሊኮተኮቱ፣ ሊታረሙና በጥንቃቄ



አቅጣጫ ማስያዝን ይጠይቃል። ሃሳባቸው ተደማጭነት ሊኖረው ይገባል። ሃሳባቸው ተደማጭነትና ተቀባይነት ከሌለው የልማት ሳይሆኑ የጥፋት ሀይሎች ይሆናሉ። ዘለቄታ ለሌለው ጥቅም ተጋላጭና ተጠቂ ሊሆኑ ይችላሉ። በሀገራቸውና በገዛ ህዝባቸው ልማትና ልማታዊ እንቅስቃሴ ዙሪያ አፍራሽ ሚና የሚጫወቱ ሀይሎች እንዳይሆኑ በያንዳንዷ እርምጃና አጋጣሚ አያያዝና አዎንታዊ ክትትል ያስፈልጋል። ይህንን መስመር በወቅቱ አጥብቀን ማሳየት ካልቻልን አሉታዊ ሚና መጫወታቸው አይቀሬ ታሪካዊ ክስተት ይሆናል። በአሁኑ ወቅት ይህንኑ አሉታዊ ሚና በአህጉራችንም ሆነ በሌሎች የዓለም ክፍሎች ተጨባጭ እያስተዋልን ያለነው እውነታ ነው።

በዓለማችን ከሰባት ቢሊዮን በላይ ህዝብ ይኖራል። ከዚህም ህዝብ መካከል ሁለት ቢሊዮን የሚገመቱት ወጣቶች እንደሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ። ወደ ሀገራችንም ስንመለስ 80 ሚሊዮን ይሆናል ተብሎ ከሚጠበቀው ህዝባችን መካከል 26 ሚሊዮኑ ወይም 31.8 ከመቶው ወጣት እንደሆነ ይገመታል። ወጣቱ በአሁኑ ዘመን ከምን ጊዜም በላይ ፊቱን ወደ ልማትና ምርምር እንዳያነጣጥር ከፊት ለፊቱ በርካታ መሰናክሎች እየተጋረጡ ናቸው። መሰናክሎቹና ምክንያቶቹ እንደ የአከባቢዎቹና እንደየሀገሩ ነባራዊ ሁኔታ የተወሳሰቡ ሊሆኑ ይችላሉ። ከነዚህም በርካታ መሰናክሎች መካከልም አደንዛዥ ዕጾች ተጠቃሾች ሲሆኑ በአደገኛ ፍጥነት ከሀገር ወደ ሀገር በመሰራጨት ላይ ይገኛሉ። አደንዛዥ ዕጾች በዘመናችን እያደረሱ ያለው ጉዳት በቃላት ብቻ ተገልጾ የሚያልቅ አይደለም። ከሀብትና ከንብረት መውደም በላይ የሰው ልጆችን ህይወትና ማህበራዊ አኗኗር ውስብስብና አሳሳቢ እያደረጉ ናቸው። ዕጾቹ በተለይም ደግሞ የወጣቶችን ንጹህ አዕምሮአዊና

አካላዊ ቁመና ባለራዕይ እንዳይሆኑ እያደናቀፉና እያቆሸሹ ይገኛሉ። ረጅም ርቀት መጓዝ እየቻሉ በአጭር እንዲቀሩ እያደረጉ ነው። በዚህም ሳቢያ ሳይለፉ ሳይደክሙና ሳይጥሩ በአቋራጭ መክበርን ምርጫቸው የማድረግ አዝማሚያዎችን የሚመርጡ/የሚያስሉ ወጣቶች ጥቂት አይደሉም።

የሱሶቹ ህገወጥ ዝውውር በዓለም አቀፍ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። የስርጭት አድማሱን እያሰፋ በመምጣትም የወጣቱን ስነልቦና፣ አዎንታዊ አስተሳሰብ፤ ተነሳሽነትና ብቃት እየጎዱ የመምጣታቸው ገሃድ እውነታ የአደባባይ ሚስጥር እየሆነ ነው። ተግዳሮቱ የማህበራዊ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ያለመረጋጋት ማስከተል የሚያስችል ሀይል አለው። እውን መሆን የሚያስችል ልማታዊ ራዕይ ያነገበ የወጣት ንቅናቄ እንዲፈጠር መስረት የሁላችንም ኃላፊነትና ግዴታ ሊሆን ይገባል። ወጣቶች የጥፋት መሳሪያ እንዳይሆኑ ድምጻቸው ሊደመጥና ተገቢውን ምላሽ ሊያገኙ ይገባል።

ወጣቶች በአግባቡ ከተያዙና አቅጣጫ ተቀምጦላቸው ከተመሩ፣ የተሳትፎ እድል ከተሰጣቸው ለዓላማ ይሰለፋሉ፤ ይሞታሉ፤ ድህነትንና በየጊዜው እንደ ተጋቦሽ በሽታ እየተከታተሉን የሚያጠቁንን የኋላቀሪነት ተቀጽላዎች በተባበረና በትኩስ ጉልበት ያጠፉሉ። አጋጣሚና ዕድል የሚጠብቁ ሳይሆኑ ለፈጠራ ለምርምርና ለአርቆ አስተዋይነት ተኝተው የማያድሩ ንቁ ዜጎች ይሆናሉ። ሙሉ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን ለአዎንታዊ ተግባር መስዋዕት የሚያደርጉ ትውልዶች ይቀረጻሉ፣ ይፈጠራሉም። እንዲህ ዐይነቱን ዜጋ ለማፍራት ሃላፊነቱ የመንግስት ብቻ ሳይሆን የቤተሰብና የህብረተሰብም መሆን ይገባዋል።



ወጣቶች በመልካም ሀገራዊ ባህልና ጨዋነት ቢታነጹ ለሀገራቸውና ለህዝባቸው የጀርባ አጥንት ናቸው። ሀገር የመውደድ ስሜታቸው በቀላሉ የሚራገብና የሚወዛወዝ አይሆንም። በራሳቸው ማንነት የሚኮሩ እንጂ የሚሸማቀቁ አይሆኑም። በመጤ ባህል ሳይሆን ለራሳቸው ባህል፣ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ክብር፣ ፍቅርና መውደድ በእርግጠኝነት ሃላፊነትና ግዴታ ያላቸው ዜጎች ይሆናሉ። በቀላሉ ወደነፈሰበትና ወደተሳሳተ አቅጣጫ የሚቀለበሱ ዜጎች አይሆኑም። እጃቸውና አዕምሮአቸው ተጠምዝዞ ከሀገራዊ ልማት ያፈነገጠ መስመር አይከተሉምም። ማንነታቸውንና የወጣትነት መለያቸውን ለአልባሌ ዓላማ አሳልፈው አይሰጡም።

በጎጂ ባህላዊና ልማዳዊ ሱሶች ሳቢያ ጊዜያቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ የሚሸጡም አይሆኑም። ጽኑ ሀገራዊና ህዝባዊ ባህልና ስነምግባር መከተል ይጠበቅባቸዋል። ገና በልጅነታቸው በአንጉል ሱሶችና ልማዳዊና ባህላዊ ጫናዎች ስር እንዳይንበረከኩ እገዛ ማድረግ ይጠይቃል። የወጣቱን ትውልድ አርቆ አሳቢነት ለማኮላሸትና በአጭር ርቀት ለማስቀረት ሲባል በየስርቻው እየተተከሉና እየተፈበረኩ በሚመጡ የአደንዛዥ ዕጽ ሱሶች፣ መጤ ፊልሞችና ጌሞች መደበኛ ጊዜያቸውን ማጥፋት የለባቸውም። ጫትን በመሳሰሉ ሱስ አማጭ ዕጾች ወጣቱ ተደልሎ በዕውቀቱ ሀገሩን የሚያለማበትንና ጊዜውን ለምርምር የሚያውልበትን ጭንቅላት ማደብዘዝ ብሎም ማደንዘዝ ልማታዊ እንቅስቃሴን ይገታል።

ጫት ዛሬ የምግብ እህል እርሻ መሬቶችን እየተሻማና በከፍተኛ ፍጥነት እየተስራጨ ይገኛል። በስፋት በሚመረትባቸው ሀገሮች ብቻ ሳይሆን በውድ ዋጋ እየተገዛ ከፍተኛ ትርፍ በሚዛቅባቸው

ሀገሮች እንኳን የተጠቃሚዎች ቁጥር እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ መምጣቱ አይስተዋልም። ወጣቶች የነገ ሀገር አለኝታዎችና ገንቢዎች በመሆናቸው የጫትና የሌሎች ደባል ሱሶች ሰለባ መሆን እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ገና የልማትንና የምርታማነትን ጣዕም እያጣጣሙ ለመጡ ሀገሮች የልማት አደናቃፊነቱ ቀላል ግምት የምሰጠው አይደለም። ለዘመናት የደበዘዘውን ያህል እየፈነጠቀ የመጣውን የሰውጥ ብርሃንና ተስፋ ሰጪ የዕድገት እርምጃችንን ባለበት የሚያስኬድ አሊያም ወደኋላ የሚጎትት ጎጂ ባህል ይሆናል። በድህነታችን በተለያዩ መድረኮች ያፈርነውን ያህል እስካሁን ያስመዘገብናቸው ጅምር ድሎች ዕውቅና አስገኝቶልናል። ድህነታችንንና ኋላቀርነታችንን እንጂ ጠንካራ ጎናችንን መናገር የሚያሳፍራቸው አንዳንድ ወገኖች ሁሉ ባስመዘገብናቸው ድሎች አስገዳጅነት እውነታውን በይፋ መናገር ጀምረዋል። እንደሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎቻችን ሁሉ በነዚህ ድሎች ጀርባ፣ ከፊት ለፊትም ሆነ ከግራና ቀኝ የወጣቶቻችን ቀጥተኛ ተሳትፎ አለበት። ወጣቶች ሃላፊነትንና ግዴታን መሸከም የሚችል ሰፊና ጠንካራ ትኬሻና ብሩህ አዕምሮ አላቸው። የተሳትፎአቸውን ውጤት ራሳቸው በኩራትና በዘላቂነት ማጣጣም ይጠበቅባቸዋል። ወጣቶች እንዲህ ዐይነት ሃላፊነት መሸከም የሚችሉ ሀይሎች መሆናቸውን በማረጋገጥም ተገቢና ተከታታይ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። የሀገራችንን ወጣቶች ወደ ባዕድ ሀገሮች ስደት መዳረግና መሞት መንስኤ የሆነውን ድህነትና ኋላቀርነት በፋርጣማ ክንዳቸው መናድ ይችላሉ። በዚህም ጥረት ያገኙትን መልካም ተመክሮና አጋጣሚ የፈጠራ ችሎታቸውን በማጀብ ለሌሎች የማስፋፋት ዕድልም ድፍረትም ይፈጥርላቸዋል።



በተለያዩ ሀገሮችና ወቅቶች እየተስተዋሉ ያሉ ታሪካዊ ክስተቶች የሚያስገነዝቡን ወጣቶች ተዓምር ሰሪዎች የመሆናቸውን ያህል በሁሉም ስፍራና ጊዜ የጥፋትም የልማትም ሀይል እየሆኑ እንደሚመጡ ነው። ሆነዋልም ደግሞ። የጥፋትም ሆነ የልማት ሀይል የሚሆኑት እንደየአያያዛችን፣ አስተምሮአችንና አቀራረባችን ሊሆን ይችላል። እንደየአስተዳደጋቸው፣ እንደየአከባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታና፣ እንደየቀሰሙት ትምህርትና ትምህርት ሰጪው ዜጋ ስብዕናና መልካም አርአያነት ነው። አስቀድሞ በቤተሰብ፣ በትምህርት ተቋማት፣ በማህበረሰብና በሌሎችም ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት ማነጽ ከተቻለ አርአያነታቸው የላቀና ድንበር ዘለል ይሆናል። ለልማት፣ ለሰውጥና ለትራንስፎርሜሽን የሚያቃጥል ፍቅር፣ የማይነቃነቅ አቋምና አዎንታዊ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል። ቆራጥነትና ተቆርቋሪነት በውስጣቸው ይጸነሳል፣ ይወለዳል፣ ያድጋል። አስተማማኝ መሠረት ላይ ይቆማል። ይህ ትኩስ ሀይል ይህንን የጋለ ሀገራዊና ህዝባዊ የልማት ፍቅርና ጥማቱን በአግባቡና በወቅቱ ሳይጠቀምበት በጫትና መሰል ሱሶችና አደንዛዥ ዕጾች እንዳያዳክም እንከላከል። እንጠብቃቸው፣ እንደየአቅማችንና እንደየነባራዊ ሁኔታችን እንንከባከባቸው። እንምከራቸው።

ጫት ዛሬ በተለያዩ የሀገራችን ክልሎችና አስተዳደሮች የሚተከል ተክል ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም በፍጥነት እያዳረሰ የሚገኝ ጥንታዊና ኢትዮጵያዊ ተክል ነው። ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ለረጅም ዘመናት ከሌሎች የሃገራችን አከባቢዎች በገዘፈ መልኩ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ብቻ ተወስኖ ከነበረበት በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የገጠርና የከተማ አከባቢዎች የሚዘወተርና በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ ተክል ሆኗል።

እንዲያውም በተወሰኑ አከባቢዎች ያለው የጫት አቃቃም ስርዓት ያለ ጫት ህይወት ትርጉም የሌለው እስከሚመስል ድረስ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ነው። የአቃቃሙ ስርዓት የተጋነነ ነው የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች እንዳሉ ሁሉ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እየደረሰ ነው የሚሉ ታዛቢዎችም ቁጥራቸው በርካታ መሆኑን መረዳት አያዳግትም።

ጫት የወጣቱን አዕምሮ ማነቃቃት ብቻ ሳይሆን ያደነዝዛል። ያፈዛልም። መስራት የሚችል እጅና እግር ገና ከጠዋቱ እስሮ "መደብ" ላይ ያስቀምጣል። የስራን ክቡርነት ያዘናጋል፣ ያስረሳልም። ሰማይ ላይ ተወርውሮ እንደሚንሳፈፍ ፊኛም አስተሳሰብን ባዶ ሜዳ ላይ በትኖ "ፈላስፋ" አሊያም ቃልቻ ያደርጋል። በቃሚዎቹ አባባል በዚሁ መነቃቃት ወይም ምርቃና አዕምሮአቸው ደብዝዞና ደንዝዞ የሚገኙ ተጠቃሚዎች ቁጥር እንደየአከባቢው ቢለያይም መጠኑ እየገዘፈ መጥቷል። አብዛኛዎቹ ቃሚዎች በጫት የፈዘዙና የደነዘዙ መሆናቸውን ለማወቅ ብዙ መመራመር አያስፈልግም። በገጠርም ሆነ በተለይም በከተሞች መንገዶች ላይ በሚዘዋወሩ የአዕምሮ በሽተኞች ጫት ከእጃቸው የማይጠፋ መሆኑ አንዱ ማሳያ ነው። እሱን በእጃቸው እንደያዙ የሚያለቅሱ፣ የሚተክዙና ጋራባውን ተሸክመው ከአከባቢ ወደ አከባቢ የሚዞሩትን ብሎም በየደረሱበት ቁጥጥ ብለው በመቀመጥ የሚቅሙትን ማየት ከተለመደው በላይ እየሆነ ነው። እንዲያውም የመኪና ውስጥ መቀመጫዎችን በመዘርጋት እየቃሙ የሚፈላሰፉም አጋጥመውኛል። በሀራራ ሰዓት ጫትን ለማግኘት የማይወጡት ዳገትም ሆነ የማይወርዱት ቁልቁለት የለም። የአንዳንዶቹማ ሁኔታ ሲታይ በህይወታቸው ከጫት ውጪ ምንም ነገር ቅድሚያ ሊሰጥ አይገባም ብለው ሌክቸር ሊሰጡ የተዘጋጁ



ይመስላሉ። ወፍራም ብር ከኪሳቸው መዘው ሲያወጡ ጉራ ብጤም አለችባቸው። ምርቱ የቀነሰበት ወራት ከሆነና ይህንኑ ካገኙ በኋላም ደስታቸው ወሰን የለውም። ፊታቸው ይፈካል። ይስቃሉ። በማግስቱ ደግሞ የማይደረደር የህመም ዐይነት የለም። አንዳንዴ እነርሱ በዘረዘሩት ህመም መጠን ቆመው መሄዳቸው ደግሞ እንኳን ሌላውን እነርሱንም ሳያስገርማቸው አይቀርም። ሲያጡ ደግሞ ወዛቸው ይደርቃል። የመቃም ሱስ የተጸናወታቸው በበኩላቸው መግዛት በማይችሉበት ወቅት ቃሚ ካጋጠማቸው ለምነው ወይም አግባብተው ለመውሰድ የሚያደርጉት ጥረት ለዚህ ያበቃቸው አጅሬ ጫት መሆኑን ጥርጣሬ እንዳይገባዎት ያደርጋል። ጫት በሚሸጥባቸው ገበያዎች እንደ ጤነኛ ሰው አድፍጠውና ሰርቀው (ነጥቀው) የሚሄዱ እብዶችም አሉ። እሱማ በሀረርጌ ገበያዎች ፍየሎችም ነጋዴዎቹ ካልተጠነቀቁ በስተቀር እንደሰው አዘናግተው ቀምተው ይሮጡ የለ! ውሸት መሰለዎት? እዛ የሚያውቁት ሰው ካለ ከኔ የበለጠ በአከባቢው ጣፋጭ ቋንቋ ያረጋግጥልዎታልና ይጠይቁ! አቦ ተግባባን?

የንባብ ባህልን ያሳድጋል በሚል ሰበብ እየቃሙ ሱሰኛ ሆነው አዕምሮአቸው የተጎዳባቸው ምሁራንም ቁጥራቸው ቀላል ባለመሆኑም ይህንኑ ቤት ይቁጠረው ማለቱ ይቀላል። ትምህርታቸውን አቋርጠው የትምህርት ፍላጎታቸውና የመቀበል አቅማቸው የከሰመባቸው ወጣቶችም እንዲሁ። ምንም እንኳን በአንዳንድ ሞቃታማ የሀገራችን አከባቢዎች የሚለያይ ቢሆንም አንድ ሰው በመንግስት መ/ቤት በቀን መስራት ያለበት ስምንት ሰዓት ነው። ከስምንቱ ሰዓት አራቱ ጠዋት አራቱ ደግሞ ከሰዓት። የመቃም ሱስ ያለባቸው ከቀኑ አምስት እስከ ስምንት ሰዓት አብዛኛውን ጊዜያቸውን ለጫት

ይመድባሉ፡፡ ተገደው በስራ ገበታ ላይ እንኳን ቢሆኑ ውጤታማ አይሆኑም፡፡ ሃሳባቸውን አሰባስበውና ተረጋግተው መስራት ስለማይችሉ መነጫነጭና መቁነጥነጥ ያበዛሉ፡፡ ይህ የአንድ ቀን ክስተት ሳይሆን የየዕለት ውሎ አደር ተግባር ነው፡፡ አዕምሮአቸው በሱሱ መደንዘዙን እያወቁ ወይም ሌላው ማህበረሰብ እያወቀ ራሳቸውን እንደ ሰጎን ወፍ(ኦስትሪች) አሸዋ ውስጥ መደበቅ ይፈልጋሉ፡፡ ይመረቅናሉ፡፡ ምርቃና ማለት በሌላ አነጋገር ራስን ማደንዘዝ ማለት ነው፡፡ መደንዘዝ ያለበት የሚያም የሰውነት ክፍል ማደንዘዝ ሲወጋ እንጂ ንጹህ አዕምሮአችንን ለንጹህ ዓላማ መጠቀም እየቻልን ለምን በጫት እናደነዝዛለን?፡፡ በእምነት ስፍራዎች፤ በትምህርት ተቋማት፤ በመዝናኛ ቦታዎች፤ በቲያትር ቤቶች፤ በአደባባዮች፤ በመኖሪያ ቤቶች፤ በሲኒማ አዳራሾች፤ በመስሪያ ቤቶች፤ በለቅሶ ቦታዎች፤ በገበያዎች በአጭሩ በሁሉም ጊዜና ቦታ ሲቃም እናስታውሳለን፡፡ በዚህም ሁለገብ "አገልግሎቱ" የተጋነነ ካልመሰላችሁ እንዲያውም "የሁሉም ለሁሉም" ማህበራዊ አገልግሎቶች የሚውል ዕጽ እስከ መባል መቃረቡን ከላይ ገልጫለሁ፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ በሀገራችንም ሆነ በሌሎች አብቃይና አብቃይ ባልሆኑ ሀገሮች ጫት ባይቃምም ይተከላል፤ ባይተከልም ይቃማል፡፡ በጫት ዕርቅ ይካሄዳል፤ ይጠናል፤ ጋዜጠኛው ዘገባ ይሰራል፡፡ ደራሲው በጫት ሃይል አዕምሮውን አነቃቅቶና ጨምቆ ሃሳብ ያመነጫል፡፡ ሙዚቃኞች ውዝዋዜዎቻቸውንና የፈጠራ ስራዎቻቸውን በጫት ንቅቃት /ሞቅታ/ ያደምቃሉ፡፡ አርሶ አደሩ «የዐይን መክፈቻ» ነው ብሎ ገና ከጠዋቱ በመቃም ማሳውን ከጠዋት እስከ ቀትር ብልት በብልት ይተረትረዋል፡፡ ለመሆኑ ይህንን እምቅ ሀይላችንን ከጫት ውጭ ልናሰራ አንችልም? በጊዜ በመቃም ዙሪያ ውሳኔ



ላይ ካልደረስን ወይም እንዲደርሱ ካላደረግን በቃሚዎቹ አካላዊና አዕምሮአዊ ስብዕና ጉዳት ስለመድረሱ አንጠራጠር! ለማንኛውም ወገኖቻችን ናቸውና እስቲ በየአከባቢያችን የወጣቶቻችንን ውሎና አዳር ወዴት እያዘነበለ እንዳለ በትንሹም ቢሆን ለማጥናት እንሞክር፤ እንከታተልም፡፡

ሀገራችን ባላት አቅም ድህነትን መሻገር የሚያስችሉ በርካታ የልማት ስትራቴጂዎችን ዘርግታለች፡፡ እየዘረጋችም ነው፡፡ ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ በሆነ ልማት ሁሉም ዜጋ ተጠቃሚ እንዲሆንና ዝርጋታው ሁሉንም አከባቢ ያደረሰ እንዲሆን ደፋ ቀና እያለች ነው፡፡ መንገዱ ከባድ ውጣ ውረድ ያለበት ቢሆንም ወደ ውጤት እንደምንደርስ ደግሞ እርግጠኞች ነን፡፡ ውጣ ውረዱን መሻገር ብቻ ሳይሆን ማሻገር የሚችል ትውልድ እየተፈጠረ ነው ማለትም ይቻላል፡፡ ድህነትን፣ ስራ አጥነትን፣ መድሎን፣ ምዝበራን፤ ዘረኝነትን፣ በአጭሩ ስወርዱ፤ ስዋረዱ.. ስዋረዱ..ስዋረዱና ስንከባለሉ የመጡ ቁስሎቻችንን አራግፈን ለመጣል ወጣቱ ሁልጊዜ ዝግጁነቱንና አለኝታነቱን ማረጋገጥ አለበት እንጂ በጫትና መሰል ሱሶች መዘዝ ራሱን ማዘናጋት የለበትም፡፡ የውድድር ዘመን መሆኑን በጥንቃቄ ሊረዳ ይገባል፡፡

ዛሬ በሀገራችን ለጫት እየዋለ ያለው የወጣት ጉልበትና ጊዜ ቀላል አይደለም፡፡ እየባከነ ያለው ገንዘብም ከመቶ ሚሊዮኖች በላይ እየላቀ መጥቷል፡፡ ሀገራችን እያስመዘገበች ባለው ልማታዊ እድገት የዓለም ህዝቦች ዐይንና ጆሮ ኢትዮጵያ ላይ አነጣጥሮ ባለበት ወቅት የወጣቶቻችን አስተሳሰብና አመለካከት መቀየር ሲገባው ወደ ጫት ማነጣጠር የለበትም፡፡ አሸባሪነትና የሃይማኖት ጽንፈኝነት የሀገራችንን ብሎም የዓለም እቀፉን ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት የኒሊዮሽ ለመንተት እየተፋለሙ

ባለበት ወቅት ወጣቶቻችን የሰላም አምባሳደሮችና የልማት መሳሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ይህንኑ መሳሪያነታቸውን በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋልም። ሰላምንና ልማትን የ21ኛው ክፍለ ዘመን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መሳሪያ በማድረግ ጽኑ ትግል የወቅቱ የትግል ምርጫቸው ማድረግ አለባቸው። የዕጽ ሱሰኝነት የጥፋት መንገድ እንደሆነ ግንዛቤ ማስያዝና መያዝ ተገቢ ነው። በወጣትነት ዘመን የትኛው አካሄድ የዕድሜ ልክ ጥበብ፣ ዕውቀትና ክህሎት ማግኛ መንገድ እንደሆነ አንጥሮ መለየት ያስፈልጋል። ለዚህም ነው *በጥንታዊው የግሪክ ገጣሚ ዳወጣትነት ወደ ብልጽግና ለመረማመድም ሆነ ወደ ድህነት ለመውደቅ ምርጥ ጊዜ ነውጣ የተባለው።*

ወጣቶች ማህበራዊ ተቀባይነት በሌላቸው ሱሶች መጠመድ ከማህበረሰቡ ያገላቸዋልና ቆም ብለው ማሰብ ይጠበቅባቸዋል። በንደዚህ ዐይነት ሱሶች ሳያውቁና ሳይወስኑ የገቡ ሁሉ ጎጂነቱን እያወቁ ጠበቅ ያለ ውሳኔ ላለመውሰድ እድልን ወይም አጋጣሚን ብቻ ይጠብቃሉ። ራስንና ቤተሰብን ማስተዳደር ወዳለመቻል እያደረሰ እንደሆነ እየታወቀ የከፋ መስመር ጠበቅ አድርገው ይይዛሉ።

እያሳሳቀ እየወሰደ ወዳለው ወንዝ ውስጥ ዘለው በመግባት እየተወሰዱ ነው። ሱሶቹ ራስን አስገድደው ከመቆጣጠር አልፈው ሁለንተናዊ ስብዕናን ማዘዝ እስከሚጀምሩ ማንነትን ገዝቅ አድርጎ ማየት፤ ከሌሎች ሰዎች ራስን ማግለልና በሰዎች ዘንድ ጠቃሚ ሰው እንዳልሆነ ተደርጎ መታየት፤ ራስን መጸየፍና መጣል፤ ፍርሃት፤ መሸማቀቅ፤ ተስፋ መቁረጥ ... ወዘተ ይመጣል። ተጠቃሚው ይህ ሁሉ ችግር በምን ምክንያት



እንደተከሰተ እያወቀ ወደ መፍትሄ ከመምጣት ይልቅ ችግሩን አሳንሶ ያያል። በሱሱ ጭብጥ ዙሪያ ለመወያየትም ሆነ ለመተማን የፊቃደኝነት ማነስ ገዝፎ ይታያል።

ከየአደባባዩ፤ ከየመደርደሪያው፤ ከየቤተመጻህፍቱ፤ በአጭሩ ከየአጋጣሚው ሁሉ ዘላቂ ዕውቀት ለመኮረጅም ሆነ ለመሸመት መጣደፍ የወጣቱ የዕለት ከዕለት ተግባሩና የዘወትር ጥረት መሆን ይጠበቅበታል። መሸመት ሲባል ደግሞ አዲስ ግኝት አፍላዊነትን እንዳያጨልም ጠንቀቅ ማለት! የሌሎችን ዕውቀትና ክህሎት ለመኮረጅ ፍላጎት እንዳሳየን ሁሉ የኛንም መልካም ተመክሮ ሌሎች እንዲቀስሙ የምናደርግ አኩሪ ታሪክ ያለን ህዝቦች መሆናችንን በኩራትና በልበሙሉነት ማሳየት አለብን። ለዚህ ጥንካሬ ግንባታና ዘላቂነት ጫት አስተዋጽኦ የለውም ማለት አይቻልም ይሆን? እስቲ እያንዳንዳችን በጫትና በሌሎች ዕጾች ዙሪያ አከባቢያዎቻችንን ምን እንደሚመስል አሁንም በሀገራዊ ስሜት እንመልከት። የህሊና ደኝነት እንስጥ! ወጣት ወንዶችና ሴቶች በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ በእርግጠኝነት ተወዳድረውና አሸንፈው ተመራጭ ስራ የሚሰሩ እንጂ ስደተኝነትን ናፋቂዎች እንዳይሆኑ አሁኑኑ ተግተው መማር እንዳለባቸው መስራት ይጠበቅብናል። ተግተው እንዲማሩም በየአጋጣሚ ሁሉ መምከርና ማስተማር አለብን። ለምን ቢባል አጀንዳው ሀገራዊ ጉዳይ ነዋ!! ራዕያቸው ሊሳካ የሚችለው ሰላም ሲኖር እንደሆነ፤ ተቀናጅተው፣ ተባብረውና ተፋቅረው ሲሰሩ እንዲሁም ችግሮችን በሰለጠነና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የመፍታት ባህል ሲኖር እንደሆነ ማወቅንና ማሳወቅን ከኛ ይጠብቃሉ። በየአጋጣሚው ሁሉ የኛን ጠንካራም ሆነ ደካማ ጎን ተምረው ይህንኑ ለመተግበር ዝግጁነት እንዲኖራቸው ማስቻል አለብን።

ወጣት ታላቅ የለውጥና የልማት ሀይል እንደሆነና በሁሉም ስፍራና ቦታ በአግባቡ ካልተያዘ የጥፋት ሀይል ሊሆን እንደሚችል ከላይ ተመልክተናል። መንገዱን በትክክል ካላየናቸው መፍትሄ አፍላቂዎች ናቸው። ሁለገብ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን በሁሉም ዘርፎች እንጠቀም። ከነባርም ሆነ መጤ ሱሶች ለማላቀቅ ሁላችንም ሀገራዊ ሃላፊነት አለብን። ይህንን ማድረግ ከቻልን እያንዳንዳችን መወጣት የምገባንን ሀገራዊ የዜግነት ድርሻ የተወጣን መሆናችንን እንዘንጋ!!

በመግቢዬ ላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሁሉ ይህንን መጽሀፍ በጫት ዙሪያ ሳዘጋጅ አንዳንድ ሰዎችን አማክሬአለሁ። የበርካታ ሰዎችን የምርምር ስራዎችና ድህረ ገጾችን በተደጋጋሚ ቃኝቻለሁ። የሀገር ሽማግሌዎችንና ጥቂት የውጭ ዜጎችንም አነጋግሬአለሁ። ከሀገር ሽማግሌዎች መካከልም የጫትን ጥቅምና ጉዳት ጠንቅቀው የሚያውቁ አባቶች ይገኙባቸዋል። በተለይም አፊ ታሪኩን እንዲያጫውቱኝ ስጠይቃቸው የአከባቢው ባህልና ወግ እያሳፈራቸውና እየተሸማቀቁ የገለጹልኝም አባቶች ነበሩ። ከመረጃ ሰጪዎቼ መካከል አንዳንዶቹ ፊራ ተባ ያሉት ያለ ምክንያት አልነበረም። በአከባቢው ባህል መሰረት በጫት ዙሪያ አሉታዊ አስተያየት ለጋዜጠኛ ሰጡ ተብለው እንዳይገለሉ በመፍራትም ይመስለኛል። ነውም ደግሞ። በዚህ ርዕስ እንዳልጽፍ ያናናቁኝ ግለሰቦች እንዳሉ ሁሉ ያበረታቱኝና ያነሳሱኝ ወዳጆቼም በርካታ ናቸው። ሁሉንም ለሰጡኝ አስተያየት ከልብ እያመሰገንኩ ከዚህ በመቀጠል ስለ ጫት የአንዳንድ ሰዎችን ህያው አባባሎችና በተጨባጭ እውነታ የተደገፉ ምልከታዎችን ከልዩ ልዩ ገጠመኞች ጋር እንመለከታለን።



## ስለ ጫት ማን ምን አለ!!

የኢትዮጵያ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒትስር የነበሩት ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ መስከረም 12 ቀን 2000 ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ የመላ ሀገራችንን ወጣቶች ባወያዩበት ወቅት ጫትን ጨምሮ ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን አስመልክተው ሲናገሩ በርካታ ቁምነገሮችን አስጨብጠዋል። ከነዚህም ቁምነገሮች መካከል ጫትንና አደንዛዥ ዕጾችን ብቻ በተመለከተ የተናገሩአቸውን ጭብጦች በመለየት እንደሚከተለው አቀንባብሬአለሁና እነሆ!

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወቅቱ የሀገራችን ችግርና ይህንኑ ችግር ለመሻገር ምን መደረግ እንዳለበት ሲናገሩ «ዋናው ችግራችን ድህነት ነው። ዋናው ችግራችን የሚያነክስና የተለያዩ መሰናክሎች ያሉበት የመልካም አስተዳደር ችግር ነው። ያሁኑ ትውልድ ተልዕኮ እነዚህን ክስተቶች መቀየር ነው።

ይህንን ለማድረግ ተራራ መውጣትና ፋኖ ተሰማራ ብሎ መዘመር አያስፈልግም። ይህንን ለማድረግ ጥሩ ሙያተኛ መሆን ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ አናጢ፣ ግምበኛ ወዘተ... መሆን ያስፈልጋል። ራስን ከተለያዩ ማህበራዊ ግድፈቶች ነጻ ያደረገና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ያለው ወጣት መሆን ያስፈልጋል። ምክንያታዊና ሳይንሳዊ በሆነ ትንታኔ የሚያምን ወጣት መሆን ያስፈልጋል» ብለዋል።

ከህብረተሰባችን መካከል ወጣት ማለት ምን ማለት እንደሆነና ወደፊት የሚጠብቀውን ሀገራዊ ተልዕኮም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲያብራሩ «ወጣት ማለት በስሜት የሚነዳ ሰው ማለት ሳይሆን የለውጥ ጉልበት ያለው ሀይል ማለት ነው። እያንዳንዱ

ትውልድ ያለፈውን ትውልድ አርዕስት እየወረሰ አይኖርም። እያንዳንዱ ትውልድ የራሱን አሻራ እያስቀመጠ መሄድ አለበት። እናንተ አሁን የድህነትን ምሽግ መደርመስ የሚያስችል ትጥቅ ያስፈልጋችኋል። ጦርነቱ ያለው በተራሮች ላይ ሳይሆን በግብርና፣ በኮንስትራክሽን፣ በንግድና አዳዲስ ተቋሞችን በማቋቋም ስራ ላይ ነው። በዚህ ጦርነት ውስጥ አሸናፊ መሆን የሚያስችላችሁ የዕውቀትና የክህሎት ትጥቅ ያስፈልጋችኋል። የስራ ተነሳሽነት፣ የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የማስፈን ትጥቅ ያስፈልጋል።»

የዚህ መጽሀፍ ዋንኛ የትኩረት አቅጣጫ ወደሆነው ጫት ሲመለሱም ክቡር አቶ መለስ ልምዳቸውን ሲያካፍሉ «አንዳንዱ ወጣት ጫት መቃም ዘመናዊነትና ስልጡንነት መስሎ ይታየው ይሆናል። አደንዛዥ ዕጽ ውስጥ መዘፈቅ ስልጡንነት ሊመስለው ይችል ይሆናል። ከዚህ ነጻ መሆን ያስፈልጋል።

በኛ ትውልድ ጊዜ የመርካቶ ስልጡኖች የሚጠቀሙት ቃል ነበራቸው። ጋሪባ፣ ፋራ… ይሉ ነበር። በወቅቱ እነዚህን ነገሮች ያለመጠቀም ፋራ ተደርጎ መወሰድ ይኖራል። እኔ የራሴን ልምድ ልንገራችሁ። ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መጨረሻ ላይ ነው እኔ ሲጋራ ማጨስ የጀመርኩት። በዚያን ጊዜ ስልጡኖች የምላቸው ሰዎች ሲጋራ ያጨሳሉ። እኔም ወጉ ይድረሰኝ አልኩና ጀመርኩ። አሁን በሰለጠነው ዓለም ፋራ/ጋሪባ የሚባለው የማያጨስ ሳይሆን የሚያጨስ ሰው ነው።» ሲሉም አስምረዋል። ወጣቱ ከማን ምን እንደሚማርና እነርሱንም የማነጽ ተግባር የማን ሃላፊነት እንደሆነም በውይይቱ ወቅት ክቡር አቶ መለስ አጉልተው ሲያሳዩ «ይህንን ባህል ወላጅ ብቻ ሊዋጋው አይችልም። እኔ የተከተልኩት በአቅራቢያዬ



የሚያጨሱትን አይቼ ነው። ወጣቱም ሌላውም በአቅራቢያው የሚያየውን አይቶ ነው የሚከተለው።» ብለዋል።

ወጣቶቹን በቀጣይነትና ተከታታይነት ከሱሰኝነት ይልቅ ወደ ሀገራዊ ልማታዊ መስመር ለማምጣት ተልዕኮ ሲሰጡም «እናንተ ከዚህ ነጻ የሆናችሁ ወጣቶች በውነቱ ስልጡኖች እናንተ መሆናችሁን አውቃችሁ፣ አደንዛዥ ዕጽ ውስጥ የተዘፈቁትንና ሌት ከቀን ጫት በመቃም ከሰውነት ወደ እንጨትነት የተለወጠውን ወጣት ይህ ስልጣኔ እንዳልሆነ ማሳየት አለባችሁ። በዚህ ችግር ውስጥ የገቡ ሰዎችን ደግፋችሁና መክራችሁ ወደ ልማታዊ መንገድ ማምራት አለባችሁ። በማለት አሳስበው ከመድረኩ ከፍተኛ አድናቆትና ጭብጨባ ተችሯቸዋል።»

በአንድ መድረክ ላይ ወጣቱ ለሀገራችን ዕድገት በተለይም ደግሞ ወደ ኢንዱስትሪ መሪ ኢኮኖሚ በሚደረገው ሽግግር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለወጣቱ ትውልድ ያለውን ሚና አጉልተው ሲያሳዩም የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲህ ብለው ነበር፡- «በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ያሉትን ውጣ ውረዶች ተቋቁሞ ከውድቀት እየተማረ ጸንቶ መጓዝ የሚችለው መንፈስ ጠንካራ ዜጋ ብቻ ነው። የሚሰሩ እጆች ይዘን፣ የሚያስብ ጭንቅላት ይዘን፣ የወጣቱን መንፈስ ይዘን ስንዴ የምንለምንበት ጊዜ መቆም አለበት።»

አቶ መለስ በሌላ አጋጣሚ የራሳቸውን የጊዜ አጠቃቀምና ውድነት በተመለከተም ለወጣቶቹ ሲናገሩ የሚከተሉትን ሁለት ጠቃሚ መልዕክቶች አስተላልፈዋል። "ጊዜ በሰው ልጅ ቁጥጥር ስር ያልሆነ የመጨረሻ ውድ ነገር ነው። እንደ ሰው ምን ያህል ጊዜ እንዳለው አያውቅም። ስለዚህ ያለውን ጊዜ በአግባቡ

መጠቀም አለበት፡፡ በኔ ግምት ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም ሁለት ዋና ነገሮች ያሉ ይመስለኛል፡፡ አንደኛው አንድ ሰው መስራት ከሚችለው ጊዜ ውስጥ መስራት የሚችለውን ያህል በቅደም ተከተል ለይቶ ማስቀመጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቅደም ተከተል መስረት በስራ ዲሲፕሊን መፈጸም ስራውን በጊዜና በወቅቱ በተቻለ መጠን በጥራት ለመስራት መሞከር ይመስለኛል፡፡ "ክቡር አቶ መለስ ይህንኑ መልዕክት አጉልተው ሲያሳዩም" በተቻለ መጠን በጥራት ለመስራት መሞከር ይመስለኛል፡፡ እነዚህን ሁለት ነገሮች ለማሟላት ጥረት አደርጋለሁ፡፡" ይህ መልዕክት ራሳቸውን በዘላቂ ልማታዊነት ወደፊት ማራመድ ለሚፈልጉና ራዕይ ሰንቀው እየተንቀሳቀሱ ላሉ ወጣቶቻችን የህይወት መመሪያ ይመስለኛል፡፡ ነውም፡፡ በዚህ መስመር ውስጥ ገብተው ያሉ ወጣቶችን በተለያዩ አከባቢዎች የማየት ዕድሉ ስላለኝ ሳነጋግራቸው በሚያመነጩት ሀሳብና በሚያሳዩት ለውጥ ሁልጊዜ እኮራባቸዋለሁ፡፡ ይህንኑ መስመር የሚደግፍ ሁሉ እንደ እኔው ይሰመዋል ብዬ አስባለሁ፡፡

የአሜሪካ የቀድሞ ፕሬዚደንት የነበሩት ሮናልድ ሬገን በአንድ መድረክ ላይ ለወጣቶች ያስተላለፉት መልዕክት ከመጽሀፌ የትኩረት አቅጣጫ ጋር ስለሚዛመድ እንደሚከተለው አቅርቤአለሁና ያንብቡት "ወጣት ዘመዶቼ/ጓደኞቼ ታሪክ እንደ ወራጅ ውሃ ይዞን የሚሄድ ክስተት ነው፡፡ ነገር ግን እኛው ራሳችን ለራሳችን የምበጀን አቅጣጫ የትኛው እንደሆነ የመለየትና መሻገሪያችንን የመወሰን ሀይል አለን፡፡ ነፋሱ ወደ ላይ፣ ማዕበሉ ከፍ እያሉ ሲሄዱ ፍሬያማ ሲያደርጉን የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎች ደግሞ ለረጅም ጊዜ ይጠብቁናል፡፡ ያንን



የተከበረ ጉዞ በመጀመራችን ትውልድ ያከብረናል፣ባለውለታም እንሆናለን፡፡"

***የሲዳማና ጌዴኦ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብጹእ ዶ/ር አቡነ ገብርኤል ፦***

*"ሰው በእግዝአብሄር አምሳል የተፈጠረ ክቡር ፍጡር ነው፡፡ በምድር ላይ እግዝአብሄር ከፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ሰው የበላይ ነው፡፡ ሰውነትን የሚያቆሽሽ፣ የሚያደነዝዝና ክብሩን የሚያዋርድ ነገር እንዲያደርግ ቅዱሳን መጻህፍት አይፈቅዱም፡፡ እንስሳት እንኳን የሚጠቅማቸውን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ከሚበሉት ሣር መካከል የሚጠቅማቸውን እያሸተቱና እየለዩ ነው የሚበሉት፡፡ የሚያደነዝዝ ነገር መውሰድ የእግዝአብሄርን ቃል ማፍረስ ነው፡፡ ጫት የሰውን ክብር የሚያዋርድና አዕምሮን የሚያደነዝዝ ተክል በመሆኑ ሰው እንዲቅም አይደገፍም፡፡ አይመከርምም፡፡"*

የፌዴራል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌዴራልና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽኖችና የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመዲሀኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን አደገኛ መዲሀኒቶችና ዕጾች በሚያደርሱት ችግር ላይ በጋራ ህዳር 2006 ባሳፈሩት ባልታተመ ጽሁፋቸው የሚከተለውን መረጃ እናገኛለን፡፡ ይህንኑ መረጃ አለፍ አለፍ እያልን ስንመለከት ኤች አይ ቪ ኤድስን አስመልክቶ " ቁጥራቸው 850 የሆኑ (425 ከኤች አይ ቪ ጋር አብረው በሚኖሩና 425 በማይኖሩ ሰዎች) ላይ እ.አ.አ በ2005 በተደረገው ጥናት በሚቅሙበት ወቅት ከአልኮል ጋር ይጠቀሙ ስለነበረ ለኤች አይ ቪ መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል»ይላል፡፡ ጽሁፉ በመቀጠልም እ.አ.አ.በ2012 ጫት በሚቅሙ በስዊዲን ሀገር

በሚኖሩ ሶማሊያውያንና በ2005 በእንግሊዝ ሀገር በተካሄደ ጥናት "ለስነልቦናና ማህበራዊ ቀውስ እንዲሁም ለስነ አዕምሮ ጤንነት ችግር እየዳረጋቸውና ከሀገሬው ህዝብ ጋር አብሮ የመኖር ችግር እየፈጠረ ብሎም በዜጎቻቸው ላይ ችግር ማስከተል በመጀመሩ ለመቆጣጠር በእንቅስቃሴ ላይ ነው።" ይላል

ከላይ በተገለጹት (በኄ) ምልከታዎች እንደተብራራው ሁሉ በዚህም መረጃ ላይ እ.አ.አ. በ2002 የዓለም ጤና ድርጅት በጫት ዙሪያ ባካሄደው ጥናት በውስጡ ካቲን፣ ካቲኖንና ሚታካቲኖን የሚባሉ ንጥረ-ነገሮች መኖራቸውን ማረጋገጡን አስነብቦ መቃም ለልብ፣ ለምግብ ቧንቧ፣ ለመተንፈሻ አካላት፣ ለሰነ ተዋልዶ ጤና/ለስንፈተ ወስብ፣ ለኩላሊት፣ ለሸንት ፍኛ፣ ለአፍ ካንሰር፣ ለስነ አዕምሮ በሽታ፣ ለእንቅልፍ ማጣት በሽታዎች ይደርጋል።» የሚሉና ሌሎችንም አስፍሯል። በዚሁ ጽሁፍ ላይ እንደተመለከተው በሀገራችን የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት ላይ በተደረገው ጥናት 56.9% ጫት ቃሚዎች ሆነው መገኘታቸውንና ከነዚህም ቃሚዎች መካከል የወንዶቹ ቁጥር እንደሚተልቅና ወንዶቹ በጫቱ በጊዜያዊነት የማነቃቃት ሀይል ስለሚያገኙ ሴቶችን ለወሲብ በማነሳሳት ጥቃት ይፈጽሙባቸው እንደነበረም ገልጿል። ከዚሁ ጽሁፍ የቀነጨብኩትን መረጃ ከማጠቃለለ በፊት የኒዘርላንድሱ የአፍሪካ ጥናት ማዕከል እ.አ.አ "በ2013 ባካሄደው ጥናት በኢትዮጵያ በዓመት 297 ሚሊዮን የጫት መቃም ስነስርዓቶች እንደሚካሄዱ፣ 5.3 ኪ/ግ በነፍስ ወከፍ ደረጃ እንደሚቃምና የዚህም ወጪ በዓመት 6 ቢሊዮን ብር እንደሚደርስ" አመልክቷል።



## *ንግድ ሚ/ር ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ካቀረበው ሪፖርት*

***ሪፖርተር* ጋዜጣ** በእሁድ ግንቦት 24 2006 ዓ/ም ዕትሙ ክፍል 2 ገጽ 10 ላይ "የተገኘውን ጫት አለመሸጥ ሞኝነት ነው የሚመስለኝ" በሚል ርዕስ የንግድ ሚኒስትሩ አቶ ከበደ ጫኔ የበጀት ዓመቱን አስር ወራት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ባቀረቡበት ወቅት አንድ የም/ቤት አባል ያቀረቡትን ጥያቄ መነሻ አድርገው የሰጡትን ምላሽ እንደሚከተለው አስነብቧል።

በሪፖርተር ጋዜጣ ዘገባ መሠረት የም/ቤቱ አባል ያቀረቡት ጥያቄ የሚከተለው ነበር፡- "ወጣቱን እያበላሸ የሚገኘው የጫት ምርት ሊቀጥል ነው ወይ?" ጫት በገበሬው ማሳ እንዳይስፋፋ ነው መደረግ ያለበት ወይስ እንደተበረታታ እንደሄደ ነው? ካሉ በኋላ "የመንግስት አቋም ምን እንደሆነ ይገለጽ" የሚል ነበር።

ሚኒስትሩም ለጥያቄው የሚከተለውን ምላሽ መስጠታቸውን ጋዜጣው አስፍሯል፡- "ጫትን ለማበረታታት የምንሠራው ስራ የለም። ለግብርና ምርታችን የኤክስቴንሽን ሠራተኛ መድበን እናበረታታለን። ማዳበሪያና ሌሎች ግብዓቶችንም እናቀርባለን። ምርጥ ዘርም እናቀርባለን። በጫት ላይ ግን የምንሠራው ምንም ድጋፍ የለም። ግን በራሱ ጉልበት እራሱ እየቀጠለ ነው።"

"በራሱ ጉልበት ሲቀጥል እኛ እንደ ንግድ ሚኒስቴር እየሸጥን ተጠቃሚ መሆን አለብን፣ እየሸጥንም ነው። ስለዚህ መንግስት እያበረታታም፣ አያዳክምም። ለማዳከምም ብሎ አትሽጡ ብሎ ነቅሎ (ከማሳ) ያቃጠለበትም አጋጣሚ የለም። ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ለጊዜው ዝም ነው። እናበረታታም። የጫት ተጠቃሚ ህብረተሰብ ክፍል ስላለ ሸጠን መጠቀም ስላለብን እየሸጥን ነው።

ገቢውም ቀላል አይደለም። በዓመት እስከ 260 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይገኛል፣ ትልቅ አቅም ነው፣ እንሸጣለን።"

"ዞሮ ዞሮ እኛ ጫት አታምርት ብንለውም አርሶ አደሩ ወደኋላ አይልም። ሀረርጌ በአብዛኛው ጫት ነው የሚያመርተው። ሄደን ጫቱን ንቀልና ሌላ እህል ወይም ቡና አድርገው ብንል እንኳ እሺ የሚል አይመስለንም። ማሳመን መቻል አለብን አርሶ አደሩን። እሱ ላይ ሳንሰራ አሁን የተገኘውን ጫት አለመሸጥ ሞኝነት ነው የሚመስለኝ። ስለዚህ ሸጠን መጠቀም ነው።"

## *አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል።*

ጫት ለሱሰኝነት የሚዳርግ ተክል በመሆኑም ሱሱ ተጠቃሚዎችን ወዴት እንደሚያራምድና በዚህም ሳቢያ ምን ያህል ታማሚዎች በየዓመቱ ወደ አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እንደሚመጡ ለመጠየቅ ነው። ያለ ምንም ቀጠሮ በመድረስ በሆስፒታሉ ትብብር እንዲያደርጉልኝ ጥያቄ ያቀረብኩላቸው አመራሮችና ባለሙያዎች ሁሉ ሊመሰገኑ የሚገባ መሆናቸውን በዚህ አጋጣሚ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

ከሆስፒታሉ ፕላንና ፖሊሲ የስራ ሂደት ባገኘሁት መረጃ መሠረት ከ2003 እስከ 2006 የበጀት ዓመት ጫትን ጨምሮ በሱስ አማጪ ዕጾች (መዲሀኒቶችና እንክብሎች) ብቻ የሚከተሉት ህሙማን ወደ አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በመምጣት የህክምና አገልግሎት አግኝተዋል ወይም በማግኘት ላይ ናቸው።

በሀገራችን አቆጣጠር በ2003 በድምሩ 1589 ህሙማን ከሱሰኝነት ጋር የተያያዙ የአዕምሮ የህክምና አገልግሎቶችን



አግኝተዋል። ከነዚህም ህሙማን መካከል 1544 ወንዶች 45 ደግሞ ሴቶች ናቸው።

በ2004 በአጠቃላይ 3288 ህሙማን ጫትን ጨምሮ ከሱሰኝነት ጋር ተያያዥ በሆኑ ዕጾች ምክንያት የሆስፒታሉን አገልግሎት ማግኘታቸው ሲታወቅ ከነዚህም መካከል 3210 ወንዶች 78 ደግሞ ሴቶች ናቸው።

በ2005 ደግሞ በድምሩ 2049 ህሙማን በዕጾች ምክንያት የሆስፒታሉን ሙያዊ አገልግሎት ያገኙ ሲሆን ከነዚህም 1814 ወንዶች 235 ሴቶች ናቸው። በመጨረሻም ከሆስፒታሉ ባገኘሁት መረጃ መሠረት በ2006 የበጀት ዓመት (ከሐምሌ 2005 እስከ ታህሳስ 2006) ብቻ 1070 ህሙማን የሆስፒታሉን አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን ከነዚህም መካከል አንድ ሺዎቹ ወንዶች ሰባዎቹ ደግሞ ሴቶች ናቸው።

እዚህ ጋ አንባቢዎቼ ልብ ማለት የሚገባቸው ነገር ቢኖር በሱሱ ምክንያት የተጠቂዎች ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ በመምጣት ላይ እንዳለ ነው። ይህም መረጃ ደፍረው ወይም በሆነ አካል ተገደው ወደ ሆስፒታል የመጡትን ታካሚዎች ብቻ የሚመለከት ሲሆን ቀሪዎቹን ስለባዎች ቤታቸው (አከባቢያቸው) ይቁጠራቸው ማለቱ ይቀላል። በተለይም በወጣቶች ዘንድ የተጠቃሚነቱ ወሰን እንዲህ እየሰፋ የሚመጣ ከሆነ ለማታቂነት እየደበዘዘ ሱሰኝነቱ ደግሞ እያደገ እንደሚመጣ ማወቅ አያደግትም። ይህም አካሄድ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ፖሊሲ አውጪዎችን ጨምሮ ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ትኩረት ፈጥኖ መሳብ የሚገባ አይመስላችሁም? ሳይደርቅ--------- ነዋ!

አንድ ተቋም ሄጀ ለአንባቢ ጠቃሚ መረጃ አገኛለሁ ብዬ ተደጋጋሚ ሙከራዎችን አድርጌ ነበር። ከብዙ ልፋት በኋላ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ባገኝም አንዱ ወደ ሌላ እንደ ኳስ እየወረወረኝ መጫወት ሲጀምር እኔም ሰልችቶኝ እያለ አንድ ውስጥ አዋቂ ምን አለኝ መሰላችሁ "እነርሱም ራሳቸው ቃሚዎች ስለሆኑ አምንታዊም ሆነ አሉታዊ ምላሽ ስለማታገኝ አትልፋ!" አለኝ። መረጃ ሰጪውን አመስግኜ -------።

***ዶቸቬሌ***

ይህንኑ መጽሀፍ የመጨረሻ የአርትኦት ስራ በመስራት ላይ እያለሁ የጀርመን ድምጽ ሬዲዮ (ዶቸቬሌ) የአማርኛ ፕሮግራም ጁን 24/2014 ባስተላለፈው ዘገባ ጫት የእንግሊዝን መንግስት ትኩረት እየሳቡ ከመጡ ዕጾች አንዱ እንደሆነ አብራርቷል። ሬዲዮው በመቀጠልም ጫት በእንግሊዝ ሀገር በ "C" ደረጃ መፈረጁን አስረድቶ የተከሉ ተጠቃሚ ዜጎች ወደ አዕምሮአዊ ሁከት እየገቡ ያለበት ሁኔታ ስለመጣ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከሰኔ 17/2006 ጀምሮ ታግዷል፣ በርካታ ተጠቃሚዎችንም አንጫጭቷል። ብሏል

በዶቸቬሌ የዕለቱ ዘገባ መሠረትም ለመታገዱ ዋና ዋና መንስኤዎች በእንግሊዝ የተለያዩ አከባቢዎች የሚኖሩ ከሁለት መቶ ሺህ በላይ ሶማሊያውያንና የሌላ ሀገር ተወላጆች በሱሱ ሳቢያ ስራቸውን ሙሉ በሙሉ የማቆም አሊያም የማዳከም፣ የፍቺ ቁጥር መጨመር፣ ሁከት፣ የልጆች እንክብካቤ መቀነስ፣ ግለሰባዊና አከባቢያዊ ማህበራዊ ህይወት የመናጋት ቀውሶች ተጠቃሾች ናቸው። በወጣው ህግ መሠረትም በግልጽም ሆነ በስውር ጫት የሚያስቅሙ ቤቶች ስራቸውን እንዲያቆሙ ይገደዳሉ። ይዞ፣ ተጠቅሞ ወይም አስርጎ እስካስገባ ግለሰብ



ድረስ የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡ ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 14 ዓመታት ያሳስራል ብሏል። ዘገባው አክሎም አከባቢውን መነሻ አድርጎ በዕለቱ ባስራጨው ዘገባ የህጉ መውጣት ባሎቻቸው በጫት ሱስ ተጠምደው የቤተሰባዊ ህይወት ጣጣ የተጫነባቸው ሴቶች ትልቅ እፎይታ መሆኑ ተገልጾአል። በሀገራችንስ እንዲህ ዐይነት ችግር ውስጥ ያሉ ቤተሰቦችና ግለሰቦች የሉም? እስቲ ችግሩ የጋራ መሆኑን አውቀን አከባቢያችንን እንዲያውም እንድፈርና መ/ቤቶችን እንቃኝ!! ጥቂት የማይባሉ ሰለባዎች ይገኛሉና እናውጣቸው።

## *በጫት ዙሪያ ልዩ ልዩ አስተያየቶችና ገጠመኞች*

«ጫት እኛን እንዲህ አድርጎ ያስቀረን ይበቃል፤ እናንተ ወጣቶች ግን አትቃሙ:: መቃም ያለበት ሱቅ ውስጥ ሸቀጣ ሸቀጦችን እየጠቀለለ በመሸጥ የሚተዳደር ነጋዴ ብቻ ነው::» እውነቱን ልንገርህ ያሉኝ የረጅም ጊዜ ቃሚ የሰጡኝ አስተያየት ነበር::

(ጫት በሰው ልጆች ዘንድ እስከ ወዲያኛው የተወገዘ (የተረገመ) ተክል ነው:: የተወገዘበትም ምክንያት ፈጣሪ ወደ ምድር በመጣበት ጊዜ ከርሱ በስተቀር ሁሉም ዛፎች በመስገድ አምላካዊ ክብር ሲሰጡ እሱ ግን ባለመስጠቱ ዘላለማዊ ደስተኝነትን የማይሰጥ ተክል ሆኗል:: ለዚህም ዝንተዓለም በሰው ልጆች ሲትተኘክ ትኖራለህ ተብሎ ተረግሟል::)

«When god came to earth all the plants bowed before him showing their ultimate reverence.The exception was khat: a plant which stood straight with a posture of disrespect. Then god cursed-forever you be chewed by human,s.» (Anderson et.al.2007)

«ጫት ለማረስ፤ ለመሸጥና ለመጠቀም የተከለከለበት ምክንያት የሙሲሊሞችን አዕምሮ፤ ሀይማኖትና አካል እንዲሁም ገንዘባቸውን በማባከን ሱሰኛ ያደርጋል::» *ሼክ መሀመድ ኢብን ኢብራሂም የሰውዲ ዐረቢያ ምሁር::*

«ነቢዩ መሀመድ የሚያሰክር መጠጥና ሱስ አማጭ ዕጽ ከልክለዋል፣ ምክንያቱም ገንዘብ፤ ጊዜ፤ የመሬት አጠቃቀም ብክነት እንዲሁም ማህበራዊ፤ አካላዊና ስነልቦናዊ ቀውስ



ያስከትላልና::» አይሻ ሰይድ በዩ ኤስ አሜሪካ Griffth university ባልደረባ::

«የወንዶቹ መቃም ከመጠን በላይ አለፊ እያልን በመጨነቅ ላይ እያለን ሴቶቹ ደግሞ ጫት በመቃምና ሺሻ በማጨስ የዕጩ ተወዳዳሪነት ሪከርድ በመስበር ላይ ናቸው:: በለቅሶ ቤቶች፤ በባህላዊ ስነስርዓት ማካሄጃ ድንኳኖች በአራቱም ማዕዘን የተተከሉ የሚመስሉ ሺሻዎች የሚያስተጋቡት ድምጽ የሚሳየል እሩምታ ይመስላል:: » ከመሃል ሀገር ወደ ምስራቅ ለቅሶ ጎራ ያለ እንግዳ::

አስተማሪና አዝናኝ ገጠመኞች በብዙዎቹ የሀገራችን አከባቢዎች በተለይም ህዝብ በሚበዛባቸው ስፍራዎች በተጨባጭ የምናስተውላቸው ክስተቶች ናቸው:: በአራቱም ማዕዘናት ጋያዎች ወይም ሺሻዎች ተተክለዋል:: በመዋጮ ከሰል ይገዛና በምድጃ ይያያዛል:: ፍም ከሆነ በኋላ ወደያንዳንዱ ጋያ (ሺሻ) የሚያድል ሰው ይመደባል:: ጭንቅላት የሚነቀንቅ ራስ ምታት እስከሚከሰት ድረስ ጭሱ በአፍ ይሳብና በአፍንጫ ይለቀቃል:: የጭስ መውጫ እንደተበላሸበት ትሬንታ ኩዋትር (እንደ ቀድሞው የድሬዳዋ- ጂቡቲ ዕቃ ማመላለሻ ባቡር) በአፍና በአፍንጫ ወደ ላይ ይተኮሳል:: ሺሻው ሲሳብ በአናቱ ላይ የተቀመጠው የከሰል ፍም ባህላዊ እስክስታ የሚጨፍር ዳንኪረኛ ይመስላል:: ፍሙ አንዳንዴ ወደ ላይ ይዘላል፤ አንዳንዴ ደግሞ እዛው እንደተጣበቀ እስክስታ ይወርዳል:: ከት ብሎ የሚስቅም የሚያሾፍም ይመስላል:: ጠረኑ ደግሞ የክብር ዘብ ይመስል ወደየሄዱበት ቦታ ሁሉ አብሮ ይሳፈራል ይዘልቃልም:: አንዳንዶቹማ እንዲያውም ጫት እየቃሙ ሺሻውን ሲያንቋርሩ ፊታቸው ሁሉ ማበጥና ሁለመናቸው መቅበጥበጥ ይጀምራል::

በአንዳንድ የገጠር አከባቢዎች አርሶ አደሮች ኢ-ጀበና (የዐይን መገለጫ) ነው በማለት ጫትን እንደ ጠዋት ቁርስ መቃም ይጀምራሉ:: መቃም ብቻ ሳይሆን አቃቃማቸው ያስፈራል:: መጠኑ በትክክል የማይታወቀው ያህል በርጫ ይጠራረድ ይወራረድና የጨዋታ አሊያም የመሬት ውስጣዊ ብልት የመተርተር ስራ ይጀመራል:: ለንፋስና ለብርድ በተጋለጠ ሰውነት ስራው ከተጀመረ በኋላ የተጀመረውን መጨረስ እንጂ ማቆም የሚባል ነገር አይታሰብም:: በዚህም የተነሳ ለህይወታቸው ጥንቃቄ ባለማድረግ ለሳምባ በሽታ የሚጋለጡ ጥቂቶች እንዳልሆኑ ሀኪሞች ያወያየሁአቸው አጫውተውኛል::

በጫት ከተመረቀነ በኋላ በተለይም በግብርና ስራ ላይ ጥፍር ቢቆረጥ፤ እግር ቢቆስል ወይም ሌላ የሰውነት ክፍል ቢደማ ፈጥኖ ላይታወቅ ይችላል:: ምርቃናው በራሱ ጊዜ እየወረደ ካልመጣ ድካምም አይታወቅም ያሉ አስተያየት ሰጪዎች አጋጥመውኛል:: አንዳንዶቹ የሚላቀቁት «አረ ይብቃችሁ!» ተብለውና ተለምነው ነው:: ደም ስር ውስጥ ዘልቆ በመግባት አስፍቶ ይዘዋወር የነበረው የጫት ሃይል (ምርቃና) እየቀነሰ ካልመጣ ድካም አይስተዋልም:: የሁልጊዜ ክስተትም ባይሆን ተቆርጦም ሆነ ቆስሎ እንደሆነ የሚታወቀው ጠዋት ምርቃናው ሲለቅና ከእንቅልፍ የሚያስነሳ ራስ ምታት በተራው ጭንቅላትን መቆጣጠር ሲችል ብቻ ነውም ያሉኝ አሉ::

በከተማ ደግሞ የጫት ሱሰኛ የሆኑና መለስተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ከቀን ወይም ከወርሃዊ ገቢያቸው ከቤተሰባቸው ይልቅ ወደራሳቸው ያደላ ክፍፍል ያደርጋሉ:: ከዕለቱ የምሣ ወጪ አብዛኛውን ለጫቱ ይመድቡና በባዶ ሆድ ማለት ይቻላል «ወፍራም» በርጫ ይዘው ወደ ቤት አሊያም ወደ ሌሎች የጫት መቃሚያ ስፍራዎች ይሄዳሉ:: አቤት ያቺ ሰዓት! በተለይ ጫት



የተወደደበት ወቅት ከሆነ የገኘ/ው ኩራት አይጣል ነው:: ከመወደዱ የተነሳ የሀረር ሰንጋ እንደተገዛ ነዋ የሚቆጠረው! . . ሌሎቹ ደግሞ የአቅምቲ ያህል ጫት ከገዙ በኋላ ቪላ እንደሰሩና ቮልቮ እንደገዙ አድርገው ይቆጥራሉ:: ብቻ በዚያ ሃራራ (አፍላ) ሰዓት «በርጫን አያሳጣ!» ነው መፈክሩ ሁሉ:: ሌላ ሁሉ ከዚያ በኋላ ይታሰባል:: ብቻ በርጫ አይጥፋ ነው ዘፈኑ!!

በገጠር አንድ በግብርና ሙያ አንቱ የተባለ አርሶ አደር እህል ሲወቃ ይውልና ምርቱን ወደ ቤቱ ለማመላለስ በአህያ ይጭን ነበር አሉ:: በማመላለስ ላይ እያለ የአህያው ሸክም ወደ አንድ ወገን እያጋደለ ያስቸግረዋል:: አርሶ አደሩ ገመድ መተብተቡ ከምርቃና ጋር ተደምሮ ይሰለቸውና ወደ አንድ ወገን እያጋደለ ከሚያስቸግረው ጭነት ለመገላገል መሸከም አይቀልም? ብሎ በመወሰን ሸክሙን በሙሉ ራስ ተሸክሞ በማንጓዝ ወደ ቤቱ አድርሶ ጨርሷል እየተባለ የሚነገርበት አከባቢም አጋጥሞኛል::

ቀጣዩ ገጠመኝም ከወደ ገጠር የተገኘ አፈ-ታሪክ መሆኑ ይታወቅልኝ:: ሰፊ የእርሻ መሬት ያለው አርሶ አደር ነበረ አሉ:: መሬቱን አርሶና አለስልሶ ካበቃ በኋላ ሰፊ ማሳ ላይ እህል ሊዘራ ይዘጋጃል:: እርሻውን ለመገልበጥ ጥማድ በሬ በመጠቀም ላይ እያለ አንዱ በሬ ብዙ በማረሱ ይደክምበትና እርሻውን ገልብጦ መጨረስ ያቅተዋል:: አርሶ አደሩ በምርቃና ስሜት ልጆቹን ይጠራና የደከመውን በሬ ፍቱልኝ ይላቸዋል:: ሁኔታውን ለጊዜው ያልተረዱት ልጆቹ በሬውን ይፈታሉ:: አባትየው በተፈታው በሬ ምትክ በአንገቱ ላይ ቀንበር አስገብቶ መሬቱን ማረስ ሲጀምር ሰዉ ከያለበት ተጠራርቶ አስጥሎታል ይባላል:: ለበሬ ማዘን ወይስ የምርቃና መዘዝ ! እያዝናናም?. እንዴታ!



*እያስተካከሉም ራስን ማስተካከል!*

ለበርካታ ዓመታት ከጫት ሺያጭ ተጠቃሚ የሆነ ሌላው አርሶ አደር ነበር። ጫቱ እያረጀ ሲመጣ ይጎነደልና ከስሩ አዲስ እንዲበቅል ይደረጋል። አርሶ አደሩ ለዚሁ ዓላማ እየቆረጠ ከሚጥለው ቅርንጫፍ ላይ ደስ ያለውን እየመረጠና እየቀነጠሰ ሲቅም ውሎ ማታ ራት ብላ ተብሎ ቢለመን ቢለመን አሻፈረኝ ብሎ ይተኛል። ሌሊት በተኛበት ሲያቃስት ቤተሰቦቹ ይሰሙና ምን እንደነካው ሊጠይቁት ሲቀሰቅሱ «ወይኔ ዘመዶቼ! ወይኔ ዘመዶቼ!» በማለት ቤቱን በጩሀት እንዳናጋ ከቤተሰቦቹ እንደበት የተነገረለት ሰው ያጫወተኝ ሲሆን ይህም ከምርቃና መዘዞች አንዱ መገለጫ ነው።

በዕድሜ ገፋ ያሉ አዛውንት ናቸው አሉ። መደብ ላይ ትራስ በግራ እጃቸው ደገፍ ብለው ይበረጭጫሉ (ይቅማሉ)። ባለቤታቸው የቤታቸውን ጣጣ ለማጠናቀቅ ጓዳና ሳሎን እያሉ



ስራ ላይ ተጠምደዋል። እኚሁ አዛውንት ብቸኛ የምትታለብ ላም አቤታቸው ነበረቻቸው። እናቲቱ ላም ጥጃዋን ማጥባት ስለፈለገች ከጥጃዋ ጋር ይጠራራሉ። አዛውንቱ ለካስ በጣም መርቅነው ባለቤታቸውን እነዚህን ከብቶች አስታግሽልኝ ብለው ኖሯል። ባለቤታቸውም ትኩረታቸው ወደ ጓዳ ሥራቸው ነበርና ተማጽኖአቸውን አልሰሙም። አዛውንቱ ላምትዋ ደጋግማ ስትጮህ በመረበሻቸው ተናደዱና አጠገባቸው የነበረውን ሜጫ (መቁረጫ) ብድግ አድርገው ሁለቱንም እናት እናታቸውን በመምታት ከገደሉ በኋላ ከምርቃና ዓለም ነቅተዋል። ይህም ትክክለኛ ገጠመኝ መሆኑ ቃሚዎች እርስ በርስ ሲተራረቡ የሚጫወቱት አሳዛኝ ቀልድ ነው።

ዜግነቱ የዐረብ ተወላጅ እንደነበረ የሚነገርለት አንድ ሰው በሃገራችን ይኖር ነበር። ማሾ አብርቶ ያለ የሌለ ገንዘቡን ቆጥሮ ካበቃ በኋላ ገንዘቡን፣ ማሾና የሣጥኑን ቁልፍ በአንድ ሣጥን ውስጥ አስገብቶ መብራቱን ሳያጠፋ ቆልፎ ይተኛል። በማግስቱ ተነስቶ ቁልፉን ፈልጎ ያጣና ባለቤቱን ከደበቅሽበት አምጪ ብሎ አምባጓሮ ይፈጥራል። አልወሰድኩም ብላ ባለቤቷ ለማሳመን ብትሞክርም መተማመን አልቻሉም። በመጨረሻም ጉዳዩ ወደ ፖሊስ ጆሮ ይደርስና ሣጥኑን ይዘው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይሄዳሉ። የሣጥኑ ቁልፍ ተሰብሮ ሲታይ ቁልፉ በአንድ ጥግ ወድቋል። ማሾው ደግሞ ፈንድቶና ሁለት መቶ ሺህ ብር እንደተጠቀለለ አመድ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚያም በድንጋጤ ባለቤቱን ይቅርታ ጠይቆ ከዚያን ቀን ጀምሮ ጫት መቃም አቆመ ይባላል።

የሚቀጥለው ታሪክ ደግሞ ውጭ ሀገር ይኖሩ በነበሩ ሁለት ሶማሊያውያን ወጣቶች መካከል የተፈጠረ ክስተት ነው። ሁለት

ሶማሊያውያን ወጣቶች የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ከእርስ በርስ ጦርነቱ ለትንሽ ቀደም ብለው ወደ አንድ የሲዊዲን አነስተኛ መንደር በመግባት እድለኛ ይሆናሉ:: በሁለት ዓመታት የሲዊዲን ቆይታቸው ህይወታቸውን በጋብቻ ያለምንም ችግር ሲመሩ ይቆዩና በመካከሉ አባወራው በሀገሩ አድርጎት የማያውቀውን ጫት በጓደኞቹ አስለማጅነት በወር አንድ ጊዜ፤ በአስራ አምስት ቀን አንዴ፣ ወዘተ-----እያለ በየቀኑ መቃም ይጀምራል:: ጫትን ተከትሎ ማጨስም ጀመረ:: ሌሊቱን በሙሉ እየቃመ ስለሚያድር ቀን ይተኛል:: በዚህም ልጆቹን መንከባከብ እየቀነሰና እየቀረ ይመጣል:: ከስራ ዓለምም ተሰናበተ:: የቤተሰብ ማስተዳደር ሃላፊነትም በባላቤቱ እጅ ብቻ ወደቀ:: እንደዚያም ሆኖ በዚያው ዓቅሙ ጫት በማያገኝበት ቀን ከባለቤቱ ጋር ብቻ ሳይሆን ከልጆቹ ጋር ሳይቀር መነጫነጭና ራሱን መጣል ጀመረ:: ባለቤቱ ብቸኝነት ብቻ ሳይሆን የመላ ቤተሰቡ ሃላፊነት በሷ ጫንቃ ላይ ወደቀባት:: በመጨረሻም ሚስትየዋ ከጫት ወይም ከቤተሰብ አንዱን እንዲመርጥ በአከባቢው ህግ መሰረት ጥያቄ አቀረበችለት:: የሱም ምርጫ ጫት ሆነና:: ትዳራቸው ፈረሰ:: እሱም የዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ ጫት መሆኑን መረዳት ባለመቻሉ ቀውስ ሆኖ ቀረ ይባላል::

የሚቀጥለው ክስተትም እዛው ሲዊዲን ሀገር በሶማሊያውያን ቤተሰቦች መካከል የተፈጠረ ነው:: ሁለት ልጆች ያሏቸው ባልና ሚስት በሶማሊያ ይኖሩ ከነበረበት በጦርነት ምክንያት ወደ ስዊዲን ሀገር ይሰደዳሉ:: ባልየው ወደዚያ ከመሰደዱ በፊት ጫት ቃሚ ሲሆን እስዋ ደግሞ ጨርሶ ቀምሳ አታውቅም:: እሱ መቃሙን አጠናክሮ በመቀጠሉ የተነሳ ማህበራዊ ህይወቱ ወደኋላ መንሸራተት ጀመረ:: በየጊዜው ወደ ጓደኞቹ እየሄደ



በመቃም ያስቸገረውን ባለቤቷን ለማስጣል መፍትሄ ያገኘች መስሏት (የቸገረው ዱቂት ከንፋስ ይጠጋል እንዲሉ) እርስዋም ከርሱ ጋር እቤት ውስጥ መቃምና ማስቃም ጀመረች:: እየቆየ ሲመጣ ደግሞ ራስዋም የሱሱ ሰለባ ሆና ቀረች:: ከዚያም የባለቤትዋን አትቃሚ ምክር ልትቀበል ፈቃደኛ ባለመሆንዋ የሱን ቤተሰባዊ ድጋፍ አጣች:: በዚህም ራስዋንና ልጆችዋን በአግባቡ መንከባከብ አልቻለችም:: ባለቤትየው ራሱ በፈጠረው ችግር ጋብቻው ፈረሰና ወደ እንግሊዝ ሀገር ኮበለለ:: በአስራዎቹ የእድሜ ክልል የሚገኙ ልጆቻቸው የእናታቸውን ፈለግ በመከተል ጫት መቃም ብቻ ሳይሆን ሲጋራ ማጨስ ጀመሩ:: ሴት ልጃቸው ትምህርትዋን አቋርጣ ወደ ዝሙት አዳሪነት ስራ ገባች:: በጥቅሉ በጫት መዘዝ ቤተሰብ በአሳዛኝ ሁኔታ ተበተነ::

ሌላ ገጠመኝ ደግሞ ላጋራችሁ:: ሰውየው ቀኑን ሙሉ ሲቅም ይውልና መላ ሰውነቱ በምርቃና ትኩሳት ግሏል:: የደም ዝውውሩ እየፈጠነ ነው:: ጭንቅላቱም እንደ ገደል ማሚቶ ጩሃት እያስተጋባ ነው:: ነጩ ጥቁር፤ ጥቁሩ ደግሞ ብጫ ሆኖ የሚታይበት ወቅት ነው:: እየቀነጠሰ ወደ እግሩ የሚወረውረው ገራባ ጣቶቹን ሸፍኗቸዋል:: በዚህ ወስዋስ (ግለት) ውስጥ እያለ ወደ ጣቶቹ አየት ሲያደርግ አውራ ጣቱ ትንቃንቃለች:: እሷም የሰውነቱ አንዷ አካል ስለሆነች ከበርጫው የድርሻዋን ወስዳ ኖሮ መርቅናለቻ! የጣቱን ንቅናቄ በምርቃና ሃይል ካስተዋለ በኋላ እባብ በገራባ ውስጥ እየተሳበ የመጣ መስሎት በጥንቃቄ አጠገቡ ያለውን ሜጫ (መቁረጫ) አንስቶ ጣቱን ቀንጥሶ ጥሏል:: ከጊዜ በኋላ ድርጊቱ ምን ያህል አሳዛኝ ክስተት እንደሆነ ራሱን ኮንኖ ከሱ ሌሎች እንዲማሩ መክሯል::

ብቸኛ የእርሻ በሬውን አርዶና ገፍፎ ከጨረሰ በኋላ ድርጊቱ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን ህይወቱን ያጨለመበት መሆኑን የተረዳ አንድ አርሶ አደር በምስራቅ ኢትዮጵያ እንደነበረም አንድ የጫት አፍቃሪ የሆኑ መምህር አጫውተውልኛል።

የአፋር መንፈሳዊና ባህላዊ አባት የነበሩት ሡልጣን ዓሊሚራህ «ኢትዮጵያን እየተፈታተናት ያለው ትልቁ አደጋ ጫት ነው። በቤተሰብ ገቢ ላይ ትልቅ አደጋ አለው። ጤናን ያቃውሳል። ለልማት ዐይነተኛ ሃይል የሆነው ወጣት በጫት ሱስ ከተጠመደ ስንፍና እየተጠናወተው የመንግስትን ኢኮኖሚያዊ አቅም ያሽመደምዳል።» ማለታቸውን *ከሀረሪ ክልል ሲቪል ሴርቪስ ቢሮ በ1987 ያገኘሁት ያልታተመ ጥናታዊ ጽሁፍ አመልክቷል።* የጫት ገጠመኞች እንደየሰው ሁሉ በዐይነትም ሆነ በመጠን ይለያያል።

የቀጣዩ ገጠመኝ ባለቤት ለዓመታት በሀረር ከተማ የኖረ ሰው ነው። ከአንድ የአፍሪካ ሀገር ኤምባሲ ወደ ሀረር ከተማ የመጡ እንግዶችን እንዲያስጎበኝ ሃላፊነት ተሰጥቶት በድፕሎማት መኪና አብሮአቸው ይንቀሳቀሳል። የከተማውን የተወሰነ አከባቢ ቀን ሲያስጎበኝ ውሎ ማታ በመቀጠል ከእንግዳው ጋር እየተዘዋወሩ ከተማውን በማየት ላይ እያሉ መጠምዘዣ መንገድ ሲደርስ እንግዳው ራሱ ሾፌር ነበርና አቅጣጫ ለመቀየር ፍሬን ሲረግጥ ከኋላ በበሩት የፍሬቻ መብራቶች ላይ ሮጦ ሲጃራ ለመለኮስ የመጣ የመንገድ ላይ ቃሚ አጋጥሞታል። እንግዳው በሁኔታው ተደናግጦ እንደነበረም ያስታውሳል።

ሃዋሳ ከተማ ላይ እየተዘዋወሩ ከተማውን ይጎበኙ ከነበሩ የውጭ ሀገር ዜጎች መካከል አንዱ ሲጃራ እያጨሰና ግራና ቀኝ እየተመለከተ ይሄዳል። መንገድ ላይ ቁጭ ብሎ ጫት



ከሚቅምበት በፍጥነት ተወርውሮ ከፈረንጁ እጅ ሲጃራውን የነጠቀ ቃሚም የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ገጠመኝ ነው።

ከባልደረቦቹ ጋር ጫት ሲቅም ውሎ መሸት ሲል ጨብሲ (መጠጥ) ከጠጣ በኋላ ዝግጅቱን ለህዝብ የሚያቀርብበት ሰዓት ሲደርስ ዞሮበት ቃሪያና ቲማቲም እንዲበላ ከስራ ባልደረቦቹ ተመክሮ በብዛት ከበላ በኋላ በይሉኝታ እየተቃጠለና በውስጠ ተዋቂነት ኡኡ የማለትን ያህል እየጮሄ የዘፈነውን የአንድ ድምጻዊ ታሪክ አዲስ ልሳን ጋዜጣ አስነብቧል።[27]

አንድ የሃይማኖት አባት በእስልምና ሃይማኖት ጠለቅ ያለ ዕውቀት በሌላቸው ሰዎች ጫት ለሃይማኖቱ ተከታዮች እንደ መለያ ተደርጎ የተቆጠረበት ጊዜ እንደነበረም አጫውተውኛል። በጫት ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶችን ለማካሄድ ባደረግኩት ጥረት ሙስሊም ሆኖ የማይቅም ሰው ቢኖር እውነተኛ የሃይማኖቱ ተከታይ እንዳልሆነ ለማሳመን የሚቃጡ ጥቂት ሰዎችም አጋጥመውኛል። የሚገርመው ነገር አንዳንዶቹ «አላህ» ራሱ ስንደል ለኩሶ፤ ዕጣን አጭሶ፤ ሣር ጎዝጉዞና ጉንጩን አሳብጦ ቁጭ ብሎ ይቅም ነበር ለማለት የሚቃጣቸው መኖር ነው። የሀይማኖቱ ተከታዮች ሆነው ጨርሶ የማይቅሙ እጅግ በርካታ ሰዎች መሆናቸውን እውቃለሁ። ክርስቲያን ሆነው ከሙስሊሙ የበለጠ የሚቅሙ ግለሰቦችና የሚቃምባቸው አከባቢዎችም ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ፈጣን "ዕድገት" አሳይቷል። ይህ የሚሆነው በአብዛኛው በከተሞችም በገጠርም እየሆነ መጥቷል።

ጫት በሚዘወተርባቸው አከባቢዎች በርጫ መጋበዝ ከመስቀል ስንጋ፤ ከፋሲካ ፍሪዳ፣ ከስኮትሽ ውስኪ፤ ከራሺያ ቮዲካ፤ ከፈረንሳይ ሻምፓኝ... ወዘተ የበለጠ ክብር አለው። በአንዳንድ አከባቢዎች ላብላህ ላጠጣህ ከማለት ይልቅ በርጫ ልጋብዝህ

ማለት ልዩ ትርጉምና ክብር ይሰጣል። የመቃም ስርዓቱን ለማድመቅም አስቀድሞ ሻወር ይወስዳል። ንጹህ ልብስ ይለበሣል። ሽቶ ለራስና አብረው ላሉ ሁሉ ይርከፈከፋል። ዕጣን ይጨሳል፤ ሰንደል ይለኮሳል፤ እጅ ይሳማል። ይጨበጨባልም። እንደየሀይማኖታቸው ስርዓትም አማልክትን ይጠራሉ፤ ይማጸናሉ፤ ያ አላህ! የመላዕክት ያለህ፤ ብቻ የሁሉም ቅዱሳን ስም በአማላጅነት ይነሳል። አማልክቶቹ አማርኛ የማይሰሙ አሊያም የማያውቁ ይመስል አረብኛም ማጣፈጫ ሆኖ ይገባል።



ይሀው! ወስነህ ግባበት የነጋዴው ማስታወቂያ! (ፎቶ ከድህረ-ገጽ)

ብቻ ሁሉም አማላጅ እንዲሆኑ ተማጽኖ ይቀርባል። ዋስ እንዲሆኑ ይጠራሉ። ዳግም ክፋት ሳለመስራት ቃል ይገባል። ብቻ ብዙ ብዙ ቁም ነገሮችን ለመስራት ዕቅድ ይነደፋል። በምርቃና ሰበብ ዛሬ ተገንብቶ ነገ የሚፈርስ ፎቅ ይገነባል። በማግስቱ በደህና ቡጢ የተመታ ቦክሰኛ ይመስል መዘረር ይመጣል። ራዕይ፤ ቅዠት ወይስ ወቅታዊ ትኩሳት? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። በርጫ ዐይነቱና ብዛቱ እንደየአከባቢው ብዙ የመሆንን ያህል በቃሚዎች ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖም የዚያኑ ያህል ይለያያል። ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ የገዙትን



በርጫ በፌስታል ይዘው ሲሄዱ የስጋሌ ጦር ሜዳ ዘማች ከጀርባው የተረፈውን ስንቅ በእጁ አንጠልጥሎ ይ፡፡ የሚሄድ ይመስላል። በተለይ ጫቱ ተወዶ የመግዛት አቅም እየተዳከመ በሚመጣበት ወቅት ገንዘብ ያላቸው የመስቀል ሰንጋ እየነዱ የመጡ ይመስል ይኩራራሉ፤ አሊያም ላለማሳየት የማያደርጉት ጥረት የለም። አንዳንዶቹ ደግሞ በድርጅታዊ ዲሲፕሊን እንዳይቅሙ የተከለከሉ ይመስል አመሳስለው ይይዛሉ። አይቅሙም እንዲባሉም ይደብቃሉ። በተለመደው አባባል ዐመልህን በጉያ ስንቅህን በአህያ እንዲባል ነዋ!! ሌሎቹ እንዳይጋሩም ገና ከመግዛታቸው ፊታቸውን ኮስተር ማድረግ የሚጀምሩ አሉ። ወፍራም ገንዘብ ከኪሳቸው እያወጡ በማሳየትና በሚገዙ ሰዎች ፊት በመቁጠር የሚንጎራደዱም ዘመነኞች በርካታ ናቸው።

በርጫው እየተወደደ ሲመጣ ሻጮች በበኩላቸው በተለይም ደግሞ ሴቶች የደንበኞቻቸውን ኪስ በረጅም ርቀት በአጉሊ መነጽር የመለካት ልዩ ብቃትና ተሰጥኦ አላቸው። ጫት ሲረክስ ደግሞ አቅም በማጣታቸው ችላ ያሏቸውን ደንበኞች የት ጠፋህ? ---በማለት በሩቁ እየጠሩ ማግባባትና ደንበኝነትን ማደስ፣ ማወደስም ይጀምራሉ። የአቃቃም ስርዓትም እንዲሁ እንደየአከባቢዎቹ ይለያያል። አንዳንዶቹ ዐይን የሚማርኩ ትራሶችንና የትራስ ጨርቆችን፤ ምንጣፍ፤ ቁጤማ፤ ወዘተ በማሳመር አንጥፈው ይቅማሉ። እነዚህ ቃሚዎች የሚጋበዙ እንግዶችን ገና ከጅምሩ በማግባባት ይማርኩና በቀጥታ ወደ ሱሰኝነት ጎራ ያስገባሉ። ይደባልቃሉ ልበል ይሆን? ባያስገድዱም የእንግዳውን አእምሮ የሚጫን ስንቅ ሰንቀው ወደ መጣበት ይልካሉ። ሌሎቹ ደግሞ ጫት ይሁን እንጂ በረንዳ ላይ

ወይም አልጋ ላይ ቁጢጥ ብለውና ዐይናቸውን ፍጥጥ አድርገው ወደ ምርቃና (ሰመመን) ጉዞ ያደርጋሉ ።
ከፊሎቹ በየዛፉ ጥላ ስር፤ በየመንገዱ ዳር፤ በየመናፈሻው፤ በየጫት መሸጫ ቤቶች ጓዳዎች፤ ወይም ደግሞ እንደ «ቃልቻዎች አደባባይ» ለነርሱ ብቻ በተጠበቁ ይዞታዎች በመቃም ይመረቅናሉ። ቁምነገሩ ጫት ይሁን እንጂ ቦታና ጊዜ የማይመርጡ ሁሉ አሉ። ከጫት ጋር «አብሮ አደጎች» የሚመስሉ ደግሞ ፈረንጆችን ቼኮሌትና ከረሜላ የመሳሰሉ ጣፋጭ ነገሮች ጥርሳቸውን ቦርቡሮ የጨረሰባቸው ይመስል ማኘክ ያቅታቸውና የጥንቱ ሩቅ ዘማች አባት ጦር ይመስል እንደ ቋንጣ አድርቀውና ፈጭተው በሻይ ቅጠል መልክ ይጠቀማሉ።

በሀገራችን በጫት ንግድ ላይ በአብዛኛዎቹ ከተሞች ወንዶች በገጠር ደግሞ ሴቶች ይሰማራሉ። የገጠር ጫት ነጋዴ ሴቶች በተለይም በክረምት ያሳዝናሉ። ዝናብ በላያቸው ላይ እየወረደና ፋኖስ (ማሾ) ይዘው እስከ ሌሊቱ አራትና አምስት ሰዓት ድረስ ሜዳ ላይ በብርድ ይሰቃያሉ። ለዚህም ምክንያቱ ያልመረቀነ ወይም ምርቃናው ጣሪያ ላይ ስሜቱን ያንሳፈፈው ወይም በሚወደድበት ጊዜ መሸት ሲል ይረክሳል ብሎ አድፍጦ ስጠብቅ ያመሸው ገዥ እስከሚመጣላቸው እንዲሁም አድሮ እንዳይበላሽባቸው ቆይቶም ቢሆን ሸጦ ለመጨረስ ነው። ሰው አቅም ሲያጣ ወይም በሌሎች ምክንያቶች ገዢ ሲጠፋ ነጋዴዎቹ «ክትፎ» የሆነ ጫት አለና ቤት እንሳከላችሁ ወይም ውሰዱ እያሉ ለደንበኞች ዛሬ የሞባይል ጥሪም ይደረግላቸዋል። ዛሬ ዛሬ «የዘመናችን የሰለጠነ ባህል» ሆኖ ጫት ወደ ቤት የሚሄድላቸው ሲረክስ ብቻ ሳይሆን ሲወደድም ነው። ለደንበኞቻቸው በተለይም ፈርጠም ያለ ጡንቻ ላላቸው ከጫቱ



ዋጋ ተጨማሪ ጉርሻ በሚሰጣቸው መልዕክተኞች ወደ ቤት ይላካል፡፡ እነዚህ ቃሚዎች ጫቱን በጣም ቢወዱም ቃሚ ላለመምሰል የማያደርጉት ጥረት የለም። ጫት ተራ መገኘት ወይም መታየት አይፈልጉም። ራሳችን መርጠን ካልገዛን እርካታ አናገኝም የሚሉ ዘመነኞችም ብዙ ናቸው። ብቻ ጫት ብዙ ጣጣ አለው። ከጣጣው ጋር አብሮ መጓዝም ይከብዳል።

የአቅርቦት ማነስ በሚታይባቸው የበጋ ወራቶች ደግሞ ሻጮች ኩራታቸው አይጣል ነው። ካሉት ዋጋ ፍንክች አይሉም። ድርድርም አይፈልጉም። የባርጫውን ዋጋ ሲናገሩም የገገርውን አለባበስና ቁመና በጥንቃቄ እያስተዋሉ ነው። ሚዛን ላይ ባያስቀምጡም ኪሱን በተቻለ መጠን በመነጽር ያያሉ። አፍዝዘውና አደንዝዘው ብሯን ለመውሰድ ሲሉ የዋጋ ክርክር አይዋጥላቸውም። በባርጫ ግገርና ሽያጭ አሳህ ክርክር አይወድም እስከ ማለት ይጋፈጣሉ። ታዲያ በዚህን ሁሉ ወከባ ሻጮቹን ኪስ አውላቂዎች ናቸው ወይስ ነጋዴዎች እያሉ መግዛት ወይም መሸሽ ነዋ!!። እንደነርሱም ብልጥ መሆን ነዋ ጃል!! በይሉኝታ ኪስዎን ካራቆቱም ምርጫው የግልዎ ነውና እኔን ምን አገባኝ።

አንዳንዱ በርጫ ከቃመ በኋላ ይተክዛል። ጭልጥ ያለ ሀዘን ውስጥ ገብቶ ምርር ብሎ የሚያለቅስም አለ። የሚያስለቅሰው ነገር ምን እንደሆነ ቢጠየቅ መልስ የለውም። እስለቃሹን ምክንያት በውስጡ የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው። ገና ድሮ ሳያውቃቸው በተፈጥሮ ህግ ምክንያት የሞቱ ዘመዶች ሁሉ በዐይነ-ህሊናው ይመላለሳሉ። አንዳንዱ ጭልጥ ባለ ፍልስፍና ውስጥ ይገባል። ክርክር ብነሳ መርታትን እንጂ መረታትን ፈጽሞ አይቀበልም። ከት ብሎ በሳቅ የሚንከተከትም አለ። ከደስታው ብዛት ፊቱ ሁሉ ይበራል። ምርቃናው እየበረደ

ሲመጣ ግን ፊቱ ሁሉ ይጠወልጋል። አንዳንዱ ደግሞ ሰው ሲያይ ማናገር ይደብረዋል። ፍርሃቱ አይጣል ነው። ነፍሱን በጣም ይወዳታል። የማይነገሩና የማይጋገሩም አሉ። ከመናገር ይልቅ ጥርስ መፋቅና ጥፍርን በቢለዋ ሳይቀር መከርከም ይቀናቸዋል። በማግስቱ ደግሞ ይነጣሉ ወይም ይጠቁራሉ። አንዳንዶቹ እምንታዊ (optimist) አንዳንዶቹ ደግሞ አሉታዊ (pessimist) ነገር አሳቢ ይሆናሉ። ከዚህ ዓለም መጥፎ ሰዎችና አመለካከቶቻቸው ለምን አይጠፉም በማለት የመረረ ሀዘን ላይ ይንሳፈፋሉ። በጥቂቱ ለበቀል የሚነሳሱም አሉ። እንዲያውም ካላጠፋሁ ወይም ካልጠፋሁ ይላሉ። (በበርካታ ምልከታዎቼና ቃለ ምልልስ ወቅት ጫት ለበቀል እንደማያነሳሳ ያረጋገጡልኝ አሉ።) ይሁን እንጂ ቃሚ ባልሆኑ ላይ አቃቂር የሚያወጡም አሉ። ሚርቃናው እንደ ፍል ውሃ እየተንተከተከ ሲመጣ ከንፈር የሚነክሱ፣ ጥርስ የሚያፏጩ፣ ጥፍር የሚከረክሙ፣ ጥርስ እስከሚነቃነቅ ድረስ የሚፍቁ አሉ። በዚህን ጊዜ በምርቃናው ሰበብ ነጭ ላብ ብቻ ሳይሆን የላቦች ሁሉ ጭማቂ ላብ ይንቆረቆራል። ለዚህም ኬብን ራሽቢ ጫትን አስመልክቶ ከጻፋቸው አስተያየቶች መካከል ፡-

«ህጋዊና ህጋዊ ያልሆነ፣ አስተማማኝና አስተማማኝ ያልሆነ፣ በድምበሮችና ወሰኖች ውዝግብ ፈጣሪ፣ ሱስ አማጭም አማጭም ያልሆነ፣ ሌሊቱን በሙሉ እያስደነሰ የሚያሳድር፣ አደንዝዞ የሚያስቀምጥህ፣ ፍጥጥ አድርጎህ የሚያሳድርህ፣ በሌለ ነገር የሚያፈላስፍ፣ ወይም ምንም እርባና የሌለው፣ ስትቅም የትና ከማን ጋር እያወራህ እንዳለህ የሚወስን ነገር ነው» ያለው ይገኝበታል።



ጂም ኬሲ የተባለ ዘጋቢ ሰንዴይ ታይምስ ለተባለው የአውስትራሊያ ጋዜጣ የሚከተለውን ጽፎ ነበር። «አርድሮስ ከ. ጆንና ከርላይ ምክዳቪት በጊቢያቸው የጓሮ አትክልት መትከል ይወዳሉ። ይሁን እንጂ መጤ አፍሪካውያን ወረራ ያካሂዱባቸዋል። ተክሉ አምሮና ደምቆ ቢያድግም በሌቦች እስከ ጫፉ ድረስ ተከርክሞ ይወሰዳል። አፍሪካውያኑ ባህላዊ ስርዓታቸውን በመከተል በገጠራማ አከባቢዎች ተክሉን ማሳደግ ጀምረዋል።»[28]



*አፍሪካውያንንና አውስትራሊያውያንን ያወዛገበው የጫት ተክል ይህ ነው*

ምክዳቪት እንዳለው የጫት ተክሉ ከዓመታት በፊት አጓጊ ሆኖ አድጎ በነበረበት ወቅት ይህንኑ ያስተዋሉ አፍሪካውያን ግቢዬን አስከፍተው በመግባት ቁመቱ አምስት ሜትር የሆነውን ጫት ለመልቀም ትብብር ጠይቀው ተፈቅዶላቸው ነበር። አሁን አሁን ግን እንደ መጀመሪያ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳያቀርቡ በሳምንት ሁለት ጊዜ እየመጡ ይለቅማሉ። ይህንኑ ሌብነት ለማስቆም ተክሉ ላይ ግራሶ ተቀብቷል። ወደ ዛፉ ለመንጠልጠል እንዳያመችም የታችኛው ቅርንጫፍ ተከርክሟል። ዘጋቢው እንዳለው ምክዳቪት ለወራት እንደተከታተለው እንዳይለቅሙ የሚያስቆማቸው ምንም ሃይል የለም። የሚመጡትም ቁጡ ስሜት አስከትለውና ሁለትና ሶስት በመሆን በቡድን ነው።

**«ጋራዤ ውስጥ ሆኜ ድምጽ ሰምቼ ስወጣ ተክሉ ላይ ሰዎች ተንጠልጥለዋል። ቆይቶ በላስቲክ የተጠቀለለ ነገር ወደ መሬት ተወረወረ። ዛፉን በማሳደጉ በኩል ኩራት ቢሰማኝም የሌብነት ወረራው በዚህ ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ ዛፉን ለመቁረጥ እገደዳለሁ።»** ብሏል ምክዳቪት

ቲም ፓርከር የተባለ የፓርክ ባለቤት እዛው ሀገር ከጫት ዛፍ ላይ ቅጠሎች ለምን እንደሚጠፉ ከብዙ አከባቢዎች ጥያቄ እየየቀረበ እንደሆነ ተናግሯል። በመቀጠልም በአውስትራሊያ ውስጥ ጫት በችግኝ ማፊያ ቦታዎች የማይገኝ ተክል በመሆኑ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት በጣቢያዎች አልተራባም። ተክሉ ብዙን ጊዜ የሚተከለው በገጠራማ አከባቢዎች በመሆኑም ስርቆቱ እየበዛ ስለመጣ ባለቤቶቹ ይቆርጣሉ።

በ1980ቹ ተካሂዶ በነበረው ጥናት የትንሽዋ ሀገር ጂቡቲ ነዋሪዎች በየአመቱ ከአንድ መቶ ሰባ ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ እንደሚያደርጉ የተገለጸ ሲሆን እ.አ.አ. በ1977 ጂቡቲ ነጻነትዋን ስታገኝ ፕሬዚደንት ጉሌድ አፕቲዶን ጫትን ለማስቆም ሞክረው ዙፋናቸው ተነቃንቆ ነበር። ለዚህም ይመስላል ዮዲት ማይሰር የተባለች የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጠኛ፡-

«የትንሽዋ ሀገር ትልቁ ንግድ፤ በአዋጅ ያልተነገረ፤ ነገር ግን የጂቡቲ ብሄራዊ ተክል።" ያለችው። እ.አ.አ በ2006 ኒውዮርክ ከተማ «ኦፕሬሽን ሶማሊ ኤክስፕረስ» በሚል ስያሜ አንድ ከተማ አቀፍ ዘመቻ ተካሂዶ ነበር። በዚህ ዘመቻ ላይ አስር ሚሊዮን ብር የሚገመት ሃያ አምስት ቶን ጫት ተይዟል። በዚያን ወቅት ይህንኑ ጫት በሚያዘዋውሩ ሰዎች ላይ አስር ዓመት የሚደርስ እስራት ተፈርዶባቸዋል። የህገወጥ ንግዱ



ተሳታፊ የነበረው አንድ ሶማሊያዊ በዋሽንግተን ዲሲ ታስሮ በነበረበት ወቅት የሚከተለውን ብሎ ነበር፡-

***«ብኔ ግምት እንዲህ አይነቱ አፈሳ ትክክል አይደለም። ከኛ በላይ ስለ ጫት የሚያውቁ ይመስላሉ።»***



በውጭ ሀገር የፖሊሶችን ፍተሻ ለማለፍ ጫት እንዲህ ይንከራተታል።
ፎቶ ከድህረ-ገጽ

በአሜሪካው ሳንዲያጎ ዩኒቨርሲቲ የምረቃ ጽሁፍ ያዘጋጅ የነበረው ስታርሊን መሀመድ የተባለ ሶማሊያዊ ስደተኛ ጫት ቤተሰባዊ ምጣኔ ሃብታዊ ችግር የፈጠረና በየቀኑ የሚጠቀሙ ሰዎች ቤተሰባዊ ህይወታቸው ፍቺ እስከማስከተል የደረሰ እንደሆነ በአደባባይ ተናግሯል።

ሮብ ስሚዝ የተባለ እንግሊዛዊ ሶማሊያን ጎብኝቶ በነበረበት ወቅት ሶማሊያውያን ሴቶች ጫትን አይወዱም ይባላል ብሎ ጠይቆ ነበር። ከወንዶቹ ያገኘው ምላሽ

**«እኛ አብዘኛውን ውሎአችንን በጫት መቃም እናሳልፋለን:: ባለቤቶቻችን ደግሞ ወደ ውጭ ያያሉ:: ከምንም ነገር በላይ ቀንና ሌሊት እየቃምን ለጫት ከፍተኛ ወጪ እናደርጋለን::»** ብለው እንደነበረ ጽፏል::

እንደዚያ ከሆነ ጥቅሙ ምንድን ነው? ለምንስ ትቅማላችሁ ብለው ሲጠይቃቸው የሰጡት መልስ፦ **«ምንም ይሁን ምን አድገንበታል::»** በማለት ተጨማሪ ጥያቄ እንዳይጠይቅ አውግዘውታል::

በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 10 ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት
Arada Sub-City Woreda 10
Culture & Tourism Office



## ማጠቃለያ

ቡና በዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው በሀገራችን በኢትዮጵያ ነው:: እንኮራበታለን:: ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ የሰው ልጅ ቅሪተ አካላትም በሀገራችን በተጨባጭ ተገኝተዋል:: እነዚህም ሀገራችን የሰው ልጅ መገኛ እንደሆነች የሚያሳዩ የታሪክ ማስረጃዎቻችን ናቸው:: እንደገና እንኮራባቸዋለን::

ጫት ወይም በተለምዶ በብዙ የሀገራችን አካባቢዎች በርጫ ተብሎ የሚታወቀው የጫት ተክል ለተለያዩ አይነት ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ አገልግሎቶች ይውላል:: ጫት ለነዚህ አገልግሎቶች ጥቅም ላይ ከመዋል ባሻገር ጥቅምና ጉዳቱ ምን እንደሆነ በጥናት ተረጋግጦ ለአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በተገቢው ሁኔታ አልተሰራም ማለት ይቻላል:: ይህ ማለት ግን አብዘኛው ተጠቃሚ ህብረተሰብ የማንበብ እድል በማያገኝባቸው መድረኮችና መደርደሪዎች የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች የሉም ማለት አይደለም:: ያም ሆነ ይህ አብዘኛዎቹ ተመራማሪዎች ካታ-ኤዱሊስ በሚል ሲያሜ የሚያውቁት ጫት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው በኢትዮጵያችን መሆኑን ነው:: እውነተኛው ታሪክ ይህ ሆኖ እያለ የሚያከራክር ነገር ግን የማያስማማ መረጃ የጻፉ ተመራማሪዎችም በጥቂቱ ይገኛሉ:: ኢትዮጵያን ብሎም አፍሪካን ተሻግሮ በሁሉም የዓለማችን ጫፍ ተስፋፍቶ ጥቅም ላይ እየዋለ የመጣው ጫት በአብዘኛዎቹ ምዕራባውያን ስነጽሁፍ khat ተብሎ ይጠራል::

በአሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ጎኑ ዓለም አቀፍ ገበያዎችን ህጋዊና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ሰብሮ የገባው ጫት በአንዳንድ የውይይት መድረኮች ትልቅ አጀንዳ ሆኖ እንደነበረ የሚገልጹ መረጃዎችም አሉ:: ተክሉ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘ ስለመሆኑ ብዙዎቹ በመረጃ ቢያረጋግጡም እንዴት ተገኘ ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ መላምቶች አሉ:: ከነዚህም መካከል የመጀመሪያዎቹ የሀረር ከተማ ነዋሪዎች የሆኑት ሀረሪዎች በቦታው ሲከትሙ ተክሉ እዛው ስለነበረ መቃም ተጀመረ የሚለው ነው:: ሌላው ከሀረር አከባቢ የተገኘው አፈ-ታሪክ እንደሚያመለክተው ጫት ለሰው ልጅ ስለመገለጹ ሁለት መላምቶች እንደነበሩ ይነገራሉ:: አንዱ ሁለት ቅዱሳን የእስልምና እምነት ተከታይ አባቶች ወደ ፈጣሪያቸው ጸሎት በማድረግ ላይ እያሉ የጸሎት ስነስርዓቱ ሳያበቃ ደክሟቸው ኖሮ ብርቱ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል:: በዚህም የተነሳ ጸሎታቸውን ሳያጠናቅቁ በመቅረታቸው አዝነው በጸሎት ወቅት ድክም እንዳይሰማቸው የሚያነቃቃ ነገር ፈጣሪ እንዲሰጥ ተማጽነው ለዚያ ምላሽ ሰጣቸው ይባላል::



ጫት የገንዘብ፣ የጊዜና የጤንነት አሉታ ጎን አለው::(ፎቶ ከድሀረ-ገጽ)



ሁለተኛው አቀራረብ ደግሞ አንድ የፍየሎች እረኛ አንዲት ፍየል በየቀኑ ወደ ጫካ ሲትሄድ ድብርት እንደሚጫጫናትና ማታ ማታ ደግሞ ወደ ቤት እየቦረቀች ስትመለስ አይቶ ኖሮ እሱም በተራው በመቅመሱ ቀስ በቀስ ሱሰኛ ሆኖ ቀረ ይላሉ በሀረር አከባቢ የሚገኙ ሽማግሌዎች:: ከዚያም በሁሉም ቃሚ ዘንድ ተለመደ:: ተዘወተረም ይባላል::

በበቂ መረጃ የተደገፈ ባይሆንም ታላቁ አለክሳንደር ለስንፈት፣ ለድብርትና ለፍርሃት ማስወገጃ እንዲሆን ወደ አከባቢው ማስገባቱን የጻፉ ጥቂት ተመራማሪዎችም አሉ:: ታላቁ አለክሳንደር ጫትን ለጦሩ ማነቃቂያነት እንደሚጠቀምም አንዳንድ ምንጮች[30] ያመለክታሉ:: ክርስተፎር ዋርድ[31] የተባለው ተመራማሪ እንደገለጸው ታላቁ አለክሳንደር ጫትን ወደ የመን አመጣ የሚለው ብሂል የራሳቸው የየመኖች ነው:: በመሬቱ አቀማመጥ የተነሳ በወቅቱ በሀረር ከተማ የነበረውን መጫጫንና ድብርት መቋቋም እንዲችሉ በየመን አከባቢ ለጦሩ ይጠቀም የነበረውን ጫት ወደ ሀረር ልኳል የሚሉም ከላይ የተጠቀሱ አይነት ጸሃፊዎች አሉ:: በጥንት ዘመን ግብጻውያን ተክሉን ለምትሃት ይጠቀሙ እንደነበረም አንዳንድ ጽሁፎች ያመለክታሉ:: ( Muses et.al 1989].



የጫት ገበያ በሀራራ ሰዓት እንዲህ ይነቃቃል (ፎቶ ከድህረ-ገጽ)

ከአብዘኛዎቹ ምንጮች ማረጋገጥ እንደሚቻለው የጫት መገኛ ሀገር ኢትዮጵያ[32] ከኢትዮጵያም ደግሞ ሀረር ነው (Libermn,Mark 2003 28: 217-229 ):: ጫት ቀደም ሲል በዋንኛ ነት የሚታወቀው የሀረር ከተማ የመጀመሪያዎቹ ነዋሪዎች በሆኑት በሀረሪዎች ዘንድ ብቻ እንደነበር የሚገልጹ ህያው መረጃዎች በምርምር ጽሁፎችና በድህረ-ገጾች ይገኛሉ:: ድቦረስ የተባለ ተጓዥ በበኩሉ የሀረር ከተማን ጎብኝቶ በነበረበት ወቅት ጠጅ በጌሾ እንጂ በጫት እንደማይሰራ ካለመረዳት ይመስላል በጫት ቅጠል ሃይለኛ መጠጥ ይሰራበታል ብሏል:: «የቅዱሳን ምግብ»፤ «በፈጣሪ የተባረከና ለሰው ልጆች የተሰጠ ስጦታ»፤ «መለኮታዊ ምግብ»፤ «የአሳህ ቅጠል»፤ «የገነት ተክል» እና ሌሎችም የሚያማምሩና የሚማርኩ ስሞች ያሉት ጫት ጥንት መቃም ሲጀመር ለመንፈሳዊ አገልግሎቶችና ለጸሎት ይሁን እንጂ ዛሬ በባህላዊና በልማዳዊ ውሎዎች ሁሉ ሲዘወተር ይታያል:: ተክሉ እ.አ.አ በ1887 በሀረሪዎችና በምኒልክ ጦር መካከል ደም አፋሳሽ በሆነና ብዙ ሀረሪዎች



ባለቁበት የጨለንቆ ጦርነት ሳቢያ ይፋ ሆኖ በሌሎችም ሊታወቅ በቃ::[33] ይላሉ የታሪክ ተመራማሪዎቹ::

*ከዚያ በፊት ተጠቃሚዎቹ ተክሉን ከፈጣሪ ለቅዱሳኖች አምልኮ ስርዓት ብቻ የተፈቀደ በረከት አድርገው ይገምቱ ስለነበረ ከነርሱ ውጭ ለሌሎች አከባቢዎች ነዋሪዎች አሳልፎ የሚሰጥ ወይም እንዲተክሉ የሚያደርግ ሰው ቢኖር እስከ ሞት በሚደርስ ቅጣት ሊቀጣ ይችል እንደነበረም ይነገራል:: ጫት እርሻ ውስጥ የተተከለበት በሌሎች እንዳይታወቅም ሌላው ምርት ከተዘራ ወይም ከተተከለ ከአንድ ሳምንት በኋላ ይተክል ስለነበር ፈልጎ ለማግኘት ቀናት ይፈጅ ነበር:: እንደተመራማሪዎቹ ግኝት ይህንኑ ምስጢር ለመደበቅ እንዲያስችል ነበር ሽማግሌዎችና መንፈሳውያን አባቶች ብቻ ጥንት ይቅሙ የነበረው:: ከላይ ከተጠቀሰው ደም አፋሳሽ ጦርነት በኋላ ግን ሚስጥሩ ይፋ ስለወጣ ሌሎች የአከባቢው ነዋሪዎች የተክሉ አምራቾች፤ ተጠቃሚዎችና ለገበያ አቅራቢዎች ሆኑ:: ራቅ ወዳሉ ሀገሮች በፍጥነት መሰራጨትም ቀጠለ ይላሉ ታሪካዊ ጽሁፎቹ ::*

በሳይንሳዊ አጠራሩ ‹ካታ ኤዱሊስ› ወይም የሚበላ ተክል ተብሎ የሚታወቀው የሀገራችን ምርት (በርጫ) ከላይ የተጠቀሱትን ስያሜዎች ያገኘው ያለ ምክንያት አይደለም:: ከአፈታሪክና ከአንዳንድ የጽሁፍ መዛግብቶች እንደምንረዳው የጥንቶቹ የሃይማኖት አባቶች ጫት መቃም ሲጀምሩ ብቻ ሳይሆን እርሻ ውስጥ ገብተው ለራሳቸው መቃሚያ የሚሆን ቅጠል ሲቀነጥሱ እንኳን አስቀድመው ገላቸውን ይታጠባሉ ይባላል:: ጫቱን የሚጠቀልሉበትን ጨርቅ ደግሞ አጥበውና አድርቀው በንጽህና ይይዛሉ:: በንጹህ አዕምሮ፤ ባማረ አለባበስና በጸዳ ሰውነት ለመቃም ይዘጋጃሉ:: ከላይ ለመግለጽ

እንደተሞከረው ሁሉ ጫት ሲጀመር ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ ነበር። ዛሬ ዛሬ «የብዙ» ሰዎች፤ የሁሉም ሃይማኖቶችና አከባቢዎች ባህልና ልማድ እየሆነ ነው። በምስራቅ አፍሪቃና በዐረብ ባህረ-ሰላጤ ሀገሮች ከማህበራዊና ምጣኔ-ሀብታዊ አገልግሎት አልፎ ጠንካራ የፖለቲካ መሣሪያ (ጡንቻ) እስከ መሆንም ደርሷል። ታዲያ በዚህ ከቀጠለ እኛንስ አምራቾች (ተጠቃሚዎችን) ወዴት ይመራን ይሆን?!

ተክሉ ለሀገር እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ቀላል ላይሆን ይችላል። አምልኮአዊ፤ ባህላዊና ልማዳዊ አጠቃቀምን ተከትሎ በተጠቃሚዎች ላይ እያደረሰ ያለው አካላዊ ፤ ስነልቦናዊና ቤተሰባዊ ጫናው በመልካም አኗኗር ላይ ስር የሰደደ ተጽዕኖ እያደረሰ ነው የሚሉ ተቺዎች ደግሞ ጥቂት አይደሉም። ጫት ዛሬ በርካቶችን የራሱ ባሪያ አድርጎአቸዋል። እሱን ሳይቅሙ መዋልም ሆነ ማደር አስገዳጅ የህይወት አካል ተደርጎ ይወሰዳል። ከምንም ነገር በላይ ለሱ ቅድሚያ በመስጠት እስረኛ ሆነዋል። አልኮል በሙስሊሙ ዘንድ በቁራን የተከለከለ በመሆኑ ጫት በዚያ ምትክ የተሰጠ ስጦታ ነው የሚሉ ወገኖችም በብዙ አከባቢዎች አጋጥመውኛል። ተከራክረውኛልም። ለረጅም ጉዞ፤ ለጸሎት፤ ለከባድ የጉልበት ስራ፤ ለሠርግ፤ ለልደት፤ ለለቅሶ፤ ለባህላዊና ሃይማኖታዊ በዓላት ብቻ ለሁሉም አገልግሎቶች ይውላል። ዳሁሉምጣ ይጠቀማል እስከ ማለት ተደርሷል።

የቃሉ ትርጉም በዐረብኛ ከሚሰጠው ፊቺ ጋር በማያያዝ ተክሉ ለ501 የሀመም ዐይነቶች የፈውስነት[34] ባህርይ አለው ተብሎ እንደሚታመን የጻፉ ተመራማሪዎችም አሉ። ለዚህም ምክንያቱ በዐረብኛ Ga-a-t [ Gaat] የሚለው ቃል Ga=400 +



a=100 + t=1=501[33] የሚለውን ትርጉም ተከትሎ እንደሆነ ተጽፏል። ስለ ጫት ባህላዊ መድሃኒትነት ጥናት ካደረጉ ምሁራን መካከል ለይረስ የተባለ ተመራማሪ በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ስርዓት ቅጠሉን እየቃሙ እንትፍ እንትፍ[35] ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የረጅም ጊዜ ልማድ መሆኑን ጽፏል። ለዚህም እርግጠኝነት በአዲስ ኪዳን መጽሃፍት ውስጥ ተጠቅሷል ይላል። ማጣቀሻ ያደረጋቸው ወንጌላትም ማርቆስ ምዕራፍ 8/23 እና ዮሃንስ 9/6 ወንጌላት ሲሆኑ በየወንጌላቱም ላይ የሚከተሉት ጥቅሶች ተጽፈው ይገኛሉ፦

**«ዕውሩንም እጁን ይዞ ከመንደር ውጭ አወጣው። በአይኑም ተፍቶበት እጁንም ጭኖበት አንዳች ታያለህን ብሎ ጠየቀው»**

**«ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ። በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን አይኖች ቀባና ሂድና በሳሌሆም መጠመቂያ ታጠብ—»** አለው የሚሉ ናቸው። ከላይ በተጠቀሱት ቅዱሳን መጻህፍት «ተፍቶበት» ወይም «እንትፍ» ብሎ የሚሉ መንፈሳዊ ቃሎች እንትፍ የተባለው ጫት ይሁን አይሁን ምንም የሚታወቅ ነገር የለም። ማረጋገጫም አልተገኘ ለትም።

ስለ ጫት የሚነገሩም ሆነ የሚነበቡ መረጃዎች አሁን አሁን በተለይም በጋዜጦች ላይ እየበዙ መጥተዋል። በዚህም መሰረት ጫት ይከለከላል የሚል ያልተረጋገጠ ወሬ የሰማ አንድ ዐረባዊ ቃሚ በበኩሉ ፡ -

**«ጫት የአላህ ቅጠል ስለሆነ በሰዎች ቁጥጥር ስር ሊውል አይገባም»**

ማለቱ ይነገራል።

*ነዋሪነታቸው ጎዴ የሆኑ አንድ የአካባቢ ማህበረሰብ መሪ ደግሞ ፡-*

***«ለህብረተሰባችን ወደር-የለሽ ጎጂ ነገር፡፡»*** *ብለዋል*

*አንድ የክርስትና እምነት ተከታይ በበኩላቸው ሲናገሩ፡-*

***«ኢየሱስን እንወደዋለን፤ ንስሃም እንገባለን፡፡ ነገር ግን ለኛ ጫትን መተው ከባድ ነው፡፡ኢየሱስን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡»***

*ብለው የምራቸውን ተናግረዋል፡፡* ሌላው ቃሚ በበኩሉ

***«እኔ ጫትን አልተውም፡፡ ጫትም እኔን አይተወኝም፡፡ እንዲያውም ስሞት በጫት ተክል ስር እንዲቀብሩኝ ቤተሰቦቼን እማጸናለሁ»***[36] ማለቱ ተጽፏል፡፡



*በጫትና በሺሻ የስሜት ምጥቀት ላይ የሚገኝ ቃሚ፡፡ ፎቶ ድሀሬ-ገጽ*

ቁጥራቸው 1087 የሚሆኑ የምስራቅ አፍሪካ ሴቶች ፋውንዴሽን በሚኖሩበት አውስትራሊያ ሀገር ለሀገሪቱ ፓርላማ ም/ቤት የጫት ሽያጭ፤ ስርጭት፤ ዝውውርና አመራረት



እንዲቆም ተፈራርመው ጠይቀዋል፡፡[37] በእንግሊዝ ሀገር ሌስስተር ግዛት ነዋሪ የሆኑ ሶማሊያውያን ሴቶች፡-

**«... *በጫት* ምክንያት ልጆቻችን ትምህርታቸውን እያቋረጡ ስለሆነ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ ይታገድልን፤ በተለይም አዛውንቶች በመቃም በርካታ ገንዘብ ያባክናሉ፤ በድብርት ይጨነቃሉ»**

የሚል ተማጽኖ አቅርበዋል፡፡ እነዚሁ ተማጽኖ አቅራቢዎች በዚሁ ጥያቄያቸው በቤተሰቦቻቸው መካከል የማህበራዊ ህይወት መናጋት፤ የአዕምሮ መዛባትና የስነልቦና ቀውስ እንዳጋጠማቸውም አልሸሸጉም፡፡ አንዳንድ የጫት ተመራማሪዎች እንደሚገልጹት የጫት ቃሚዎች ቁጥር በሀገራችን እየበዛ እንዲመጣ ካደረጉ ምክንያቶች አንዱና ዋንኛው **«ዳየዕድገት በህብረት የዕውቀትና የስራ ዘመቻ»** ነው፡፡ የሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በጠቅላላ የሀገራችን ክፍሎች ዘምተው በነበረበት ጊዜ አብዘኛውን ጊዜ የሚያሳልፉት ገጠር ስለነበረ መቃም ለመዱ፡፡ ይህንኑ ሱስ ከዘመቻ መልስ ወደየዘመቱባቸው አካባቢዎች ሲመለሱ በገጠርም ሆነ በከተማ አስፋፉት፡፡ በእርግጠኝነት እያስፋፉ መምጣታቸው ብቻ ሳይሆን እንደ ሰደድ እሳት አቀጣጠሉ የሚሉ የወቅቱ ዘማቾችም አሉ፡፡ ከዚያም የቃሚዎች ቁጥር እየተበራከተ ቢመጣም ስር የሰደደ ሱስ ሆኖ በተጠቃሚዎች ላይ እያደረሰ ያለው አሉታዊ ተጽዕኖ ጎልቶ እንዳይወጣ መደረጉ ይነገራል፡፡ በሌላ አገላለጽ አዎንታዊና አሉታዊ ጎኖችን መጻፍ የሚገባቸው ጸሃፊዎች ራሳቸው ይቅሙ ስለነበረ ይኃው እውነታ ጎልቶ እንዳይወጣ ተደርጓል ይላሉ፡፡

ሌሎች እንዳመለከቱት ደግሞ እነዚህ ሰዎች ነጻነታቸውን ጫት የቀማባቸውና ባሪያ ያደረጋቸው፣ ህይወትን በራሳቸው እይታ ብቻ የሚተረጉሙ፣ ስነልቦናዊ ቀውስ ያጋጠማቸው፣ እውነታዎችን እየካዱና ከራሳቸው እንደበት ተደብቀው የሚኖሩ የሚመስላቸው፣ እውን መሆን የማይችል ተስፋን ከስውር ሀይል የሚጠብቁና በስውር ሃይል ማምለክ የጀመሩ ናቸው:: ስለዚህም በአንዳንድ ህብረተሰብ አኗኗር ጫት የዕለት ከዕለት ተግባር ብቻ አይደለም:: ለዕለት ከዕለት ተግባር እንደ ዳቦና ውሀ አስፈላጊም ተፈላጊም ነው:: በህብረተሰቡ ማህበራዊ አኗኗር ተጽዕኖ ፈጣሪና ውጤት አምጪ ተደርጎም ስለሚቆጠር የህዝቡን ፍላጎት ገዥ ተክል ተደርጎ በበርካታ አከባቢዎች ይወሰዳል:: ከረጅም ዘመናት ጀምሮ ጥቅም ላይ በመዋሉም በተጠቃሚዎች ባህላዊ አስተሳሰብ ውስጥ ቀላል የማይባል ክፍተት አስከትሏል::

እንዲያውም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የትምህርት ተቋማት ሱሰኞችን የሚያበረታቱ መንደሮች ሆነዋል የሚሉ ታዛቢዎች ጥቂት አይደሉም:: ይህ ጽሁፍ በዋንኛነት በጫት ላይ ያተኩር እንጂ ከጫት ባልተናነሰ ሁኔታ በሌሎች መጤ-በሚባሉ አደንዛዥ ዕጾች የተላመዱ ተጠቃሚዎች ቁጥርም የሚናቅ እንዳልሆነ ያምናል:: ሱሰኝነቱም ለአካላዊ፣ስነልቦናዊ፣ ምጣኔ-ሀብታዊና የጤንነት ቃውስ ዳርጓል ማለት ይቻላል::

ከዋና ከተማችን አዲስ አበባ ጀምሮ እስከ ክልል ከተሞቻችን ድረስ ዕጾቹ በፍጥነት እየተሰራጩ መሆኑ ትኩረት የሚሻ ይመስላል። ዕጾቹ በማንኛውም ስፍራና ጊዜ ተደራሽ እየሆኑ መምጣታቸው በተለይም አንዳንድ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች ጫት ካልቃሙና ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን ካልተጠቀሙ በትምህርታቸው ውጤታማ



እንደማይሆኑ አድርገው እስከ መገመት ደርሰዋል። የማይቅሙ ከሆነ ደግሞ በከተሜዎቹ ያልሰለጠኑ ተደርገው የመታየት ሁኔታ እየደረሰባቸው ነውም ይባላል። ውይይት ካደረግንባቸው በርካታ መረጃ ሰጪዎቼ መካከል የጫትን ጉዳት የሚያናንቁ እንዳሉ ሁሉ ማቆም ካልቻሉ ህይወታቸውን በአግባቡ መምራት እንደማይችሉ እየተረዱ የመጡም በብዛት አጋጥመውኛል።

ውድ የሆነውን የመንግስት የስራ ሰዓት በመቃም የሚያሳልፉትንና ካልቃሙ ዐይናቸው ፊደል መለየት የማይችሉት ዜጎች ሁኔታ በዚሁ አካሄድ የሚቀጥል ከሆነ ችግሩ ከሱሰኝነት አልፎ ለወደፊቱ የልማት እንቅስቃሴያችን ሁሉ አደጋ ከመሆን አይቀርም። ከማህበራዊ ችግርነትም አልፎ የፀጥታ ችግር እስከ መሆን እንደሚደርስ በሜክሲኮ፣ በአፍጋኒስታን፣ በኮሎምቢያ፣ በባርማ፣ በላኦስ፣ በቬትናም፣ ኢራን ወዘተ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ያሳያል። የጫቱ አሳሳቢ ነው እያልን እሱኑ መቆጣጠር ሳንችል ቀርተን ስንዘገይ የማሪዋና፣ የኮኬይን፣ የሄሮይንና የካናቢስ ዕጾች መናኃሪያ እንዳንሆን ከወዲሁ ማሰብ ግድ ይላል። ለዘመናት አብሮ የቆየና የተዋሃደ በመሆኑም ስሜታዊ ሳይሆን በጥናት የተደገፈ መፍትሄ ማስፈለጉ አይቀሬ መሆኑን ነባራዊ ሁኔታው እየጠቆመ ነው።

በአሜሪካ፣ በካናዳ፣ በምዕራብና ምስራቅ አውሮፓ ... ወዘተ ሀገሮች በርካታ ዜጎችን ለችግር የዳረጉት እነዚህ ዕጾች ጉዳታቸውና ጥቅማቸው ለህብረተሰቡ መረጃዎች ናቸውና በተገቢው ሁኔታና በወቅቱ እንዲደርሱ ጉዳዩ ይመለከተናል የሚሉ ሁሉ (ለነገሩ ጉዳዩ የማይመለከተው የለም) ሊያስቡበት

ይገባል፡፡ የሀገራችን የስነልቦና ጠበብትና የህክምና ምሁራን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን በመጠቀም በተለያዩ ማስተማሪያ ዘዴዎች ቢያሰራጩ ሱሰኞቹ ብቻ ሳይሆኑ ቀጣይ ትውልድ ጭምር ተጠቃሚና መረጃ አዘል ይሆናል፡፡ ለነርሱ ደግሞ መንግስት ከጎናቸው እንደማይለይ እርግጠኛ ሆኜ ነው ይህንን የምለው፡፡ ለጓደኛ፤ ለዘመድ፤ ለዜጋ በአጭሩ ለዜጎች ሁሉ ጎጂ ሱስ ሳይሆን ጥሩ ባህል እናስተምር፡፡ ለሁሉም ፍቅር፤ ሣቅ፤ ዕውቀት፤ አመራር፤ ተስፋ፤ ህይወት፤ ጊዜ፤ ገንዘብ፤ ክህሎት፤ ጤና፤ መቀራረብ፤ ትኩረትና ምክር እንስጥ፡፡ ጠቃሚ ያልሆኑ ሱሶችን አሳማኝ ባልሆነ ቋንቋ ሳይሆን ጠንክር ባሉና በተከታታይ አስተምህሮዎች ጊዜ ሳናጠፋ በመስጠት ልንቋቋማቸው የሚገባ ይመስለኛል፡፡ በተለይም የቀጣዩን ትውልድ ህይወት ወዳልሆነ አቅጣጫ የሚገፉ አጋጣሚዎችን ሁሉ ወገኖቻችን ናቸውና ልንጋፈጥና እነርሱም በተራቸው የሚጋፈጡበትን መንገድ ልናሳያቸው ይጠበቅብናል፡፡ በየቤቱና በየአከባቢው በዚህ ሱስ ሳቢያ የጨለሙ አዕምሮዎችና ስሜቶች ብሩህ የህይወት ተስፋ እንዲሰንቁ በማድረግ በስነምግባር የታነጸና የህይወት ምዛኑን የጠበቀ አኗኗር እንድንመራ ይገባናል፡፡



## ጫት ትናገራለች፡ ፡

ተደብቄ እያለሁ ፍየል ቀመሰችኝ
ልክላክላት ፈልጌ መናገር
አላስቻለኝ፡፡
መርዝ ነኝ ብያትም ልትተወኝ
አልፈለገች
ቀምሳ ምርቃና መሆኔን አወቀች፡፡
ውስጤ ያለው ቅመም በምሽት
ቀስቅሷት
እንቅልፍ ነስቼ ኮከብ
አስቆጠርኳት፡፡
ባለ ፍየሉም ተነሳ ሁኔታዋን
ሲያያት
ተቅበዝብዛ ሮጠች አረንጓዴውን
ለመብላት፡፡
እንዲያው ሲንከባለል ሌሊቱ ነጋበት
ጣሪያ እያስቆጠርኩ እንዲሁ
አሳደርኩት፡፡
በሶላት ወቅት እንቅልፍ ጀመረው
እረኛውም ተጠጋ ቅጠሏን
ሊቀምሳት
ፊቱ እስኪያብጥ ጉንጩን
ሞላው
ምላሱም ተፍታታ ደስታም
ተሰማው፡፡
ከባዱን ጉዞ አንድ ርምጃ
አደረጋት
የተሸከመውም ዕቃ የዶሮ ላባ
ሆነለት፡፡
ቤቱ መመለስ ፈለገ ግን
አቃተው
ከብዙ ድካም በኋላ አገኘው፡፡
ሊተኛ ቢፈልግ አልጋ ጠፋበት
እንደ እው ሀኪምጋራ ዱካክ
ተጫነው እንደተጣላ ሰው
ጎሮሮውን አነቀው፡፡

Arada Sub-City Woreda 10
Culture & Tourism Office

እንዲያው ሲያንኮራፋ ሶላቱንም
ሳይሰግድ
እፉን እንደ ከፈተ እንትልፉንም
ሳይጠግብ ክፋትን ሲያስብ በሀሳቡ
ፎቅ ሲሰራ
ዳግም ሳለመቃም እርም መሰሰበት
ዐይኑ ሲከፈት ፋታ ይፈልጋል
ጠመንጃ አስመስሎ በብብቱ
ይሸጉጣል
መቃም ሲጀምር ሥራውንም
ይዘነጋል፡፡
ከማበዱበፊትቢተወኝ ይሻለው ነበር
የወንዶቹ ሳያንስ ሴቷም ጀመረችኝ
ጥርስ አልባው ሳይቀር በሙቀጫ
ወቀጠኝ
ብር በኪሱ ያጣም በብድር ወሰደኝ፡፡
ከልጆቹ ጎሮሮ እኔን አስበለጠኝ

ሥራ ሳለመስራቱ ምክንያቱ እኔ
ነኝ
ወንዱን እሳብጃለሁ ሴቲቱስ
ብትተወኝ
ለጸሎት ነበር ሁለት ፍሬ ለንቃት
አያበዙም ነበር ጉዳቱን በመረዳት
የዛሬ ትውልድ እንደነሱ አይሁን
ከልቡ ያቁም በርጫ መቃሙን
ቆንጆ ኮረዳ ትጥላኝ
ከርታታ እንዳትሆን ተማሳጼን
ትስማኝ፡፡
ወደኔ አትምጣ ትጠብቅ
ውበትዋን ይቅርብሽ በሉልኝ፡፡

በሀረሪኛ ገጣሚ ኮሎኔል ማህዲ በርሀድሌ ይባላሉ፡፡ የተቀነባበረ ቢሆንም ለትርጉሙም ሆነ ግጥሙን ፈልጎ በመስጠት ስማቸው እንዳይገለጽ ለጠየቁኝ ለሀረሩ ተባባሪዬ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡



## የዘገምተኛዋ ጫት ቃሚ ምርቃና አባባሎች፡፡

ተው ማረኝና ልግባ ወዳገሬ
መጥምቁ ዮሐንስ የሀገሬ ገበሬ፡፡
መስከረም ስጠባ
ወደ አዲስ አበባ፡፡
ወይ ፋፋ
እየለ ወርደፋ፡፡
ወላጅ አይቶጣት
ዘመድ ማጣት፡፡
አይኔን መልሱ
እፈጌን በዳቦ አብሱ፡፡
ወይ ኛኛ

አንተ ጥብኛ፡፡
Love is milk
But not drink
አንተም አራዳ እኔም አራዳ
ምን ያጣላናል በሰው በረንዳ፡፡
ቡትቶ ለባሽ
የለውም አስዋተሽ፡፡
ወይ ጣጣ
አንተ ሚጥሚጣ፡፡
የኔ ታታ
የወንድ ከርታታ፡፡

# አከባቢያዊ የጫት መጠሪያዎች

በሀገራችን የተለያዩ አከባቢዎች ጫት ከሚጠራባቸው መጠሪያዎች መካከል:-

ታጫር (ፋታ)---ደቃቅ ጫት
ዴ (ጨ)ሬ-------ረጅም ጫት
አቃሬ----------መካከለኛ
ቀርጢ------ቀይና ተወዳጅ
ዑመርከሌ-------ፈዲስ አከባቢ
የሚበቅልና ሀይለኛ ጫት
ኮሎምቢያ----የባህርዳር ጫት
ዳሎታ--------ነጭ፣ ጆሮው
ትናንሽና ተፈላጊ ጫት
አወዳይ--- --በውጪ ሀገር
ሳይቀር ተፈላጊነት
ያለው ምርጥ ጫት
አቦ ምስማር---ተፈላጊነቱ በሀገር
ውስጥ የሆነ ተወዳጅ ጫት
ዘቢብ--------በዐረቢኛ ቆንጆ ጫት
መሆኑን ለማመልከት የተሰጠ
ሲያሜ
ጀፋላ-----ዝቅተኛ ተፈላጊነት
ያለው

በለጬና ወንዶ----- ከሲዳማ
የተለያዩ አከባቢዎች የሚቀርብ
ጫት
ገለምሶ------ከምስራቅ ኦሮሚያ
ገለምሶ ለገበያ የሚቀርብ ጫት
አጥሬሬ---------ተለቅሞ ለመጉረስ
የተዘጋጀ
ብርቃማ-----መጠነኛ ተፈላጊነት
ባለበት ወቅት የሚሰጥ መጠሪያ
ቡልቱ------ያደረ ወይም ትኩስ
ያልሆነ
ጨብሲ-----ምርቃና ማዳከሚያ
መጠጥ
ጎራባ-----ዋናው ከተቃመ በኋላ
የቀረው ልቅምቃሚ
ጀበና-----ጠዋት ጠዋት የዐይን
መክፈቻ ነው እየተባለ የሚቃም
ጫት



ሉሉቃቻ------አፍ ውስጥ
ተሞልቶ በአንድ ጊዜ በውሀ
የሚወራረድ ጫት
ጀዝባ-------በጫት የደነዘዘ ወይም
የሰከረ
ቃጥሬ-------እየቃሙ ማደር

ራብሳ------መቃም ከመጀመሩ
በፊት በገን ተደርጎ ለሌላ ሰው
የሚሰጥ
ዱካክ------ባለመቃም የሚመጣ
ድብርት፣ ቅዠትም ይሆናል
ምርቃና-------ከመቃም በኋላ
የሚመጣ የመነቃቃት ስሜት።

# ማጣቀሻዎች (Bibliography)


1. Chevalier [1943 ] " les cats d 'arable, d'Abyssinie et d'afrique orientale. Revue de botanque appalique 29:413. A/professor John Fitzgerald louse Laurense pty ltd 5, March 2009, p.4. Stevensen et.al.,1996. *Krinikorian, 1984; Kennedy,* 1987; Baasler, 1980; Al-habeshi & skaug,2005; "about khat".
2. Niebuhr m,travel through Arabia and other countries in the east.vol 11 Edinburgh 1792.224, Krinikorian, 1984; kennedy, 1987,about khat
3. Ratsch,the encyclopedia of psycho-active plants,park street press,1998
4. Ibid p.156
5. Kiple,K, 'the Cambrige world history of food'. Cambrige university of press,p 200
6. Ibid .356
7. P, Merab, impressions d, Ethiopia,vol 1,Paris H libert, 1921 p. 175-176
8. Ibid
9. Bob G Hills " Khat, East African agriculture 1947 p. 98
10. Richard Punchrast "an introduction to to the economic history of Ethiopia". London, 1961,p. 210.
11. J.Spencer Trimingham, Islam in Ethiopia, London 1952, p.228.
12. William Harrison "All about coffee". 2nd edition,1935, p. 661-662.
13. Ibid
14. Giannini, A J Price W A, Shaheen J A " Khat an other drug of abuse". Journal of psycho-active drugs, 1986, 18. 155-159.U S register, vol, 60 [155] Aug, 11 1995.





15. C.C.f. Hantington, 1965, 55-56; Peruchon,1989,p 331; Trimingham,1965, p.228. Forskal, flora, Aeguptic-Arabico Havinae 1975.
16. Persian physician, Al-Samaraqandi,1237; Nezar N, Al-Hebshi & Nils Skaug, Oral micro-biology, university of Bergen, Norway, 2005 10: 299-307.
17. "adverse effects of khat". A review 1 doc. 2006. US federal register, vol,60 [155], peruchon, 1989, p.331; Trimingham, 1965, p. 228.
18. Al Biruni AAA, Abu Reyan AM, El saydra Fi El Tib, Ed,Hakim Mohammed Said, " In the book of pharmacy and material medica, Karachi,Hamdard national foundation,1973 [Arabic].
19. A.D. Krikorian and its use: an historical perspective, 1973 ,Peters DWA, 1952, khat; its history,botany, chemistry,and toxicology,pharm,J,1952, p: 16-18.
20. Sir Richard Burton (1821-1890)" first foot steps in east Africa" 1856.
21. Kevin Rushby,"Eating the flowers of paradise".One man's journey through Ethiopia & yemen,NY,1999,p:59.
22. Rottenburg et.al 1982.
23. Daifalah and Santavy, University of hospital olomuuc, 2004
24. Kevin Rushby,"Eating the flowers of paradise". One man's journey through Ethiopia & Yemen,NY,1999, p.59.
26. Ibid:13
27. አዲስ ልሳን ጋዜጣ ሰኔ 1 ቀን 1994 ‹ሲናዊ ገጠመኝ›.
28. Australian Sunday times news paper, Oct, 23, 2005.
29. Et.al.et Amare Getahun & A.D.Krikorian, chat: coffee,s rival from Harar, Ethiopia. 1 botany, cultivation and use, economic botany, 1973, 27 p: 356.

30. Elmi,1983; national drug intelligence center, 2007.
31. Ibid
32. Amare Getahun and A.D. Krinikorian "about khat, coffee,s rival from Harar, Ethiopia.1 botany, cultivation and use, economic botany1973, 27: 370. Chevalier, A. (1949) les cat, sd, arabie, Abyssinie et de Afrique orientale
33. Leiris (1951pp.391, 415 passim and 1952, p.60.
34. Getahun and krikorian,1973; Kenndy, Teasue, kakaw & cooney,1983
35. Leius [1951, p.391, 415 passim; 1958, p.60] strelcyn, 1973, p.155; khat and its use: an historical perspective, Abrham D. Krikorian, August 5, 1984, NY, p.115.
36. Mereb,1921, vol.1 p .176,1929 vol.3.p. 491, anonymous, 1956
37. Australian News, Sep, 2008, Melborne.
38. The Titi Tudorancea learning center 1987

በመጠናቀቅ ያሉ ስራዎቼ:-

1. ተግባቦትና የዘመናዊ ጋዜጠኝነት ቀላል አቀራረብ
2. ባህልና ጨዋነት፣--- እና ሌሎችም



ወ/አማኑኤል ጉድሶ ከ20 ዓመት በላይ በጋዜጠኝነትና በህዝብ ግንኙነት ሙያዎች እያገለገለ ነው:: በፖለቲካል ጆርናሊዝም ኤም.ኤ ድግሪ ከቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት አግኝቷል:: የሀረሪ ክልል ጋዜጣና መጽሄት መስራችና ዋና አዘጋጅ ሆኖ ሰርቷል:: በደቡብ ክልል ከማስታወቂያ ቢሮ ጀምሮ እስከ ብዙሀን መ/ድርጅት ከሪፖርተርነት እስከ ም/ሥ አስኪያጅነት አገልግሏል:: በአከባቢያዊ ክልላዊና ሀገር አቀፍ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ አስተዋጽኦ አድርጓል፣ እያደረገም ነው:: በአደንዛገር ዕጾች በተለይም ደግሞ በጫት በዐይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን መጽሐፍ አቅርቧልና ያንብቡት::

"በተለይም ወጣቶች ጠቃሚውንና ጎጂውን ከወዲሁ ለይተው በማወቅ ራሳቸውን ለለውጥ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል:: "

ገጽ 7

" የገዛ ደሜን ጠጥቻለሁ:: ተነሳሽነቴም ከኔ ላይ በኗል:: --- ጥቁር ቆዳዬንና አስፈሪ ዐይኔን ይዤ ተመ፡ስዬ ካለሁበት ወደ አውሮፓ እየተመለስኩ ነው:: "

ፈረንሳዊው ባለቅኔና ገጣሚ አርተር ራምቦ (ገጽ 22)

"ይህ የጉዞ ታሪክ ነው:: ይህ የዕጽ ታሪክ ነው:: ይህ በዕጽ በነደደ ስሜት የተጻፈና በጫት መቃም ላይ ያነጣጠረ --- የጉዞ ታሪክ ነው:: ለማንበብ ተዘጋጅተዋል? እንግዲያው እንሂድ::"

ኬቨን ፌዳርኮ (ገጽ 29)

" ጫት የጫነ አይሮፕላን ሞቃድሾ ሰማይ ላይ በሚያንዣብብበት ጊዜ የሶማሊያ ጦር አበጋዞች ሁሉ በተኩስ ማቆም ስምምነት ላይ ይደርሳሉ:: "

ሰን ሚክላቪች (ገጽ 43)

"አንዳንዱ ወጣት ጫት መቃም ዘመናዊነትና ስልጡንነት መስሎ ይታየው ይሆናል:: "

መለስ ዜናዊ (ገጽ 59)

" ጫት የሰውን ክብር የሚያዋርድና አዕምሮን የሚያደነዝዝ ተክል በመሆኑ ሰው እንዲቅም አይደገፍም::"

ብጹዕ ዶ/ር አቡነ ገብርኤል (ገጽ 62)

"መንግስት ጫትን አያበረታታም፣ አያዳክምም:: ለማዳከምም አትሽጡ ብሎ ከማስ ነቅሎ ያቃጠለበት አጋጣሚ የለም::

ንግድ ሚኒስቴር (ገጽ 64)

**ዋጋ 35.00**

ህትመት፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ. 011 156 536